# <u>ምስጋና</u>

በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት በጽሑፍ ጥንቅር ለረዱት ለአቶ ሽመልስ አድማሴና ለአቶ ምኒልክ አስፋው እንዲሁም በገንዘብ ለደገፉት ለአቶ ንዋይ አርጋው፥ ረቂቁን በመተየብ ለተባበሩን ለወ/ሪት ሮማን ደምሴ አዘጋጆቹ በዚህ ጽሑፍ ተጠቃሚዎች ስም ልባዊ ምስጋና ያቀርባሉ።

**ገጽ**


<u>መክሥተ አርእስት</u> 1

መግቢያ 3

ክፍል ፩ ቤተክርስቲያንና አመራርዋ 7

ምዕራፍ አንድ፡- የቤተክርስቲያን ትርጉም ተግባርና ተመርሆ 8

1.1 ትርጉም 8
1.2 የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ተግባር 11
1.3 የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ተመርሆ 14

ምዕራፍ ሁለት፡- የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያንና አመራርዋ 18

ምዕራፍ ሦስት፡- የአጥቢያ ቤተክርስቲያን የአመራር መርህ ብዙኀናዊ ወይስ ዋሕዳዊ? 24

ምዕራፍ አራት፡- ሽማግሌ (እረኛ/መጋቢ፥ ኤጴስቆጶስ፥ ጳጳስ) 34

4.1 የስያሜ ተወራራሽነት 34
4.2 የሚያበራየው በሬ 39
4.3 ተጠሪነትና ተጠያቂነት 41

ምዕራፍ አምስት፡- ለቤተክርስቲያን መታነጽ የተሰጡ ስጦታዎች 44

ክፍል ፪ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን መስተዳድርና ዲኖሚኔሽን እንዲሁም የማኅበረ ምዕመናንና የሽማግሌዎች ኀላፊነት 52

ምዕራፍ ስድስት:- የአጥቢያ ቤተክርስቲያን መስተዳድር 53
6.1 የመስተዳድር ዓይነቶች 53
6.1.1 ኤጲስቆጶሳዊ መስተዳድር 53
6.1.2 ሽማግሌያዊ መስተዳድር 56
6.1.3 ማኅበረ ምዕመናናዊ መስተዳድር 58
6.1.4 ማኅበረ ምዕመናናዊ ወሽማግሌያዊ መስተዳድር 62
6.2 የአጥቢያ ቤተክርስቲያንና የዲኖሚኔሽን ግንኙነት 63

ምዕራፍ ሰባት:- የማኅበረ ምዕመናንና የሽማግሌዎች ኀላፊነት 70
7.1 የማኅበረ ምዕመናን ኀላፊነት ለሽማግሌዎች 71
7.1.1 ሽማግሌዎችን የማወቅ ኀላፊነት 72
7.1.2 ሽማግሌዎችን የማክበር ኀላፊነት 74
7.1.3 ሽማግሌዎችን የመታዘዝ ኀላፊነት 75
7.2 የሽማግሌዎች ኀላፊነት በቤተክርስቲያን 79
7.2.1 ሽማግሌዎች ቤተክርስቲያንን ያስተዳድራሉ 79
7.2.2 ሽማግሌዎች ምዕመናንን ይጠብቃሉ 81
7.2.3 ሽማግሌዎች ምዕመናንን ይመግባሉ 83
7.3 የምዕመናን ኀላፊነት ለቤተክርስቲያን 86
7.3.1 የአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል መሆን 86

ምዕራፍ ስምንት:- የሽማግሌዎች አመራረጥ መስፈርት 93

የግርጌ ማስታወሻ 117
የቃላት መፍቻ 123
ዋቢ መጻሕፍት 125

# መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቤተክርስቲያን የሚያስተምረው ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ሕዝብና የክርስቶስ አካል እንደሆነች ነው:: የቤተክርስቲያን ህልውና የተመሠረተው በክርስቶስ ትምህርትና በክርስቶስም ቤዛነት ላይ ነው:: ቤተክርስቲያን የ"ቅዱሳን ካህናት" (1ጴጥ 2÷5) ኅብረት ሆና "የእግዚአብሔርን በጎነት እንድትናገር" (1ጴጥ 2÷9) የተመሠረተች መንፈሳዊ ተቋም ናት:: ይህች ተቋም ከእግዚአብሔር የተቀበለችው ተግባርና ተልዕኮ አላት::

ስለ ቤተክርስቲያን አመራር የተለያዩ አስተያየቶች ሲሰነዘሩ ይሰማል:: አንዳንዶች ቤተክርስቲያን መመራት ያለባት በአንድ ሰው ብቻ ነው ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ የለም ቤተክርስቲያን መመራት ያለባት ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች ነው ይላሉ:: ታዲያ ትክክሉ የቱ ነው? መጽሐፍ ቅዱስስ የሚያስተምረው ስለየትኛው አመራር ነው? እነዚህንና ሌሎችንም ተዛማጅ ጥያቄዎች በግልጽ መመለሱ አስፈላጊነቱ እየጨመረ መጥቷል:: ለዚሁም ይረዳ ዘንድ ይህንን ጽሑፍ ማዘጋጀት ግድ ሆኖአል::

የመጽሐፉ ተቀዳሚ ዓላማ በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሊኖር የሚገባው የአመራር ስልት ምን መሆን አለበት? የሚለው ነጥብ የበለጠ እንድናስብበት ማነሳሳት ነው:: ቤተክርስቲያን መመራት ያለባት በአንድ ሰው ብቻ ነው የሚል አመለካከት በሰፊው በሚናኝበት ሰዓት ነገሩን በጥሞና መመልከት ተገቢ ይሆናል::

ቤተክርስቲያን መከተል ያለባት ዋሕዳዊ (የአንድ ሰው ብቻ) አመራርን ነው? ወይስ ብዙኀናዊ (የብዙ ሰዎች) አመራርን? ከሁለቱ የአመራር መርሆችስ የትኛው አመራር ነው ሰፋ ያለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አብነት ያለው? እነዚህ ጥያቄዎች ስለ ነገሩ ያለንን አመለካከት በእጅጉ ይወስናሉ:: አመለካከታችን ከግብታዊነትና ከግላዊነት እስካልጸዳ ድረስ

ለነገሩ የምንሰጠው ምላሽ መቼም ቢሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊሆን አይችልም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን የምንመራ ከሆነ ግን የትኛው የአመራር መርህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አብነት እንዳለው በተጨባጭ ማረጋገጥ እንችላለን። ከቅዱሳት መጻሕፍት እውነታ ጋር መስማማት መቻል ለክርስቲያን ራሱን የቻለ ዋና ጉዳይ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ዋሕዳዊና ብዙኀናዊ የአመራር መርሆችን ብቻ በማየት አናበቃም። ከዚሁ ጎን የምናነሳውና ትኩረት የሚሻ ሌላም ነገር አለ። ያም የሽማግሌዎች አመራረጥ ጉዳይ ነው።

በአገራችን ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ችል የተባለ ሁነኛ ነገር ቢኖር "*የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን ስንመርጥ ምን ምን ነገሮችን መመልከት አለብን?*" የሚለው ጥያቄ ነው። ሽማግሌዎችንና የአመራር ብቃትን አስመልክቶ የሚነሱ ጥያቄዎችን ሁልጊዜ ስናድበሰብሳቸው ይታያል። ነገሩን እንደሚገባ ማጤን ሲገባን ከነገሩም ስንሸሽ ይስተዋላል። ይህን የምናደርገው ግን መፍትሄ እየመሰለን ነው። በሌላ አነጋገር ለችግሩ የምንሰጠው መፍትሄ ትክክለኛውን መንገድ የተከተለ ባለመሆኑ ችግሩ ሁልጊዜ ሲያስጨንቀን ይኖራል።

የዚህ መጽሐፍ ሌላው ዓላማ ችግር ለሆነብን ነገር የተሻለ መፍትሄ መጠቆም ይሆናል። መጽሐፉ እነዚህን ዓላማዎች መሠረት በማድረግ የተጻፈና ለሚያነሳቸውም ጉዳዮች ሁሉ ሥነ-መለኮታዊ አስተያየት የሚሰጥ ነው። ይህ መጽሐፍ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት።

የመጀመሪያው ክፍል፥ አንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ስለሚኖራት ተግባርና ተልዕኮ እንዲሁም ስለ ቤተክርስቲያን መመሪያ ያወሳል። ቤተክርስቲያን ግብ ያላት ተቋም ናት። ወንጌልን ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ ማዳረስ፥ ሰዎችን ደቀመዛሙርት ማድረግ፥ ድሆችን ማሰብና እግዚአብሔርን ማምለክ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ወደዚህ ግብ ለመድረስ ደግሞ አንድ ብቸኛ መመሪያ አላት፤ ያም መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ



ነው። ክፍሉ በእነዚህና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ ሐሳብ ይሰጠናል።

ሁለተኛው ክፍል፥ አንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ልትከተለው ስለሚገባ መስተዳድራዊ ስልትና በአማኞችና በመሪዎች መካከል ስለሚኖረው የእርስ በርስ ግንኙነት ሐሳብ ይሰጣል።

እስከ ዛሬ ድረስ በሥራ ላይ ከዋሉት መስተዳድራዊ ስልቶች ሁሉ የትኛው የበለጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊነት እንዳለው የምናየው በዚህ ክፍል ነው። የአወቃቀሩ ውስብስብነት በጊዜ ውስጥ ይከረር እንጂ ኤጲስቆጳሳዊ፥ ሽማግሌያዊና ማኅበረ ምዕመናዊ መስተዳድሮች በጉልህ ሲሠራባቸው የቆዩ ናቸው። ከኤጲስቆጳሳውያኑ መስተዳድር በስተቀር የቀሩት ሁለቱ መስተዳድሮች በብዙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት አላቸው። የእነዚህን ሁለት መስተዳድራዊ ስልቶች ጠንካራና ደካማ ጎን ከጠቆመ በኋላ ከሁለቱ መስተዳድራዊ ስልቶች ወስጥ አንዳንድ ሐሳቦችን አጣምሮ የያዘ መስተዳድራዊ ስልት ለማሳየት ይሞክራል።

በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ማንነትን መሠረት ያደረገ የልዩነት መደብ የለም፥ ሊኖርም አይችልም። ይህ ማለት ግን አገልግሎትን መሠረት ያደረገ ልዩነት የለም ማለት አይደለም። ምዕመናን ሽማግሌዎችን የማወቅ፥ የማክበርና የመታዘዝ ኀላፊነት አለባቸው። ምክንያቱም ሽማግሌዎች በመስበክና. በማስተማር፥ በመመገብና በማስተዳደር እንዲሁም በመጠበቅና በማስማራት ዘወትር ይጋደላሉ፥ ደግሞም ይደክማሉ። ይህ መንፈሳዊ ተጋድሎ ደግሞ እውቅናን፥ አክብሮትንና ታዛዥነትን ይሻል። ይህ አግድማዊ ግንኙነት ማንነትን ሳይሆን አገልግሎትን ነው መሠረት ያደረገው። የእርስ በእርሱ ግንኙነት በኀላፊነት የተሸረበ ስለመሆኑ በክፍሉ ውስጥ ተብራርቷል። ከዚህ በተጨማሪ ምዕመናን የአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል የመሆን ኀላፊነት (እስከ ግዴታ የሚደርስ ኀላፊነት) እንዳለባቸውም ተገልጿል። በኢትዮጵያ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የበሰለ አመራር ዘወትር

ይገኝ ዘንድ ጽኑ ምኞታችን ነው። በጌታም ፊት የምንማልደው ነገሩ እውን ሆኖ እንዲታይ ነው።

ክብር ለእግዚአብሔር አብ
ለእግዚአብሔር ወልድ
ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡— አንድ አምላክ
ይሁን፤ አሜን።

*አዲስ አበባ 1990*



# ክፍል አንድ

## ቤተክርስቲያንና አመራርዋ

# ምዕራፍ አንድ

# የቤተክርስቲያን ትርጉም፥ ተግባርና ተመርሆ

## 1.1 ትርጉም

ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል "ኤክለሲያ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው:: ይህ ቃል "ኤካሌኦ" ከሚለው ጥምር ቃል ወይም ከሁለት ቃላት የተተረጎመ ሲሆን "ኤክ" ማለት "መውጣት" ማለት ሲሆን "ካሌኦ" ማለት ደግሞ "መጥራት ወይም መሰብሰብ" ማለት ነው ። እንግዲህ "ኤክለሲያ" ማለት "ተጠርተው የወጡ ወይም ተጠርተው የተሰበሰቡ" ማለት ነው[1] :: የዚህን ቃል ሙሉና ትክክለኛ ፍቺ መረዳት እንዲቻል ቃሉ በጥንት ግሪካውያን ዘንድ የነበረውን አጠቃቀም መለስ ብሎ መቃኘት ይጠቅማል::

### 1.1.1 ኤክለሲያ በጥንት ግሪካውያን ዘንድ የነበረው አጠቃቀም

በጥንት ግሪካውያን ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ ኤክለሲያ የሚለው ቃል ሰፊ አጠቃቀም አለው:: አንድ አስቸኳይ ውሳኔ ለመስጠት የተሰበሰበ የአመራር ቡድን ወይም በማኅበራዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ለመስጠት የተሰበሰበ ሕዝብ ኤክለሲያ ተብሎ ይጠራል[2] :: ለጥንቱ ዓለም ኤክለሲያ፥ ማንኛውንም ስብሰባ ወይም ጉባኤ የሚወክል ቃል ነው:: ይህ ቃል ሰፊ አጠቃቀም እንዳለው በአዲስ ኪዳን ላይ በግልፅ ተወስቷል:: ጳውሎስን ለመቃወም በታላቅ ቁጣ የተሰበሰበው የኤፌሶን ከተማ ነዋሪ "ኤክለሲያ" በመባል ተጠርቷል (የሐዋ 19፥32-41):: በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ የሕዝቡን ጉዳይ የሚመረምረው ክፍል ደግሞ "ሕጋዊ ሸንጎ" ወይም "ሕጋዊ ጉባኤ" በመባል እንደሚታወቅ ተጠቅሷል (የሐዋ 19፥39):: እንግዲህ "ኤክለሲያ" የሚለው ቃል ስብሰባ ወይም ጉባኤ የሚወክል ቃል ነው ማለት ነው:: እዚህ ላይ



አንድ መጤን ያለበት መሠረታዊ ነጥብ አለ:: ይኸውም ኤክለሲያ የሚለው ቃል ስብሰባን እንጂ መሰብሰቢያ ቦታን አያመለክትም:: የስብሰባው ዓላማ ምንም ይሁን ምን ስብሰባው እንጂ ቦታው ኤክለሲያ ተብሎ አይጠራም[3]::

### 1.1.2 ኤክለሲያ በሴፕቱዋጀንት ትርጉም ውስጥ ያለው አጠቃቀም

ከባቢሎን ምርኮ በኋላ በየቦታው ተበትነው የነበሩ አይሁዳውያን ከትውልድ ቀዬአቸው ብቻ ሳይሆን ከትውልድ ቋንቋቸውም ብዙ ርቀው ነበር:: በዚህ ምክንያት በአካባቢያቸው በሚነገረው ቋንቋ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የሚያስፈልግ በመሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ብሉይ ኪዳን ከዕብራይስጥ ቋንቋ ወደ ግሪክ ቋንቋ በ280 ዓ.ዓ. ላይ በግብፅ እስክንድርያ ተተረጎመ:: ይህ ትርጉም ከኢየሩሳሌም በመጡ 70 ሊቃውንት የተሠራ በመሆኑ ሴፕቱዋጀንት ወይም LXX የሚል ስያሜ ተሰጠው (በላቲን ቋንቋ ሴፕቱዋጀንት ማለት 70 ማለት ነው)::

በሴፕቱዋጀንት ትርጉም ውስጥ "ኤክለሲያ" የሚለው ቃል "ቃሃል" ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የተተረጎመ ነው:: በዚህ ትርጉም ውስጥ ይህ ቃል 100 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን በቁሙ "ጉባኤ ወይም ሕዝባዊ ስብሰባ" ማለት ነው:: የክፉዎች ጉባኤ (ዘፍ 49፥6፤ መዝ 26፥5)፥ ሕዝባዊ ጉባኤ (1ኛነገ 12፥3፤ምሳ 5፥14)፥ የጦረኞች ስብሰባ (ዘኁ 22፥4፤ መሳ 20፥2)፥ ወይም እግዚአብሔርን ለማምለክና ቃሉንም ለማድመጥ የተሰበሰበ ጉባኤ (ዘዳ 9፥10፤ ነህምያ 5፥13) ቃሃል ተብሎ ተጥርቷል[4]:: ቃሃል የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ሰፊ አጠቃቀም ቢኖረውም ሁልጊዜ የሚያመለክተው ግን አንድን ስብሰባ ነው:: በእርግጥ የ"ቃሃል" ተቀዳሚ ፍቺ "ስብሰባ ወይም ጉባኤ" የሚል ነው:: ይሁንና ቃሉ "ተጠርቶ መሰብሰብንም" ያመለክታል:: በሌላ አነጋገር ጥሪ አለ፤ ስብሰባም ደግሞ አለ:: ጥሪውም ሆነ ስብሰባው ገሀዳዊ ይዞታ አለው:: የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ይህን መሠረታዊ እሳቤ ሳይለቁ ኤክለሲያ

የሚለውን ቃል በእንዴት ያለ ይዘት እንደተጠቀሙበት ቀጥለን እንመለከታለን።

### 1.1.3 ኤክለሲያ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው አጠቃቀም

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኤክለሲያ የሚለው ቃል 114 ጊዜ ተጠቅሷል [5]። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልፅ እንደሚታየው ኤክለሲያ በአንድ የተወሰነ ቦታ የሚገኝን ስብስባ የሚያመለክት ቃል ነው። ምክንያቱ በውል የማይታወቅ ጉባኤ ወይም ህልውናው በተጨባጭ ያልተገለጠ ስብሰባ ኤክለሲያ በሚለው እሳቤ ውስጥ ጨርሶ አይገኝም። በሌላ አነጋገር ኤክለሲያ የሚለው ቃል ለአንድ የተወሰነ ዓላማ በአንድ የተወሰነ ቦታ የተሰበሰበ ጉባኤን የሚያመለክት ቃል ነው። ለምሳሌ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ ከጻፋቸው 13 ወይም 14 መልእክቶች ውስጥ ዘጠኝ የሚያህሉት በአንድ የተወሰነ ቦታ ለአንድ የተወሰነ ዓላማ ለተሰበሰቡ አማኞች የተጻፉ ናቸው። ስለሆነም "በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን (ኤክለሲያ)" (2ኛቆሮ 1፥1) እና "ለተሰሎንቄ ሰዎች ቤተክርስቲያን (ኤክለሲያ) "(1ተሰ 1፥1) የሚሉት አነጋገሮች የሚያመለክቱት ኤክለሲያ በውል በሚታወቅ ቦታ የሚገኙ ስብሰባዎችን የሚገልጽ ቃል መሆኑን ነው።

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች አስፈላጊ ጉዳዮችን ለመግለጽ ካልሆነ በቀር ኤክለሲያ የሚለውን ቃል አልተጠቀሙበትም። ቃሉ አምስት ጊዜ በአጠቃላይ አገባቡ የተጠቀሰ ሲሆን (የሐዋ 19፥32፤ 39፥41፤ 7፥38 ዕብ 2፥12) ሌሎቹ 109 አጠቃቀሞች ደግሞ ከአጥቢያ ቤተክርስትያን ህልውና ጋር የተገናኙ ናቸው። እንግዲህ በአዲስ ኪዳን አጠቃቀም መሠረት "ኤክለሲያ" ማለት ለአንድ የተወሰነ ዓላማ በአንድ የተወሰነ ቦታ የሚገኝ የአማኞች ጉባኤ ወይም ስብሰባ ማለት ነው። ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ያለበት ዓይነተኛ ችግር የአማኞችን ስብሰባ ብቻ ሳይሆን አማኞቹ የተሰበሰቡበትንም ቦታ (ሕንፃ) የሚያካትት መሆኑ ነው። ቤተክርስቲያን ሲባል ፈጥኖ የሚታሰበን ህንጻው ነው። እርግጥ የቃሉም መደበኛ ፍቺ "ክርስቲያኖች የሚሰበሰቡበትና የወንጌልን ስብከት የሚሰሙበት ቦታ" ማለት



ነው። ነገር ግን በቃሉ መደበኛ ትርጉም ውስጥ "የምዕመናን ጉባኤ" የሚልም ፍቺ የተካተተ መሆኑን የአማርኛ ቋንቋ ሊቃውንት ያስገነዝቡናል። ለምሳሌ "ቤተሰብ" ስንል "ያንድ ቤት ሰዎች ወይም ያንድ ቤት ትውልድ" ማለታችን ነው። "ቤተ እስራኤል" ስንል ደግሞ "የእስራኤል ሰዎች" ወይም "የእስራኤል ሕዝቦች" ማለታችን ነው። ቤተክርስቲያን የሚለውም ቃል ልክ እንዲሁ ነው። ቃሉ አንድ ጊዜ "ምዕመናን የሚሰበሰቡበትን ቦታ" ሌላ ጊዜ ደግሞ "የምዕመናንን ጉባኤ" ይወክላል። ባጠቃላይ ቃሉ ሁለት መደበኛ ፍቺዎች አሉት ማለት ነው። ኤክለሲያ ግን ምዕመናንንና መሰብሰቢያውን አጣምሮ የያዘ ቃል አይደለም። ቃሉ ሁልጊዜ የሚያሳየው የአማኞችን ስብሰባ ወይም ጉባኤ ነው። ተሰብሳቢ አማኞች ከሌሉ ኤክለሲያ የለም።

## 1.2 የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ተግባር

ቀደም ባለው ምዕራፍ ላይ ቤተክርስቲያን (ኤክለሲያ) ማለት ለአንድ የተወሰነ ዓላማ በአንድ የተወሰነ ቦታ የሚገኝ የአማኞች ጉባኤ ወይም ስብሰባ ማለት እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የአጥቢያ ቤተክርስትያን ዓላማ ምን እንደሆነ እናያለን።

ቤተክርስቲያን ግብና ዓላማ የለሽ ተቋም አይደለችም። ወይም ደግሞ ስለምን ጉዳይ እንደተሰበሰቡ እንደማያውቁት እንደ ጥንት የኤፌሶን ከተማ ነዋሪዎች ዓይነትም አይደለችም (ሐዋ 19፥32)። ይልቁንም መለኮታዊ ተግባርና ተልዕኮ ያላት መንፈሳዊ ተቋም ናት። የቤተክርስቲያንን ተቀዳሚ ተልዕኮ አስመልክቶ አያሌ አስተያየት ቢኖርም ወንጌልን ለዓለም ሕዝቦች ማዳረስ፥ ምዕመናንን በጌታ ቃል ማሳደግ፥ ልዑል እግዚአብሔርን ማምለክና ችግረኞችን ማሰብ ዋና ዋናዎቹ የቤተክርስትያን ተግባራት ናቸው።

ከቤተክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው፥ በአንድ ወቅት ትልቅ ትኩረት አግኝቶ የነበረው ጉዳይ በሌላ ወቅት ተዘንግቶ ወይም እስከ ወዲያኛው ተረስቶ ይታያል። ለምሳሌ፥

ቤተክርስቲያን በተመሠረተችበት በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት (30-100 ዓ.ም) እግዚአብሔርን ማምለክ፥ ወንጌልን ማዳረስና ምዕመናንን ማሳደግ አበይት የቤተክርስትያን ተግባራት ነበሩ:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለጌታ ሥራ ተልከ በሄደባቸው ቦታዎች ሁሉ እግዚአብሔር መመለክ የሚገባው አምላክ መሆኑን ሲያሳውቅ (ቆላ 1፥12-13)፥ ምዕመናንን በጌታ ቃል ሲያሳድግና (የሐዋ 18፥11)፥ ችግረኞችን ወይም ድሆችን ማሰብ አስፈላጊ መሆኑን ሲመክርና (ገላ 2፥10) ወንጌል ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ መሰበክ ያለበት መሆኑን ሲያሳስብ ነበር (2ጢሞ 4፥2):: በሐዋርያት ተልዕኮ ውስጥ አራቱ ተግባራት ጉልህ ቦታ ነበራቸው::

በመካከለኛው ክፍለ ዘመን (1000-1500 ዓ.ም) ወንጌልን መሰበክ ሙሉ በሙሉ ተዘንግቶ ነበር:: ገዳማዊ ሕይወትን ማስፋፋትና ራስን ከዓለም ሁኔታዎች ሁሉ ማላቀቅ ቅዱስ ተግባር ተደርጎ በሚታይበት ሰዓት "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" (ማር 16፥15) የሚለው የጌታ ቋሚ ትእዛዝ ከቤተክርስቲያን ሕይወት ተፍቆ ነበር:: በዚህ ወቅት የነበሩ ክርስቲያኖች ከዓለም አካባቢያዊና ማኅበራዊ ሕይወት ተነጥለው ስለነበር ዕለታዊ ተግባራቸው መንፈሳዊ ተረቶችን መፍጠር ብቻ ነበር:: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምሁራን እንደሚያስገነዝቡን፥ አያሌ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ትምህርቶችና ልምምዶች ቤተክርስቲያን ውስጥ ስርገው የገቡት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው:: ቅዱሳን መላእክትን እንዲሁም ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኛ ዋነኛ መንገድ አድርጎ መቁጠር የተጀመረውም በዚህ ወቅት ነው::

ከ18ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ፥ አሁን እስካለንበት ዘመን አጋማሽ ድረስ ወንጌልን መስበክ ከፍተኛ ቦታ የተሰጠው ተግባር ነው:: በርካታ የአፍሪካ፥ የእስያና የላቲን አሜሪካ ሀገሮች ትክክለኛውን የወንጌል መልእክት ማግኘት የቻሉት "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ" የሚለው የጌታ ቃል፥ መለኮታዊ ትእዛዝ መሆኑን የተረዱ የአውሮፓና የአሜሪካን ሚሲዮናውያን ባደረጉት ታላቅ ተጋደሎ ነው:: ከአውሮፓ ዊሊያም ኬሪ፥



ከአሜሪካን ደግሞ ሄድሰን ቴይለር መቼም የማይረሱ የ18ኛው ክፍለ ዘመን ወንጌል ሰባኪያን ናቸው::

ይሁንና ምዕመናንን በጌታ ቃል ማሳደግና ጠንካራ ደቀ መዛሙርት ማድረግ የቀረና የተተወ ተልዕኮ ሆኗል:: ለምሳሌ ከጠቅላላው የአሜሪካን ሕዝብ ውስጥ 80% የሚሆኑት የክርስትና እምነት ተከታይ መሆናቸው ሲነገር ከዚህ ውስጥ 49% የሚሆኑት "የተራራውን ስብከት" (ማቴ 5-7) ማን እንደሰበከው አያውቁም:: ይህ የሚያሳየው ምዕመናንን ደቀ መዛሙርት ማድረግ ጊዜው ያለፈበት የጥንት ክርስቲያኖች ተልዕኮ ብቻ ተደርጎ መቆጠሩን ነው:: ምዕመናንን በጌታ ቃል ማሳደግና አካባቢያዊ አመለካከት የማይነቀንቃቸው ጽኑ አማኞች ማድረግ በቀረበት በዚህ ዘመን አያሌ ምዕመናን የሚያምኑትን ጌታ ለምን እንደሚያምኑት ወይም የሚከተሉትን ጌታ ለምን እንደሚከተሉት በትክክል መናገር አልፎም ምክንያት መስጠት አይችሉም:: ይህ አባባል ግብታዊና ጭፍን አባባል ሊመስል ይችላል:: ሆኖም ስታትስቲካዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በጣም ታዋቂ የስህተት ክፍሎች (ኑፋቄያን) አዳዲስ አባሎችን ወደ እነርሱ እምነት የሚያፈልሱት ከፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች እየዘረፉ ነው:: ነገሩ ምን ያህል እርግጥ እንደሆነ ለማሳየት ሁለት አብነቶችን ብቻ እንጠቅሳለን::

በአሁኑ ጊዜ የሞርሞንስ እምነት ተከታዮች ብዛት ወደ 9 ሚሊዮን ይጠጋል:: ከዚህ ውስጥ ዋና የሚሆኑት በአንድ ወቅት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የነበሩ ናቸው [6]:: በሌላ በኩል ደግሞ የይሆዋ ምስክሮች (Jehovah's Witnesses) ኢትዮጵያን ጨምሮ በ231 አገሮች 11,865,000 ያህል አባላት ያላቸው ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ቀድሞ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ነበሩ [7]:: እነዚህ ሁለት የኑፋቄ ቡድኖች የክርስቶስ ኢየሱስን አምላክነት ከመካዳቸውም በላይ የሥላሴ አስተምህሮ "የክርስቲያኖች ተረት-ተረት ነው" የሚሉ ናቸው::

እንግዲህ ይህ ሁኔታ የሚያስገነዝበን፥ በርካታ ክርስቲያኖች የሚያምኑትን ነገር ለምን እንደሚያምኑት ምክንያታዊ መልስ መስጠት የማይችሉ መሆናቸውን ነው:: ቤተክርስቲያን ዋነኛ ወይም ተቀዳሚ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ የምታካሂዳቸውን ዘመቻ አቁማ ወደ አቢዩ ተልዕኮዋ እንድትመለስ ትሁት ጥሪ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያመንበት በወቅቱ ከሚታየው እውነታ በመነሣት ነው:: እርግጥ ነው ይህ ያለንበት ዘመን ከፍተኛ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ የሚታይበት ዘመን ነው:: ይሁን እንጂ ለቤተክርስቲያን የተሰጣት ተልዕኮ ዘመን በተለወጠ ቁጥር አብሮ ያሚለወጥ ወይም አመለካከቶች በተሻሻሉ ቁጥር አብሮ የሚሻሻል አይደለም:: "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው..." (ማቴ 28፥19) የሚለው የጌታ ትእዛዝ ጊዜም ሆነ ዘመናዊነት (Modernism) የማይሽረው ቃል ነው:: ጌታ "ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" ሲል በነገር ሁሉ የበሰሉ ክርስቲያኖች አድርጓቸው ማለቱ ነው:: ይህ ዘመን በጌታ ነገር መብሰልን የሚጠይቅ ዘመን ነው:: ምክንያቱም በነገር ሁሉ ዘመናዊ መሆን የወቅቱ መሪ ሐሳብ ነው:: ቤተክርስቲያን ግን "ከዘመናዊነት ፈሊጥ" ጋር ምንም ኅብረት የላትም:: ይልቁንም ዘመናዊ በሆነ ዓለም ውስጥ ዘመን በማይሽረው የጌታ ቃል መሠረት የምትኖር ናት:: ይህን ጉዳይ በተከታዩ ክፍል የምንመለከተው ይሆናል::

## 1.3 የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ተመርሆ

ነገሮች ሁሉ መለኪያ አላቸው:: በሌላ አነጋገር ከመለኪያ ወይም ከመመሪያ ውጪ የሆነ ነገር የለም:: ለምሳሌ ርቀትን በሜትር፥ ክብደትን በኪሎ ግራም፥ ሙቀትን ደግሞ በቴርሞ ሜትር መለካት ይቻላል::

ልክ እንዲሁ መንፈሳዊ ነገርም መለኪያ ወይም መመሪያ አለው:: ክርስትና መንገዱ እንደጠፋበት ሰው "ትክክለኛው መንገድ የቱ ነው?" በማለት ያገኘውን ሁሉ



የሚጠይቅ እምነት አይደለም:: እግዚአብሔር ውሉ የጠፋበት ሰው እንድንሆንና በመንገድ ፍለጋ ዝንተ ዓለማችንን እንድንባዝን ከቶ አልተወንም:: ነገር ግን በትክክለኛው መንገድ ላይ መጓዝ እንድንችል ለመንገዳችን ብርሃን ሰጥቶናል:: ያም ብርሃን መጽሐፍ ቅዱስ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ የምንጓዝበትን መንገድ በትክክል የሚያሳየን መለኮታዊ ብርሃንና የመንገዳችንንም ትክክለኛነት የምንመዝንበት መለኮታዊ መለኪያ ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ወጣቱን ጢሞቴዎስን ሲመክር፡- "የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ፥ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል" (2ኛ ጢሞ 3፥16) ብሏል:: መጽሐፍ ቅዱስ ለአስተምህሮ ማለትም እውነትን ለማስተማርና ስህተትን ለማረም ይጠቅማል፤ እንዲሁም ለሥነ-ምግባር ማለትም የተሳሳቱትን ለመገሰጽና ሕይወትን ለማግኘት ይበጃል:: ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ለመንፈሳዊ ነገር ብቸኛ መመሪያ መሆኑን ያስገነዝበናል::

ዛሬ አያሌ አብያተ ክርስቲያናት ከፍተኛ መንፈሳዊ ቀውስ የገጠማቸው መጽሐፍ ቅዱስን ብቸኛ የእምነትና የተግባር መለኪያ ካለማድረጋቸው የተነሣ ነው:: ከዛሬ 500 ዓመታት በፊት "ብቸኛ የሆነ የእምነትና የተግባር መለኪያ የለም" የሚለው አመለካከት ትልቁ የቤተክርስቲያን ችግር ነበር:: ከዚህ የተነሳ በርካታ ሰዎች ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንኳ በትክክል አያውቁም ነበር:: ይህ ታሪክ ከተፈጸመባቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ ማርቲን ሉተር ነው (1483-1575):: አንድ ጊዜ በቤተክርስቲያን ወግ ሌላ ጊዜ ደግሞ በቤተክርስቲያን ጳጳሳት አስተሳሰብ ከወዲያ ወዲህ ሲዋከብ ከቆየ በኋላ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት የመዳንን መንገድ አገኘ:: ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው ማርቲን ሉተር "መጽሐፍ ቅዱስ የእምነት ብቸኛ መመሪያ ነው" (Sola Scriptura) በማለት ጽኑ አቋም የወሰደው [8]:: በአሁኑ ጊዜ የሚታየው ሁኔታ ከዚህ ብዙ ያልራቀና ክርስትናን ክፉኛ ሊጎዳ የሚችል አዝማሚያ ነው:: "መጽሐፍ ቅዱስ ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ትርጉም የሚሰጥ በመሆኑ መተርጎምም ያለበት እንደ

ሰዎቹ መረዳት ነው" የሚል አስተያየት በሰፊው እየናኘ ነው:: በሌላ አነጋገር የመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ "በአንባቢው እንጂ በጸሐፊው ትርጉሙ አይወሰንም" በሚለው አመለካከት ተወረናል:: (በዚህ አገባቡ "አንባቢው" ሲባል የቅዱሳት መጻሕፍት አንባቢ ማለት ሲሆን "ጸሐፊው" ሲባል ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን የጻፉት ሰዎች ማለት ነው)::

ይህ አመለካከት በቤተክርስቲያን ውስጥ ስር መስደድ የጀመረው ካለፉት 50 ዓመታት ወዲህ ነው:: በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ጥናት ያደረጉ የሥነ-መለኮት ምሁራን እንደሚያስገነዝቡት ከሆነ "መጽሐፍ ቅዱስ የእምነትና የተግባር ብቸኛ መመሪያ አይደለም" የሚለው አመለካከት ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ (New age movement) ጋር ጥብቅ ዝምድና አለው:: የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አስተሳሰብ የተመሠረተው "መጽሐፍ ቅዱስ ለእምነትም ሆነ ለተግባር ብቸኛ መመሪያ ወይም መለኪያ አይደለም" በሚለው መርህ ላይ ነው [9]:: የእንቅስቃሴው ዋነኛ ግብ ሃይማኖቶችን ሁሉ አንድ ማድረግ ነው:: እንደ እንቅስቃሴው አራማጆች አባባል ወደዚህ ግብ መድረስ የሚቻለው "አንድ ብቸኛ መመሪያ " የሚለው አቋም ሲወገድ ብቻ ነው:: ይህ ሲሆን ሰዎች ሁሉ በአንድ አስተሳሰብ ስር አንድ ይሆናሉ [10]:: ይህ እንግዲህ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ዋነኛ መርህ ነው::

በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የአዲሱን ዘመን እንቅስቃሴ ትምህርት ማየት በጣም የተለመደ ክስተት ሆኖአል:: ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ ፍጹም አንድነት ሊመጣ የማይችል መሆኑን ስንቶች ተገንዝበን ይሆን? ቤተክርስቲያን ዘወትር ከሚያደክማት የአመለካከት ቅራኔ ተላቃ ለመንፈስ ቅዱስ አሠራር ምቹ መሣሪያ መሆን የምትችለው ለነገሯ ሁሉ መመሪያ ይሆናት ዘንድ የተሰጣትን ቅዱስ መጽሐፍ የእምነቷና የተግባሯ ብቸኛ መለኪያ ስታደርገው ብቻ ነው:: "መንፈስ ይሙላባችሁ" (ኤፌ 5÷18) ያለን ጌታ "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ" (ቆላ 3÷16) ብሎናል:: ሁለቱም (የእግዚአብሔር መንፈስና የእግዚአብሔር ቃል) አብረው የሚሄዱ እንጂ ተነጣጣይ አይደሉም:: በምንም መልኩ ቢሆን አንዱን አጉልቶ ሌላውን ማደብዘዝ አግባብነት የለውም::



የቀድሞዋ ቤተክርስትያን ችግር ቀደም ሲል የጠቀስነው ሁኔታ ነበር:: የአሁኗ ቤተክርስቲያን ችግር ደግሞ የመንፈስ ሥራ በምትለውና በእግዚአብሔር ቃል እውነት መካከል የተጣጣመ አቋም መውሰድ አለመቻሏ ነው:: የቀድሞዎቹን ችግር ስናወሳ የእኛንም ችግር ማውሳትና ከችግሩም የምንወጣበትን መንገድ መተለም ይኖርብናል:: ምንም ችግር እንደሌለ መቁጠር ግን የትክክለኛ የእግዚአብሔር ሰው አቋም አይደለም::

# ምዕራፍ ሁለት

## የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያንና አመራርዋ

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል በኢየሩሳሌም ሆነው እንዲጠባበቁ በጋራ ትእዛዝ ሰጣቸው:: መንፈስ ቅዱስም በላያቸው በወረደ ጊዜ ኃይልን ተቀብለው በኢየሩሳሌም፥ በይሁዳ፥ በሰማሪያ እንዲሁም እስከ ምድር ዳር ድረስ ምስክሮቹ እንደሚሆኑ ነገራቸው:: እነርሱም ይህን መመሪያ በጋራ ተቀብለው በሕብረት በመሆን በጸሎትና ቃሉን በመመርመር ተጠባበቁ:: የተስፋው ቃልም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገ ከአስር ቀን በኋላ ተፈጸመ (ሐዋ 1፥12-20፤ 2፥1-4)::

የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን በበዓለ ኀምሳ ዕለት ተመሠረተች (ሐዋ 2፥14-42):: በዚሁ ቀን ጴጥሮስ ከሌሎቹ አስራ አንድ ደቀመዛሙርት ጋር በመቆም ወንጌልን አወጀ (ቁ 14):: ሰምተውም ልባቸው የተነኩት ጴጥሮስን ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር በአንድነት ቆመው የነበሩትን ሐዋርያት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ጠየቁ (ቁ 37):: መልእክቱንና ምክሩን ተቀብለው ወደ ቤተክርስቲያን የተጨመሩት ሰዎች በሐዋርያት ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በጸሎት ይተጉ ነበር (ቁ 41-42)::

ሂደቱን ስንመለከት የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን አገልጋዮች በጋራ መመሪያ ተቀበሉ፤ በጋራ የተስፋውን ቃል ተጠባበቁ፤ የተባረከውን የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ከተቀበሉ በኋላ በጋራ ለማገልገል ተነሱ:: በተመሠረተችው ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩት ቅዱሳንም በኅብረት ተመላለሱ:: ሉቃስ ሁኔታውን "... በሰው ሁሉ ፍርሃት ሆነ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ:: ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ፤ መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ



ያካፍሉት ነበር:: በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው:: ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር" ይላል (ሐዋ 2፥43-47፤ 4፥32-37):: ምዕመናንም መሬታቸውንና ጥሪታቸውን ሸጠው ሲያመጡ ገንዘባቸውን ያስቀመጡት በጴጥሮስ እግር ሥር ሳይሆን በሕብረት በቆሙት በሐዋርያት እግር ሥር ነበር:: ሐዋርያትም በጋራ በመሆን ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር::

አዲስ በተጀመረችው በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ውስጥ ደቀመዛሙርት በቁጥር እየበዙ ሲሄዱ በማእድ አገልግሎት ዙሪያ ችግር ተፈጥሮ ነበር:: ለዚህም ጉዳይ መፍትሄ ለመስጠት አስራ ሁለቱም ሐዋርያት ሁሉንም ጠርተው "የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማእድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ አይደለም ...በመልካም የተመሰከረላቸውን ... ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን" አሉአቸው:: ከዚህም የሚከተሉትን ዋና ዋና የኅብረት አሠራሮችን እንመለከታለን:: እነዚህም አሥራ ሁለቱም ደቀመዛሙርት በኅብረት መቆማቸው፥ ሁሉንም መጥራታ ቸው፥ ምዕመናን ሁሉ በምርጫ እንዲሳተፉ ማድረጋቸው፥ የሚመረጡትን ከመካከላቸው መሆናቸው፥ የተመረጡትንም ከሐዋርያቱ መካከል አንዱ ብቻ ሳይሆን ሁሉም በጋራ መሾማቸው ነው:: ምንም አንኳ አንድ ሐዋርያ የመሾም ስልጣን ቢኖረውም በዚህ ስፍራ ግን አንድ ሐዋርያ ከሌሎቹ ሐዋርያት ተነጥሎ እንደ ዋና መሪ ብቻውን ሆኖ ሹመቱን ሲያኪያሂድ አንመለከትም:: እንግዲህ በዚህ ቦታ የጋራ አሠራር ጎልቶ እንደሚታይ በቀላሉ ማስተዋል ይቻላል::

ምንም እንኳን ቤተክርስቲያን በበዓለ ኀምሳ ቀን እንደተመሠረተች ወዲያውኑ የዲያቆናትና የሽማግሌዎች አገልግሎት ክፍል ተለይቶ ባናይም በዚያን ወቅት በሐዋርያት ተይዞና ተሸፍኖ የነበረው አገልግሎት ወደኋላ በዲያቆናትና በሽማግሌዎች አገልግሎት ተተክቶ በግልጽ እናያለን:: በዚህ

ጉዳይ ላይ የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ እንዲህ ይላል፡- "አሥራ ሁለቱም ደቀመዛሙርት ሁሉን ጠርተው... የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም:: ... በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ÷ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፤ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን:: ይህም ቃል ሕዝቡን ሁሉ ደስ አሰኛቸው፤... ከጸለዩም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው" (ሐዋ 6÷1-6፤ 11÷30፤ 12÷17፤ 15÷1-22)::

ሽማግሌዎች በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ስላላቸው የአመራር ስፍራና ሚና ከዚህ የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማያሻማ ሁኔታ ያስረዱናል:: በአንጾኪያ በነበሩት አማኞች መካከል ደኅንነትን ለማግኘት በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን ብቻ በቂ አይደለም፤ ከዚህ በተጨማሪ የሙሴን ሕግጋት በተለይም ግርዘትን መፈጸም አስፈላጊ ነው በሚለው ሐሳብ ላይ በተፈጠረው አለመግባባት መፍትሄ ፍለጋ ጳውሎስና በርናባስ ወደ ኢየሩሳሌም ተልከው ነበር (ሐዋ 15÷2):: ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ በአንጾኪያ ስለነበረው አገልግሎታቸው ለሁሉም ሪፖርት አደረጉ (ሐዋ 15÷4):: ሪፖርቱን ካዳመጡት መካከል ከፈሪሳውያን ወገን ያመኑት ተነስተው ግዝረትንና የሙሴን ሕግ እንዲጠብቁ ታዟቸው ዘንድ ይገባል ባሉበት ወቅት ጉዳዩን በቅርብና በጥልቀት ለመወያየትና መፍትሄም ለማግኘት ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ለብቻቸው ተሰበሰቡ:: ተወያይተው ወደ አንድ ሐሳብ ከመጡ በኋላ ከቤተክርስቲያን (ከምዕመናን) ጋር በአንድነት ሆነው የመፍትሄውን መመሪያ ጽፈው በተመረጡት ሰዎች ማለትም በይሁዳና በሲላስ እንዲሁም ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ወደ አንጾኪያ ላኩ (ሐዋ 15÷1-29)::

የወንጌል መልእክት በየቦታው እየተዳረሰ በሄደበት ጊዜ በአብያተ ክርስቲያናት በያሉበት ተመሰረቱ፤ ጳውሎስና በርናባስ በመጀመሪያው የሚሲዮናዊ ጉዞአቸው ወንጌል ሰብከው ደቀመዛሙርትን ካፈሩ በኋላ ቤተክርስቲያንን አቋቁመው የአመራሩን ኀላፊነት ለሾሙአቸው ሽማግሌዎች አደራ



በመስጠት ወደሚቀጥለው ስፍራ ያልፉ ነበር:: ሉቃስ የጳውሎስንና የበርናባስን ልማድ ሲገልጽ፡- "በየቤተክርስቲያኑም ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው በኋላ ጦመውም ከጸለዩ በኋላ ላመኑበት ጌታ አደራ ሰጡአቸው" ይላል (ሐዋ 14÷23):: በተለይ ሐዋርያው ጳውሎስ በሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ለሦስት ዓመት ያህል በኤፌሶን ተቀምጦ በማስተማር አብያተ ክርስቲያናትን ያደራጅ ነበር:: እዚያ የነበረውን ተልእኮ ጨርሶ ለመሄድ በተነሳበት ጊዜ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን ሰብስቦ በሽምግልና አገልግሎት ያለባቸውን የአመራር ኀላፊነት እንደሚገባ እንዲወጡ መመሪያ ሰጣቸው (ሐዋ 20÷17-28)::

የተሰጣቸውን ምክር ይዘት ስንመለከት የራስን ሕይወት የአገልግሎት አካሄድና የተቀበለውን ፈተና የሚገልጥ ነው:: ለምን ይህን የመሰለ ምክር ለመስጠት ተነሣ የሚለውን ጥያቄ ስናነሳው መልሱ እነርሱም የተሰማሩበት የሽማግሌነት አገልግሎት ከፍተኛ ባለአደራነትን የሚጠይቅ በመሆኑ ነበር (ሐዋ 20÷19-27):: በዚህ ቦታ "መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት..." የሚለውን ቃል ስናነብ ሽማግሌዎች የአገልግሎት ኀላፊነታቸውን የሚቀበሉት ከመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ነው (ሐዋ 20÷28):: ጢሞቴዎስ ቤተክርስቲያንን ለማደራጀት በኤፌሶን እንዲቀመጥ ጳውሎስ ሲጠይቀው የሽማግሌዎች መምረጫ መስፈት ሰጥቶት ነበር (1ጢሞ 3÷1-7):: ሽማግሌዎች በመስፈርቱ ተለክተው ቢመረጡም ለአገልግሎቱ በቅዱሳኑ ሆኖ የሚመርጥና የሚሾም ራሱ እግዚአብሔር ነው::

የመምረጥንና የመሾምን አሠራር በተለያዩ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ተገልጾ እናገኛለን:: በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 ስንመለከት ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ጥበብና መንፈስ ቅዱስ የሞላባቸውን አይተውና መዝነው ምዕመናን እንዲመርጡ ኀላፊነትና ሥልጣን እንደነበራቸው እናያለን:: ይህንንም ሲያደርጉ ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ እንዳልሆነና የሚመርጧቸው ሰዎች የተመሠከረላቸው መሆን እንደሚገባቸው እንገነዘባለን:: ምርጫውን ሲያካሂዱ በራሳቸው ብቻ ሳይሆን በእነርሱ ውስጥ አድሮ በሚመራቸው

በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እንደነበረ ማስተዋል ይቻላል፡፡ ምዕመናን እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት ከእግዚአብሔር ጋር የሚሠሩ ናቸውና (ማር 16÷20፤ 1ቆሮ 3÷9፤ 2ቆሮ 6÷1፤ 1ጴጥ 2÷9)፡፡

በዚህ የአገልጋዮች ምርጫ ላይ ምዕመናን ከእግዚአብ ሔር ጋር (የእግዚአብሔር መሣሪያ ሆነው) አገልጋዮችን ሲመርጡና ሐዋርያትም የተመረጡትን ሲሾሙ እናያለን፡፡ በሌላ አባባል በአገልጋዮቹ ውስጥ የተለየ የአገልግሎትን ጸጋ የሚያስቀምጥ እግዚአብሔር ነው፤ በአገልጋዮቹ ውስጥ የተቀመጠውን ጸጋ የመለየቱን ብቃት ደግሞ በምዕመናን ዘንድ አስቀምጦ ወደ ተጠሩበት አገልግሎት እንዲመጡ የሚያደርግ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው፡፡ እዚህ ላይ የምዕመናኑ ድርሻ ለተለየ አገልግሎት የተለየ ጸጋ ያደረባቸውን በእግዚአብሔር ቃል እውነት አስተውሎ መለየት ነው፡፡ በእግዚአብሔር መንፈስ እስከተመሩ ድረስ ይህንን ምዕመናን በእግዚአብሔር መንፈስ እስከተመሩ ድረስ ይህንን መረዳትና ማወቅ ይችላሉ፡፡ እንግዲህ ምርጫ በምዕመናን÷ ሹመት ደግሞ በሐዋርያት እንደነበርና በሁሉም ላይ ግን እግዚአብሔር እንደሠራ እንመለከታለን፡፡ ምዕመናን ሲመርጡ በዘፈቀደ ሳይሆን ለአገልግሎቱ የሚያበቃውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መስፈርት መሠረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡

ሽማግሌዎች በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ አመራር ሰጪዎች ናቸው በቤተክርስቲያን ውስጥ ችግሮች ሲፈጠር አስተዳደራዊ መፍትሄዎችን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በመስጠት ተግባራቸውን ይፈጽማሉ (ሐዋ 15÷28)፡፡ ስለዚህም ነው በሕይወታቸው ከፍተኛው የባሕሪይ ምሳሌነት የሚጠይቅ መስፈርትም የተቀመጠው (1ጢሞ 3÷1-7)፡፡ ሽማግሌዎች በአገልግሎታቸው ጌታ በደሙ የዋጀውን መንጋ በምሳሌነት የመጠበቅ ኀላፊነት እንደሚጠበቅባቸው ተገልጧል፡፡ ለሽማግሌዎች የተሰጠውን የእረኝነት ኀላፊነት ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲገልጽ እንዲህ ይላል:- "... የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ÷ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ



እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን÷፤ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጎብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ" (1ጴጥ 5÷1-5)፡፡

በቤተክርስቲያን አመራር ሰጪዎች ሽማግሌዎች ናቸው (ፊሊ 1÷1)፡፡ በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሽማግሌዎች መንፈሳዊ አገልግሎትን ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ ለታመሙ መጸለይ (ያቆ 5÷14)÷ አገልጋዮችን ለአገልግሎት መለየትና መሾም (1ጢሞ 4÷14፤ 2ጢሞ 1÷6)÷ ቅዱሳን በሕይወታቸው ታንጸው እንዲያድጉ ማስተማርና መስበክ ነው (1ጢሞ 5÷17)፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጥቢያ ቤተክርስቲያን የአመራር መርህ ብዙኅናዊ ወይስ ዋሕዳዊ?

የዚህ ምዕራፍ አቢይ ጉዳይ አንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን መመራት ያለባት በኅብረት ወይስ በአንድ ሰው ነው በሚለው ላይ ነው:: ከዚህ በመቀጠል ለማየት የምንመክረው የብዙኅናዊና የዋሕዳዊ ወይም የኅብረትና የግለሰብ አመራርን መጽሐፍ ቅዱሳዊነት አስመልክቶ ይሆናል::

በአዲስ ኪዳን ውስጥ "የዋሕዳዊ ሽምግልናን" (single eldership) አመራር በግልጽ የሚደግፍ ማስረጃ የለም:: አዲስ ኪዳን የሚናገረው ስለ "ብዙኅናዊ ሽምግልና" (plural eldership) እንጂ "ስለ ዋሕዳዊ ሽምግልና" አይደለም:: እንዲያውም የሽምግልናም ሆነ የዲቁና ሹመት በተሰጠበት ቦታ ሁሉ በግልጽ የሚታየው ዋሕዳዊ ሳይሆን ብዙኅናዊ ሹመት ነው [1]::

ብዙኅናዊ አመራር ሲባል ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች የሚሰጡት የጋራ አመራር ማለት ነው:: ብዙኅናዊ የሚለው ቃል "ብዝኅ" ከሚለው የግዕዝ ቃል የረባ ሲሆን በቁሙ ብዙ÷ ብዛት÷ ብዙነት ማለት ነው:: ይህን ቃል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምንጠቀምበት ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች የሚሰጡትን አመራር ለማመልከት ነው:: ዋሕዳዊ አመራር ሲባል ደግሞ አንድ ሰው ብቻ የሚሰጠው አመራር ማለት ነው:: ይህ ቃል "ዋሕድ" ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም የተስማማ÷ የተዋሐደ÷ ወይም አንድ የሆነ ማለት ነው:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቃሉን የምንጠቀምበት በጥሬው ትርጉም ሳይሆን በውልደተ ቃል (derivation) ትርጉሙ ነው:: በዚህ አገባቡ ዋሕዳዊ ሲባል አንድ ብቻ መሆን ማለት ነው::

ብዙኅናዊ የሽምግልና አመራር የአዲስ ኪዳን መርህ ነው:: "የአንድ ሰው" አመራር ግን በአዲስ ኪዳን የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አመራር ውስጥ ያልተጠቀሰና "የብዙ ሰዎች"



አመራርን ፊት ለፊት የሚቃረን ነው:: ቅዱሳት መጻሕፍት መልሰው መላልሰው የሚያስተምሩን ስለ ብዙኅናዊ ሽምግልና እንጂ ስለ ዋሕዳዊ ሽምግልና አይደለም:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተወሱት አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ሁሉ አንድም ጊዜ በአንድ ሰው ሲመሩ አልታየም:: ብዙኅናዊ ሽምግልና የተለመደው የአዲስ ኪዳን መርህ ወይም አሠራርና ደንብ ነው [2]:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህን ግዕዝ (norm ወይም ደንብ) የጣሰ ከተንቀፈው አምባገነኑ ዲዮጥራጢስ ከተገኘበት አጥቢያ በስተቀር (3ዮሐ 9-10) አንድም አጥቢያ ቤተክርስቲያን አልተጠቀሰም::

አዲስ ኪዳናዊ ንባባት በግልጽ እንደሚያመለክቱት÷ የሽምግልና አገልግሎት የቡድን ወይም የኅብረት አገልግሎት ነው:: "ፕረስቡተሮስ" ወይም "ሽማግሌ" የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ ይኸውም ሐዋርያው ዮሐንስ በ2ኛ እና በ3ኛ ዮሐንስ ላይ "ከእኔ ከሽማግሌው የተላከ መልእክት" (በነጠላ ቁጥር አጠቃቀም) እንዲሁም ሐዋርያው ጴጥሮስ በ1ጴጥ 5÷1 ላይ "እኔ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ ... የሆንሁ" (በነጠላ ቁጥር አጠቃቀም) በማለት ስለራሳቸው ለመናገር ካልሆነ በቀር በአዲስ ኪዳን ውስጥ በነጠላ ቁጥር አጠቃቀም የተጠቀሰበት ጊዜ የለም:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ "ብዙኅናዊ" ሽምግልና እንጂ "ዋሕዳዊ" ሽምግልና በሥራ ላይ ሲውል አልታየም [3]::

እንግዲህ አዲስ ኪዳናዊ ንባባት የሚያስተምሩን ስለ ብዙኅናዊ ሽምግልና አመራር እንጂ "የአንድን ሽማግሌ" ወይም "የአንድን መጋቢ" አመራር አይደለም:: ይህን መርህ መቃረን ማለት የእግዚአብሔርን ሐሳብ መቃረን ማለት ነው:: በአንዳንድ ቦታዎች ላይ እንደሚታየው ጢሞቴዎስን÷ ቲቶን÷ ያዕቆብን (የጌታን ወንድም) ኢጳፍራንና ሌሎችንም ሰዎች እንደ መጋቢ ወይም እንደ ሽማግሌ በመቁጠር "ዋሕዳዊ አመራር" (single leadership or eldership) ነበር የሚሉ አሉ:: እንዲህ የሚሉ ቡድኖች አሉ በማለት ብቻ ነገሩን ማለፍ ተገቢ አይደለም:: በመሆኑም ለነገሩ መነሻ የሆኑትን (የጢሞቴዎስን÷ የቲቶን÷ የያዕቆብን እና የኢጳፍራን) ጉዳዮች አንድ በአንድ በማንሳት ሁኔታውን እንመለከታለን::

የሚያስደፍር አንድም ፍንጭ የለም 6:: ይልቁንም የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን የቡድን ሽማግሌ አመራር (ብዙኀናዊ አመራር) እንደነበራት የሚያስረግጥ ግልጽ ማስረጃ አለ (የሐዋ 15÷ 2):: ያዕቆብ ከሌሎች ሐዋርያት ጋር እንደ "አዕማድ" ከሚታዩት አንዱ ነበር (ገላ 1÷19)::

ኤጳፍራንም የወሰድን እንደሆነ ከዚህ የተለየ ነገር የለውም:: ኤጳፍራን አስመልክቶ የተባሉት ነገሮች ሁሉ የእርሱን ዋሕዳዊ መሪነት (መጋቢነት) ሳይሆን መልእክተኛነት ነው የሚያወሱት:: ይህ ሰው በሁለት የተለያዩ ጳውሎሳዊ መልእክቶች ወስጥ የተጠቀሰ ሲሆን (ቆላ 1÷7፤ 4÷12፤ ፊልሞና 23) በሁለቱም መልእክቶች ላይ የተገለጸው ታማኝ የክርስቶስ አገልጋይነቱ ነው:: ኢጳፍራም የቆላስይስ ቤተክርስቲያን መጋቢ ነበር የሚለውን የአንዳንዶችን አስተያየት የምናረጋግጥበት አንድም ማስረጃ የለም:: ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ከጳውሎስ ጋር ብዙ የደከመና የተጋደለ ቢሆንም በአንድ ወቅት ግን የቆላስይስ ቤተክርስቲያን ብቸኛና ዋሕድ መሪ ነበር ለማለት ፈጽሞ አይቻልም:: ምክንያቱም እንዲህ ለማለት የሚያስችል ምንም መሠረት የለም [7]::

ከላይ የጠቃቀስናቸው ነጥቦች ሁሉ የሚያሳዩን በሐዋርያት ዘመን የነበረው አስተዳደራዊ መርህ ዋሕዳዊ አመራር ሳይሆን ብዙኀናዊ አመራር መሆኑን ነው:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ "ለሚመራችሁ ሰው ታዘዙ" በማለት በነጠላ ቁጥር የተጠቀሰ መመሪያ የለም:: ወጥነቱን ሳይለቅ ሁልጊዜ የተባለው "ለዋኖቻችሁ ወይም ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ" ነው (በብዙ ቁጥር አነጋገር ዕብ 13÷17):: ዋሕዳዊ (የአንድ ሰው ብቻ) የአመራር መርህን መከተል ባዕድ የሚሆነው ቤተክርስቲያን በተመሠረተችበት ዘመን እንዲህ ያለ የአመራር መርህ ፈጽሞ ያልተደገፈ በመሆኑ ነው:: ከዚህ የአመራር መርህ ውጭ÷ የተለየ የአመራር መርህ የነበራት ጤናማ ቤተክርስቲያን ከቶውንም አልነበረችም [8]:: ዋሕዳዊ አመራረ አሉታዊና አምባገናናዊነት በቀላሉ የሚጠናወተው ነው፤ ዲዮጥራጢስን ልብ ይሏል (3ዮሐ 9-10)::



በ3ኛ ዮሐንስ ቁጥር 9-10 ባለው ላይ ዲዮጥራጢስ የተባለው አንድ ሰው የአጥቢያ ቤተክርስቲያንን ብዙኀናዊ አመራር በመቃረን ዋሕዳዊ አመራርን በመፈለግ በአንባገነናዊነት አመራር ቤተክርስቲያንን ለማስተዳደር ሲነሳ እንመለከታለን:: ይህ ሰው ቅንና ትክክለኛ የሆነውን የጽድቅ አገልግሎት የሚሰጡ አገልጋዮችን ስፍራ ሲነፍግና ከቤተክርስቲያንም ሲያስወጣቸው ይታያል:: ሐዋርያው ዮሐንስ የዚህን ሰው አቋምና አመራር አጥብቆ ተቃውሞታል:: ስለነፍሳት የሚተጋ አገልጋይ ስለ ግል ወንበሩ የሚታገል አይደለም፤ ስለ ወንበር መጋደልና አገልግሎት አብረው አይሄዱምና ሐዋርያትም "እኛ ለቃሉና ለጸሎት እንተጋለን" ነው ያሉት:: ለጸሎትና ለቃሉ የሚተጋ አገልጋይ ወንበር ለማሳደድና ለወንበሩ ዘብ ለመቆም ጊዜ የለውም::

ብዙኀናዊ የአመራር መርህ÷ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ የተጠቀሱ አያሌ ጠቀሜታዎችም እንዳሉት እንመለከታለን:: ከዋሕዳዊ አመራር ይልቅ ብዙኀናዊ አመራር ክርስቲያናዊ ወንድማማችነትንና እህትማማችነትን የበለጠ ያጠናክራል:: የዋሕዳዊ አመራር ትልቁ ችግር አመራር ላይ የሌሎች ሰዎችን አስፈላጊነት መካዱ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ አመራር ሁሉ በአንድ ሰው ሥልጣን ስር እንዲማከል በማድረግ የጠያቂና የተጠያቂ ግንኙነቶችን ውል ያሳጣል (አማከለ ማለት ማንኛውንም ነገር ወደ አንድ ማእከል ወሰደ ወይም ሰበሰበ፤ ራሱን የነገሮች ሁሉ ግብና ዒላማ አደረገ ማለት ነው):: የእግዚአብሔርን ሕዝቦች በአመራር ላይ የማያሳትፍ አመራር ሁሉ ጤነኛ አመራር አይደለም::

በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙኀናዊ አመራር ሲጠፋ በገንዘብ ጥቅምና በሥልጣን ለመታለል እንዲሁም ለመሳት እጅግ አመቺ ይሆናል:: የቤተክርስቲያን ታሪክም የሚያስረግጥልን ይሄንኑ እውነታ ነው:: ማንኛውም ሰው እንደሚሳሳት ሁሉ መሪም ይሳሳታል::

ተጠያቂነት በጎደለበት ስፍራ ከአመራር ስህተት የመመለስ ዕድሉ እጅግ የመነመነ ነው:: ስለዚህ ነው

አብዛኛውን ጊዜ ዋሕዳዊ አመራርን የሚያራምዱ መሪዎች የሚስቱትና የሚያስቱት። ከዚህ ሁኔታ ለመጠበቅ ፍቱን መንገድ ተጠያቂነት (መልስ ሰጪነት) ግድ የሚባልበት ነው። ይህን ተጠያቂነት ከዋሕዳዊ አመራር ይልቅ በብዙኀናዊ አመራር ውስጥ ማስፈን መቻሉ አሌ የማይባል ነው። አንዳንዶች በሚመሩት ሕዝብ ዘንድ ተጠያቂነትን ለመከላከል ወይም ከተጠያቂነት ለማምለጥ ተጠያቂነታችን ለእግዚአብሔር ብቻ ነው ይላሉ። ነገር ግን የእነ ጳውሎስን አገልግሎት ስንመለከት በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት ተጠያቂዎች ነን ሲሉ እንሰማቸዋለን (ሐዋ 6፥3፤ 24፥16፤ 2ቆሮ 8፥20-21፤ 1ጢሞ 3፥4-7)። ለምሳሌ ያህል በጋብቻ ሥነ ሥርዓት ላይ ሁለት ተጋቢዎች ቃል ኪዳን ሲጋቡ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ፊት ነው ቃል ኪዳናቸውን የሚፈጽሙት። በአገልግሎታችን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ምስክርነት በየጊዜው ማግኘት አስፈላጊ ነው።

ከዋሕዳዊ አመራር ይልቅ በብዙኀናዊ አመራር ውስጥ ከመሳት የመጠበቁ ዕድል ከፍተኛ ነው፤ የተሻለም ለመሥራት የምክር ጥበብ የበዛበት ነው። የመጽሐፈ መክብብ ጸሐፊ ስለ እርስ በርስ መጠባበቅ ሲናገር፥ "አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል። ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሣዋልና፤ አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሣው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት ... በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም" (4፥9-12)።

ብዙኀናዊ አመራርን እንድንቀበል ግድ የሚለን ሌላው ነጥብ በሥላሴ አካላት መካከል ያለው አንድነትና ሕብረት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምናየው እግዚአብሔር አብ ብቻውን ሲሠራ፥ ብቻውን ሲያድን፥ ብቻውን ሲያስተዳድር አልታየም። ከእግዚአብሔር አሠራር እንደምን ረዳው ኅብረት ትልቅ ቦታ እንዳለው ነው። እግዚአብሔር አብ ሲያቅድ፥ ሲሠራም ሆነ ሲያድን እንዲሁም ሲያስተዳድር ብቻውን አልነበረም (ዘፍ 1፥26፤ 2፥18፤ 11፥6፤ ማቴ 3:16-17፤ ዮሐ 3፥16፤ 16፥5-11፤ 2ቆሮ 13:14)። በዚህ ሁሉ ውስጥ የሥላሴ አካላት ማለትም አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ተሳታፊዎች ነበሩ። በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው አሠራር



እንዲህ ከሆነ በቤተክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ ሊኖር የሚገባው አሠራር ከዚህ የተለየ እንዴት ሊሆን ይገባል?

የሰው ልጆች ትልቁ ችግር ሚዛን መጠበቅ አለመቻላ ችን ነው። አያሌ ታላላቅ ሰዎች የሚጠይቃቸውና "ሀይ የሚላቸው" (ወደ ጥፋት እንዳይሄዱ የሚከለክላቸው) ሰው ባለመኖሩ አስከፊ ውድቀት ውስጥ ሲገቡ ታይተዋል። ራስን ከተጠያቂነት የሚያርቅ አመራር መፍጠር ማለት ራስን በራስ ለማጥፋት መዘጋጀት ማለት ነው። ማንም አይድረስብን የሚል የአመራር ስፍራ ራሳቸውን የሚያስቀምጡ መሪዎች እጅግ ምስኪን ሰዎች ናቸው። ምክንያቱም ስህተታቸውን የሚያሳያ ቸውና የሚመክራቸው ሆነ ፊት ለፊት የሚወቅሳቸው እውነተኛ ወዳጅ አይኖራቸውም። ራስን የሁሉ የበላይ ለማድረግ መሞከር ትልቅ በደል ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ሰው የሆነ አንድ መሪ ይሁን ከተባለ ሥጋ የሆነው ቃል፥ ይኸውም የቤተክርስቲያን መሠረትና ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ከዚህ መለስ ግን በቤተክርስቲያን ውስጥ ሊኖር የሚገባውና የተደነገገውም ብዙኀናዊ አመራር ነው።

እንደ አዲስ ኪዳን አስተያየት በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሊኖር የሚገባው የአመራር መርህ ብዙኀናዊነትን የተከተለ መሆን አለበት። ምክንያቱም አጥቢያ ቤተክርስቲያንን መምራት "ለአንድ ባለሙያና ሃይማኖታዊ መሪ ብቻ" የተሰጠ ኀላፊነት አይደለም። ከጳውሎስ መልእክቶች እንደምንረዳው በአንድ ሰው ዙሪያ ያማከለ ጤነኛ የቤተክርስቲያን አመራር ከቶ አልነበረም። ጳውሎስ ለፊልጵ ስዩስ ቤተክርስቲያን ሲጽፍ "የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያዎች የሆኑ ጳውሎስና ጢሞቴዎስ በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ ከኤጲስቆጶሳትና ከዲያቆናት ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ ... ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን" (ፊል 1፥11) ያለውን መጥቀሱ በቂ ነው። ሐዋርያው የፊልጵስዩስን "ኤጲስቆጶሳትና ዲያቆናት" ለይቶ የጠቀሰው ከሌላው የተለየ ቦታ ሊሰጣቸው ፈልጎ ሳይሆን ለፊልጵስዩስ ቅዱሳን ሰላምታ ሲያቀርብ እነርሱም መታለፍ ስለሌለባቸው ነው።

እርግጥ ነው ምዕመናን አስፈላጊ እንደሆኑ ሁሉ መሪዎችም አስፈላጊ ናቸው:: ይሁን እንጂ የቤተክርስቲያን መሪዎች የሚገኙት ከምዕመናን (ከቅዱሳን) መካከል ነው:: ጳውሎስ በምዕመናንና በመሪዎች (በኤጲስቆጶሳትና በዲያቆናት) መካከል ድንበር አላካለለም:: ይልቁንም በሁለቱ መካከል ያለውን ቅርብ ዝምድናና አንድነት "... ከኤጲስቆጶሳትና ከዲያቆናት ጋር... ቅዱሳን ሁሉ ..." በማለት ገልጾታል:: በሌላ ስፍራ ደግሞ ጴጥሮስ ቅዱሳን ሁሉ "የንጉሥ ካህናት" እንደሆኑ ይገልጻል (1ጴጥ 2÷9):: የጳውሎስ ዋና አትኩሮትም እዚሁ አንድነታቸው ላይ ነው:: ምክንያቱም በቤተክርስቲያን ውስጥ ከዚያና ከዚህ መለስ የሚል ልዩነት የለምና [9]:: በአንድ በኩል እረኞችና በጎች ተብሎ የእረኞች ኀላፊነት ቢገለጥም እረኞች ራሳቸውም እኰ በጎች ናቸው:: እንግዲህ እረኞች በመባላቸው ኀላፊነትን እንጂ የምንነት ልዩነትን አያመለክትም::

በዮሐንስ ራእይ ላይ የተጠቀሱት የሰባቱ ቤተክርስቲያን መላእክት የሚለውን እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን በአንድ ሽማግሌ እንደሚመራ አድርጎ የመተርጎም አዝማሚያ አለ:: ይሁን እንጂ ይህ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ለምሳሌ "ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን መልአክ" (ራእይ 2÷1) የሚለው ሐረግ በኤፌሶን ቤተክርስቲያን ውስጥ አንድ ሽማግሌ ብቻ መኖሩን የሚያመለክት ሐረግ አይደለም:: ምክንያቱም ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፉ ላይ እንደገለጸው የኤፌሶን ቤተክርስቲያን በርካታ ሽማግሌዎች ነበሯትና (የሐዋ 20÷17)::

በተመሳሳይ ሁኔታ ሐዋርያው ጴጥሮስም "በመካከላችሁ ያሉትን የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ:: በአደራ የተሰጣችሁን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ" (1ጴጥ 5÷1-2) በማለት የብዙ ሽማግሌዎችን አመራር በግልጽ ጽፏል::

እውቁ እረኛና የሥነ መለኮት ሰው የሆኑት እንግሊዛዊው ጆን ስቶት የአንድን እረኛ ተግባርና ዓላማ ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ ግሩም አድርገው አብራርተውታል:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ እረኞች ያለው እሳቤ (ግንዛቤ) አገልግሎቶችን ሁሉ በመዳፉ ስር የሚጨመድድ ወይም



የሌሎችን የአገልግሎት ጥሪዎች ሁሉ የሚያኮላሽ አይደለም:: ይልቁንም የእግዚአብሔር ሕዝቦች የተሰጣቸውን ስጦታ ለይተው እንዲ ያውቁት÷ እንዲያሳድጉትና እንዲጠቀሙበት የሚያበረታታ ነው:: አንድ እረኛ የሚያስተምረው ትምህርት ሁሉ ዓላማ ማድረግ ያለበት የእግዚአብሔር ሕዝቦች አገልጋይ እንዲሆኑ መርዳት ላይ ነው:: እረኛ አገልግሎቶችን ሁሉ እርሱ ብቻ (በሞኖፖል) ጨምድዶ ከመያዝ ይልቅ አገልግሎቶችን የሚያበዛ÷ የሚያባዛና የሚያበረክት መሆን አለበት [10]::

ታዲያ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን አገልግሎት በምን እንመስለው? ለረጅም ዘመን ሲሠራበት የቆየው ምሳሌ (ተምሳሌት) ፒራሚድ ነው:: በሌላ አነጋገር በቤተክርስቲያን ውስጥ አንድ አገልጋይ አለ፤ ሌሎች ተመልካቾች ናቸው:: ይህን የፒራሚድ ምሳሌ በአንድ የከተማ አውቶቡስ ልንተካው እንችላለን:: እረኛው እንደ ሹፌር ሲሆን ምዕመናን ደግሞ እንደ መንገደኞች (ተጓዦች) ናቸው:: ይህ አሠራር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን የመሰለው "በአካል" ነው:: በአንድ አካል ላይ ያሉ የአካሉ ብልቶች (ክፍሎች) ሁሉ የሥራ ድርሻ አላቸው:: በአካል ላይ "ተመልካች" የሆነ አንድም ብልት ወይም የአካል ክፍል የለም:: ይህ ተምሳሌት አገልግሎትን ሁሉ በአንድ ሰው ዙሪያ ማማከልን በጽኑ የሚቃረን ነው:: አዲስ ኪዳን የሚያጸናልን አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች (ካህናት) እንደሆኑ ነው (1ጴጥ 2÷9) [11]::

እስከ አሁን ከቀረበው ገለጻ እንደምንረዳው በየትኛውም የአዲስ ኪዳን ክፍል ውስጥ የአንድ ወይም የነጠላ ሽማግሌን አመራር የሚደግፍ ማስረጃ የለም:: ከዚህ በተቃራኒው የብዙ ሽማግሌዎች አመራር "በየቤተክርስቲያኑ" (የሐዋ 14÷23፤ ቲቶ 1÷5) እንደነበር የሚያረጋግጥ ግልጽና በማያሻማ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ነው:: ሁለተኛው÷ በአዲስ ኪዳን ውስጥ መንፈሳዊ አመራርና ትምህርት የሚሰጡ ሽማግሌዎች የሌሏት ቤተክርስቲያን አልነበረችም (የሐዋ 20÷28፤ ዕብ 13÷17፤ 1ጴጥ 5÷2-3)::

ኤጲስቆጶስ" ማለት ነው:: ይህም በሽማግሌና በእረኛ መካከል የስም ወይም የመጠሪያ ልዩነት እንጂ የተግባርና የኀላፊነት ልዩነት የሌለ መሆኑን በሚገባ ያሳያል::

የሽማግሌዎችን ኀላፊነት ለማመልከት በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰው ሌላው መጠሪያ "ኤጴስቆጶስ" የሚለው ቃል ነው:: በአማርኛው ትርጉም ላይ "ኤፒስኮፖስ" የሚለው የግሪክ ቃል አንድ ጊዜ "ጳጳስ" ሌላ ጊዜ ደግሞ "ኤጲስቆጶስ" ተብሎ ተተርጉሟል:: ጳውሎስ የኤፌሶንን ሽማግሌዎች ካስጠራ በኋላ እንዲህ በማለት ሐዋርያዊ ምክሩን ሰጥቷል፡- "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት (በግሪክ "ኤፒስኮፖስ") አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" (የሐዋ 20፥28):: ሐዋርያው እነዚህን ሽማግሌዎች "ኤጲስቆጶስ" በማለት የጠራበት ምክንያት አለው:: ይኸውም አንደኛው የሽማግሌዎች ተግባር ምዕመናንን መጠበቅ ነው:: በግሪክ ቋንቋ "ኤፒስኮፖስ" ማለት "ጠባቂ ወይም ተመልካች" ማለት ነውና [3]::

በ1ጢሞ 3፥1-2 ላይ ጳውሎስ ሲጽፍ "ማንም ኤጲስቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል. የሚለው ቃል የታመነ ነው:: እንግዲህ ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባል" ብሏል:: እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን፥ ጳውሎስ ይህንን መልእክት ለጢሞቴዎስ የጻፈው ጢሞቴዎስ በኤፌሶን ሳለ መሆኑን ነው (1ጢሞ 1፥3 "በኤፌሶን ትቀመጥ ዘንድ ለመንሁህ"):: ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 20 እንደምንረዳው ደግሞ፥ በኤፌሶን ሽማግሌዎች ነበሩ :: እንግዲህ "ጳጳስ" ወይም "ኤጴስቆጶስ" የሚለው መጠሪያ "ሽማግሌ" ለሚለው መጠሪያ ተለዋጭ ስያሜ እንጂ ሌላ የተለየ ነገር አይደለም:: ምክንያቱም በጳውሎስም ሆነ በሌሎች መልእክቶች ውስጥ "ሽማግሌዎች" አንድ ጊዜ "ጳጳስ" ወይም "ኤጲስቆጶስ" ሌላ ጊዜ ደግሞ እረኛ (መጋቢ) ተብለው ተጠርተዋል:: በሌላ በኩል "ማንም ኤጲስቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው. . ." ሲል፤ ልናስተውል የሚገባው ቁም ነገር አለ:: ኤጲስቆጶስነት የአገልግሎትና



የሥራ ጉዳይ እንጂ የወንበርና የሥልጣን ጉዳይ አለመሆኑን ነው::

በቲቶ 1፥5 ላይ ጳውሎስ ቲቶን ሲያሳስብ "የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም፥ እኔ አንተን እንዳዘዝሁህ፥ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ" ብሏል:: ማንኛውም ሽማግሌ ከመሾሙ በፊት ሊያሟላቸው የሚገቡ መሠረታዊ መመዘኛዎች እንዳሉ ሲዘረዝር ደግሞ እንዲህ በማለት ጽፏል "ኤጲስ ቆጶስ፥ እንደ እግዚአብሔር መጋቢ፥ የማይነቀፍ ሊሆን ይገባዋል" (ቲቶ 1፥7):: ሐዋርያው በቁጥር 5 እና በቁጥር 6 ላይ "ሽማግሌዎች" ብሎ የጠራቸውን የቤተክርስቲያን እረኞች በቁጥር 7 ላይ "ኤጲስቆጶስ" በማለት ጠርቷቸዋል:: በዚህም ቦታ እንደሚታየው እነዚህ ሁለት የተለያዩ መጠሪያዎች ማለትም "ሽማግሌ" እና "ኤጲስቆጶስ" ሁለት የተለያዩ ሰዎችን ሳይሆን የሚያመለክቱት አንድን ሰው ነው:: ይህ ሁሉ እንግዲህ የስያሜ ወይም የመጠሪያ ተመሳሳይነት እንጂ የትርጉም ወይም የአጠቃቀም ልዩነት አይደለም:: በጥቅሉ የስያሜ ተወራራሽነት ወይም ተለዋዋጭነት ነው ሊባል ይችላል [4]::

በፊልጵስዩስ 1፥1 ላይ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ሲጽፍ "... በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ ከኤጲስቆጶሳትና ከዲያቆናት ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ ... ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን" ብሏል:: ይህ የጳውሎስ አባባል አሁንም "ሽማግሌ" በሚለው መጠሪያና "ኤጲስቆጶስ" በሚለው መጠሪያ መካከል የትርጉም ልዩነት የሌለ መሆኑን አጥርቶ ያሳያል:: ምክንያቱም ጳውሎስ ቤተክርስቲያንን በሚመሠርትበት ቦታ ሁሉ ሽማግሌዎችን የመሾም ልምድ አለውና ነው (የሐዋ 14፥23):: በፊልጵስዩስ ሽማግሌዎች ያሉ ከሆነ ጳውሎስ የኤጲስቆጶስን ቢሮ ከሽማግሌዎች ቢሮ ለይቶ ያየዋል ማለት ፈጽሞ የማይታሰብ ነገር ነው:: ስለሆነም "ኤጲስቆጶሳትና ዲያቆናት" ሲል "ሽማግሌዎችና ዲያቆናት" ማለቱ ነው [5]::

እዚህ ላይ አጠቃላይ አስተያየት መስጠት አስፈላጊ ይሆናል:: ይኸውም፥ ጳውሎስ አንድን የቤተክርስቲያን

ጳውሎስ ስለ ራሱ ሲናገር፡- "ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም፤ እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላችሁ" ብሏል (ሐዋ 20፥33-34)። በሌላም ቦታ አገልግሎቱን በገዛ እጁ እየሠራ እንደሚደግፍ ሲናገር "ወንድሞች ሆይ፥ ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና፤ ከእናንተ በአንዱስ እንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን፥ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን" (1ተሰ 2፥9) ይላል። እንዲሁም ለተሰሎንቄ ሰዎች ለሁለተኛ ጊዜ ሲጽፍ፥ "ከእናንተ ዘንድ በአንዱስ እንኳ እንዳንከብድበት፥ ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ፥ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም። ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ፥ ያለ ሥልጣን ስለሆንን አይደለም" በማለት ተናግሮአል (2ተሰ 3፥8-9)።

ከጳውሎስ ሕይወት እንደምንረዳው ከቤተክርስቲያን ቀለብ የማይሰፈርላቸው ለአገልግሎቱ ራእይና ጥሪ የላቸውም ማለት እንደማይቻል ነው። ጳውሎስ ለራሱ ብቻ ሳይሆን አብረውት ላሉት እንኳ እየሠራ ራእዩ ሳይጠፋበት፥ ቅንአቱ ሳይጎድልበት የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት የተሰጠውን አደራ በብቃት ተወጥቶአል። እንግዲህ እውነታው እንዲህ ከሆነ ሙሉ ጊዜአቸውን የሰጡ ቀለብ ቢሰፈርላቸው አግባብ ነው።

በምዕራቡ ዓለም በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ አገልግሎቶች ሁሉ በአብዛኛው የሚሸፈኑት ገንዘብ እየተከፈ ላቸው በሚሠሩ አገልጋዮች በመሆኑ አገልግሎቶች ሁሉ በተወሰኑ ሰዎች ይያዛሉ። ስለዚህ ቤተክርስቲያን እስከከፈለቻቸው ድረስ ሁሉንም እነርሱ ይሥሩት የሚል አመለካከት አለ። ይህ እንደየአገሩ ያለ ባህል እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው አይደለም። በእኛ አገር ብዙ አገልግሎቶች የሚሸፈኑት የራሳቸውን ሥራ በሚሠሩ ሰዎች ነው። በዚህ ላይ በፈቃደኝነት የሚያገለግሉ በርካታ ሰዎች ስላሉ ቤተክርስቲያን በተወሰኑ አገልጋዮች ብቻ አትያዝም።



የሚያገለግሉ ሰዎች ሁሉ ገንዘብ ይከፈለን ካሉ ስህተት ነው። በአንዳንድ አገሮችና በአንዳንድ ቦታዎች ሁሉም (ሽማግሌዎች) ይከፈለን ስለሚሉም ነው ቤተክርስቲያን በሚከፈለው በአንድ ሽማግሌ (መጋቢ) ወደ መመራት ልማድ የምትገባው ወይም የገባችው።

## 4.3 ተጠሪነትና ተጠያቂነት

እያንዳንዱ አገልጋይ ወይም ሽማግሌ ለሽማግሌዎች ጉባኤ ተጠሪ ነው። እንዲሁም እያንዳንዱ ምዕመን በተለይ በዲሲፕሊን ጉዳይ ለሽማግሌዎች ተጠሪ ነው። የሽማግሌዎች ጉባኤ ለቅዱሳን ጉባኤ የአገልግሎቱን እንቅስቃሴ በተመለከተ ሪፖርት በማድረግ ተጠሪነቱን ይገልጣል፤ ደግሞ እንዲህ ያለው አሠራር ለጤናማ አገልግሎት ፍቱን መንገድ ነው። ምዕመናን በጸሎት፥ በሙያ፥ በጉልበትና በገንዘብ የቤተክርስቲያንን ተልዕኮ የሚደግፉ በመሆናቸው ለእነርሱ ተጠሪ አንሆንም ማለት አግባብ አይደለም። የምዕመናን ሥራ ዝም ብሎ መመራትና መነዳት ብቻ ነው ብሎ መደምደም አማኞች ሁሉ "የንጉሥ ካህናት ናቸው" የሚለውን አዲስ ኪዳናዊ መርህ እንደመቃረን ይቆጠራል። ያላቸውን ነገር ሁሉ በመስጠት የሚያገልግሉ ምዕመናን የቤተክርስቲያኒቷ ሥራ ከየት እንደደረሰ ማወቅ ይገባቸዋል። ይህም ምዕመናን የበለጠ ለአገልግሎት እንዲነሳሱ ያደርጋል።

እንዲህ ዓይነቱ የተጠሪነት ሰንሰለት ማን አለብኝ ባይነትንና ተጠሪነቴ ለእግዚአብሔር ብቻ ነው በሚል ማምለጫ ከተጠያቂነት የመደበቂያ ጎሬን ያስወግዳል። ለእግዚአብሔር ተጠሪ ነኝ የሚል ለእግዚአብሔር ሕዝብ ተጠሪ ነኝ ማለቱ ጤናማነቱ ሊካድና አሌ ሊባል አይችልም። ስለዚህም ነው የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አወቃቀር "ማኅበረ ምዕመናዊ ወሽማግሌያዊ" ቢሆን የሚበጀው።

ሽማግሌ ለማስተማር የሚበቃ መሆን ያለበት ቢሆንም ሽማግሌ ሁሉ ግን በማስተማር አገልግሎት ላይ እኩል ጊዜ ወይም አንድ ዓይነት ጊዜ በመስጠት ይሠማራሉ ማለት

አይደለም:: አንዳንዶች በአስተዳደሩ ብዙ ጊዜ ከመስጠታቸው ይልቅ ለማስተማሩና ለመስበኩ የበለጠ ጊዜ የሚሰጡ እንደሆነ ያስገነዝባል:: ስለዚህ ከሽማግሌዎች መካከል አንዳንዶች ወደ ማስተማሩ ቢያደሉ የአገልግሎቱ ሁኔታ ግድ በማለቱ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል:: የሙሉ ጊዜ መጋቢያንና አስተማሪዎች ወይም ወንጌላውያን ወደ አስተዳደሩ ከሚያዘነብሉ ለቃሉና ለጸሎት ሰፊ ጊዜ በመስጠት የሚተጉ ቢሆኑ የሚበጅ ነው:: በአስተዳደር መጠመዱ ለቃሉና ለጸሎት የሚኖራቸውን ጊዜ ይሻማል:: ሐዋርያትም ራሳቸው የተናገሩት እኛ ግን "ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን" በማለት ነው (ሐዋ 6÷4)::

በ1ጢሞ 5÷17 ላይ እንደምናነበው "በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች፥ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት፥ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል" ይላል:: በዚህ ቦታ "እጥፍ ክብር" የሚለው ሐረግ "ዲፕሌስ ታይሜስ" ከሚለው የግሪክ ሐረግ የተተረጎመ ሲሆን በቁሙ "እጥፍ ደመወዝ" ወይም "እጥፍ አክብሮት" ማለት ነው:: ሐረጉ አንድም ደመወዝን አንድም ደግሞ አክብሮትን የሚያሳይ ሲሆን ሐረጉ ያለበት ዐውደ ንባብ ግን "እጥፍ ደመወዝ" መሆኑን ያሳየናል:: ምክንያቱም በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 18 ላይ "የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር፥ ደግሞ ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል" ይላል:: ይህ ሐሳብ (ማለትም በቁጥር 18 ላይ ያለው) በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሦስት ቦታዎች ላይ የሚገኝ ሲሆን በሦስቱም ቦታዎች ላይ የሐሳቡ አትኩሮት በደመወዝ ወይም በሚገባ ለሚሠራ ሠራተኛ በሚከፈል ክፍያ ላይ ነው (ሉቃ 10÷7፣ 1ቆሮ 9÷9):: ብዙ ጊዜ የሚሰጡ ሽማግሌዎች (እረኞች) በማስተማርና በመስበክ ለዚህም በሚሆን ዝግጅት ሁሉ ለኑሮአቸው የሚሆን ገቢ ለማመቻቸት ጊዜ ስለሚያንሳቸው (ስለሚጠብባቸው) በዚህ አኳያ "እጥፍ ክብር" የሚለው በቂ ክፍያ ሊመደብላቸው ይገባል ማለት ነው::

ይህን የተጠሪነትና የተጠያቂነት እሳቤ ከሌላም አቅጣጫ ማጤን ይቻላል:: እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን አባል ለእግዚአብሔርና ለሌላው አባል ተጠሪና ተጠያቂ ነው:: ይህም



ሌላውን ለማነጽ፥ ሸክሙን ለመጋራት፥ ለመገሠጽ፥ ከክፉ መንገድ ለመመለስና ለመረዳዳት ነው (ገላ 6:2፣ ፊሊ 2:4):: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌላውን ማሰናከል ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል ጉዳይ እንደሆነ ሲገልጽ እያንዳንዱ ለሌላው ተጠሪ መሆኑን ያሳያል:: እግዚአብሔር ቃየልን ወንድምህ አቤል ወዴት ነው? ብሎ ሲጠይቀው ስለ ወንድም መጠየቅ እንዳለ እንረዳለን:: ይህ ተጠያቂነትና ተጠሪነት የሚመለከተው በየትኛውም የሕይወት ደረጃ፥ የእድሜ ክልል፥ የአገልግሎት ኀላፊነት ወይም የጸጋ ስጦታ ያለውን ክርስቲያን ሁሉ ነው:: ምክንያቱም የሌላውን ክርስቲያን አገልግሎት የማይፈልግ ክርስቲያን ሊኖር ስለማይችል ነው:: በዚህ መልኩ ሽማግሌውም ሆነ ዲያቆኑ ወይም ሌላው ምዕመን እያንዳንዱ በአገልግሎቱም ሆነ በአኗኗሩ አንዱ ለሌላው ተጠያቂና ተጠሪ ነው:: ሁሉም ድካም ያለው፥ ጉድለት ያለው ሰው ነው እንጂ ፍጹም የሆነ ፍጥረት አይደለምና:: ሌላውን አልጠይቅም፥ በሌላውም ሰው አልጠየቅም ማለት ከመንፈሳዊነት ጩርሶ የራቀ ሐሳብ ነው::

አይደለም:: አንዳንዶች በአስተዳደሩ ብዙ ጊዜ ከመስጠታቸው ይልቅ ለማስተማሩና ለመስበኩ የበለጠ ጊዜ የሚሰጡ እንደሆነ ያስገነዝባል:: ስለዚህ ከሽማግሌዎች መካከል አንዳንዶች ወደ ማስተማሩ ቢያደሉ የአገልግሎቱ ሁኔታ ግድ በማለቱ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል:: የሙሉ ጊዜ መጋቢያንና አስተማሪዎች ወይም ወንጌላውያን ወደ አስተዳደሩ ከሚያዘነብሉ ለቃሉና ለጸሎት ሰፊ ጊዜ በመስጠት የሚተጉ ቢሆኑ የሚበጅ ነው:: በአስተዳደር መጠመዱ ለቃሉና ለጸሎት የሚኖራቸውን ጊዜ ይሻማል:: ሐዋርያትም ራሳቸው የተናገሩት እኛ ግን "ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን" በማለት ነው (ሐዋ 6፥4)::

በ1ጢሞ 5፥17 ላይ እንደምናነበው "በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች፥ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት፥ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል" ይላል:: በዚህ ቦታ "እጥፍ ክብር" የሚለው ሐረግ "ዲፕሌስ ታይሜስ" ከሚለው የግሪክ ሐረግ የተተረጎመ ሲሆን በቁሙ "እጥፍ ደመወዝ" ወይም "እጥፍ አክብሮት" ማለት ነው:: ሐረጉ አንድም ደመወዝን አንድም ደግሞ አክብሮትን የሚያሳይ ሲሆን ሐረጉ ያለበት ዐውደ ንባብ ግን "እጥፍ ደመወዝ" መሆኑን ያሳየናል:: ምክንያቱም በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 18 ላይ "የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር፥ ደግሞ ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል" ይላል:: ይህ ሐሳብ (ማለትም በቁጥር 18 ላይ ያለው) በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሦስት ቦታዎች ላይ የሚገኝ ሲሆን በሦስቱም ቦታዎች ላይ የሐሳቡ አትኩሮት በደመወዝ ወይም በሚገባ ለሚሠራ ሠራተኛ በሚከፈል ክፍያ ላይ ነው (ሉቃ 10፥7፤ 1ቆሮ 9፥9):: ብዙ ጊዜ የሚሰጡ ሽማግሌዎች (እረኞች) በማስተማርና በመስበክ ለዚህም በሚሆን ዝግጅት ሁሉ ለኑሮኣቸው የሚሆን ገቢ ለማመቻቸት ጊዜ ስለሚያንሳቸው (ስለሚጠብባቸው) በዚህ አኳያ "እጥፍ ክብር" የሚለው በቂ ክፍያ ሊመደብላቸው ይገባል ማለት ነው::

ይህን የተጠሪነትና የተጠያቂነት እሳቤ ከሌላም አቅጣጫ ማጤን ይቻላል:: እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን አባል ለእግዚአብሔርና ለሌላው አባል ተጠሪና ተጠያቂ ነው:: ይህም



ሌላውን ለማነጽ፥ ሸክሙን ለመጋራት፥ ለመገሠጽ፥ ከክፉ መንገድ ለመመለስና ለመረዳዳት ነው (ገላ 6:2፤ ፊሊ 2:4):: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌላውን ማሰናከል ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል ጉዳይ እንደሆነ ሲገልጽ እያንዳንዱ ለሌላው ተጠሪ መሆኑን ያሳያል:: እግዚአብሔር ቃየልን ወንድምህ አቤል ወዴት ነው? ብሎ ሲጠይቀው ስለ ወንድም መጠየቅ እንዳለ እንረዳለን:: ይህ ተጠያቂነትና ተጠሪነት የሚመለከተው በየትኛውም የሕይወት ደረጃ፥ የእድሜ ክልል፥ የአገልግሎት ኀላፊነት ወይም የጸጋ ስጦታ ያለውን ክርስቲያን ሁሉ ነው:: ምክንያቱም የሌላውን ክርስቲያን አገልግሎት የማይፈልግ ክርስቲያን ሊኖር ስለማይችል ነው:: በዚህ መልኩ ሽማግሌውም ሆነ ዲያቆኑ ወይም ሌላው ምዕመን እያንዳንዱ በአገልግሎቱም ሆነ በአኗኗሩ አንዱ ለሌላው ተጠያቂና ተጠሪ ነው:: ሁሉም ድካም ያለው፥ ጉድለት ያለው ሰው ነው እንጂ ፍጹም የሆነ ፍጥረት አይደለምና:: ሌላውን አልጠይቅም፥ በሌላውም ሰው አልጠየቅም ማለት ከመንፈሳዊነት ጨርሶ የራቀ ሐሳብ ነው::

# ምዕራፍ አምስት

## ለቤተክርስቲያን መታነጽ የተሰጡ ስጦታዎች

የአንድን ንባብ ትክክለኛ ፍቺ ለማግኘት ንባቡ የሚገኝበትን ዐውድ በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል:: ቃላት ስሜት ያለው ትርጉም የሚሰጡት ከሌሎች ቃላት ጋር ሲጣመሩና ሲሳኩ ነው:: አንድ ቃል ጠባብና ሰፊ ወይም ነጠላና ድርብርብ ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል:: ነገር ግን አንድ ቃል በአንድ ጊዜ አንድን ትርጉም ወክሎ መቆሙን በእርግጠኛነት መናገር የሚቻለው ከዐውደ ንባቡ ብቻ ነው:: ቃሉ ሌሎች ትርጉሞችን ያላንተተና ያላሳሳበ መሆኑን በትክክል የሚነግረን ቃሉ የተዋደደበት ዐውደንባብ ነው:: ይህን መሠረታዊ መርህ በመያዝ ኤፌ 4÷11ን ለማብራራት እንሞክራለን::

ኤፌ 4÷11 ጠንካራ ንባባት ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ነው:: ንባቡ ስለ ምን ርዕሰ ጉዳይ እንደሚያትት በቀላሉ መናገር ቢቻልም የንባቡን ትርጓሜ ግን እንዲህ በቀላሉ መፍታት አይቻልም:: ምክንያቱም ንባቡ በብቻው የቆመ ሳይሆን ከፊትና (4÷1-10) ከኋላ (4÷12-16) ካሉ ንባቦች ጋር በጥብቅ የተዋደደ ወይም የተጎዳኘ ነው:: ለምሳሌ በቁጥር 8÷9 እና 10 ላይ የተባሉት ነገሮች ስለ ምን ርዕሰ ጉዳይ እንደሚያትቱ በድፍረት መናገር ያዳግታል:: ወደ ላይ የወጣውና ወደ ታች የወረደው ማን ነው? ወደ ላይ የወጣው ወዴት ሄደ? ወደ ታች የወረደውስ ወዴት ነው? ደግሞስ ምንድን ነው የማረከው? ምንስ ነው የሰጠው? ንባቡ የተጠቀሰው ከመዝሙር 68÷ 18 ላይ ነው:: ታዲያ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዐውደ ንባባት ውስጥ (በመዝሙር 68÷1-35 እና በኤፌሶን 4÷1-32) ያለው ፍቺ ምን ያህል ተቀራራቢ ነው? እነዚህን ጥያቄዎች በትክክል መመለስና ነገሩንም ትኩረታችንን ከሳበው ንባብ (ኤፌ 4÷11) ጋር ማዛመድ መቻል የንባቡን ትክክለኛ ፍቺ እንድናገኝ ሊረዳን ይችላል:: ጥያቄዎቹ ጠንቃቃ ሥነ-ሐቲትን (ትንታኔን-



exegesis) ይሻሉ:: ቀጥለን የምናደርገውም ንባቡን (4÷11) በራሱ ዐውደ ንባብ (4÷1-16) ውስጥ ማፍታታት ይሆናል::

ትንተና የምንሰጥበት ክፍል (4÷1-16) በሦስት ንዑሳን ክፍሎች ሊዘረዘር ይችላል::

<u>ኤፌ 4÷1-16</u>
1. 4÷1-6
2. 4÷7-11
3. 4÷12-16

በአዲስ ኪዳን ውስጥ "ሐዋርያ" የሚለው ቃል ሁለት አጠቃቀሞች አሉት:: ይህ ቃል "አፖስቴሎ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ሲሆን ቀዳማይ ፍቺውም "የተላከ" ማለት ነው:: እያንዳንዱ አማኝ "ሐዋርያ" መሆኑን የሚያስገነዝብ ጥቅስ አለ:: ጌታ ኢየሱስ ሲናገር "እውነት እውነት እላችኋለሁ÷ ባርያ ከጌታው አይበልጥም÷ መልክተኛም (አፖስቶሎስ) ከላከው አይበልጥም" (ዮሐ 13÷16) ብሏል:: እንደ ጌታ ኢየሱስ አባባል እያንዳንዱ አማኝ ባርያ (በግሪክ *ዱሎስ አገልጋይ*) እና መልክተኛ (በግሪክ *አፖስቶሎስ ሐዋርያ*) ነው:: አማኞች ሁሉ የክርስቶስ አምባሳደር በመሆን ወደ ዓለም ሁሉ ተልከዋል:: ይህ ማለት ግን ማንኛውም አማኝ ልክ እንደ "አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት" ዓይነት ነው ማለት አይደለም:: የእነሱ ሐዋርያነትና የእኛ ሐዋርያነት እጅግ ለየቅል ነው:: በተልዕኮ እንጂ በሌላ አንመሳሰልም [1]::

ሁለተኛው አጠቃቀም ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጋር ብቻ የተዛመደ ነው:: እነዚህ ሐዋርያት የተመረጡትም ሆነ የተላኩት በራሱ በጌታ ነው:: የክርስቶስ ሐዋርያ በክርስቶስ ከመመረጡም በላይ የክርስቶስ ትንሣኤ ምስክር መሆን አለበት:: (ሐዋ 1÷21-22፤10÷40-41፤ 1ቆሮ 9÷1፤ 15÷8-9):: ጳውሎስ "ሐዋርያ" የሚለውን ቃል በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀመበት በሁለተኛው አጠቃቀም እንደሆነ እናስተውላለን:: ምክንያቱም በ1ኛ ቆሮንቶስ 12÷28 ላይ እንዳደረገው በዚህም ቦታ የጸጋ ስጦታዎችን ሲዘረዝር በቅድሚያ የጠቀሰው

"ሐዋርያትን" ነው:: ሐዋርያት የቤተክርስቲያንና የአዲስ ኪዳን ትምህርት መሠረት ናቸው (ኤፌ 2÷20፤ 3÷5):: በዚህ ረገድ እነርሱን የሚመስል ሰው በዚህ ዘመን የለም [2]:: አንድ መሠረት ተጥሏል (ኤፌ 2÷20):: አንድም ትምህርት ተሰጥቷል (ኤፌ 3÷5):: ከዚህ በኋላ ሌላ መሠረትና ሌላ መገለጥ ሊኖር አይችልም:: በክርስቶስ ላይ ከታነጽን ሌላ በማን ላይ እንታነጻለን? ክርስቶስን ካገኘን ሌላ ማንን እንሻለን? ከእንግዲህ ወዲህ የሚቀረው "ሐዋርያት በጣሉት መሠረት ላይ መገንባትና ሐዋርያትም በጽሑፍ ባቆዩት መገለጥ ላይ መታነጽ" ነው (ኤፌ 2÷21-22፤4÷13-16)::

ከዚህ ላይ ግን ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ወይም ከበጉ ሐዋርያት በተጨማሪ የቤተክርስቲያንን ተልዕኮ ወደ ተለያየ ቦታ ይዘው በመሄድና አብያተ ክርስቲያናትን በማደራጀት አገልግሎታቸውን የፈጸሙ የቤተክርስቲያን ሐዋርያት የሚባሉ እንዳሉ ማጤን ያስፈልጋል (2ቆሮ 8÷23፤ 1ተሰ 2÷5-8)::

በብሉይ ኪዳን የነበሩ ነቢያት በእግዚአብሔር ስም ("የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ያላል" እያሉ) የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቡ የሚናገሩ ናቸው:: የመልእክታቸውም ይዘት ሁለት መልክ አለው::

አንደኛው፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከኪዳኑ ማለትም ከትእዛዙ ሲወጣ ያለበትን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሁኔታ በማሳየት ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ የሚያስጠነቅቁ ናቸው:: ይህም የሚያሳየው የነቢያቱ አገልግሎት በየወቅቱ ሕዝቡ ያለበትን ሁኔታ የሚያመለክት መሆኑን ነው::

ሁለተኛው፥ ሕዝቡ በእግዚአብሔር መንገድ ባይመላለስ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚጠብቀው የሚያስጠነቅቁ ወይም ደግሞ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ፈርቶ ወደ መንገዱ ቢመለስ ምሕረቱን እንደሚያገኙ የሚያስረዱ ናቸው:: እንዲሁም የተሰወረን፥ ያለና ሊሆን ያለውን ዕውቀት በመልእክታቸው ይገልጡ ነበር:: ይሁን እንጂ የመልእክታቸው አብዛኛው ክፍል በወቅቱ የእግዚአብሔር ሕዝብ ያለበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው::



በአሁኑ ጊዜ የነቢያትን አገልግሎት ስናስብ የወደፊቱን ተናጋሪዎች ብቻ አድርገን እንቆጥራቸዋለን:: የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ትክክለኛው የእግዚአብሔር መንገድ መመለስ እንዳለበት በመልእክታቸው የሚጣሩ መሆናቸውንም መዘንጋት የለብንም:: እንዲህ ሲባል ግን የተሰወረውን ወይም ሊመጣ ያለውን በቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን ስር በመሆን አገልግሎት አይሰጡም ማለት አይደለም::

ጳውሎስ ሐዋርያትንና ነቢያትን ከጠቀሰ በኋላ ወንጌል ሰባኪዎችን ደግሞ ያነሳል:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ወንጌል ሰባኪ ወይም ወንጌላዊ የሚለው ስም (noun) ሦስት ጊዜ ብቻ ነው የተጠቀሰው:: ኤፌ 4÷11 ጨምሮ በሐዋ 21÷8 ላይ ፊልጶስ፥ በ2ኛጢሞ 4÷5 ላይ ደግሞ ጢሞቴዎስ በዚህ ስም ተጠርተዋል:: ይህ ቃል በስም (noun) ደረጃ ሦስት ጊዜ ብቻ ቢጠቀስም በግሥ ደረጃ ግን ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል:: ከሌሎች አዲስ ኪዳናዊ ንባባት እንደምንረዳው አማኞች ሁሉ የወንጌል ባለአደራዎች ናቸው:: ይህ ንባብ ("አንዳንዶቹ የወንጌል ሰባኪዎች... እንዲሆኑ ... ሰጠ") ግን ልዩ አጠቃቀም አለው:: በሐዋርያት ዘመን ወንጌል ሰባኪዎች እንዳሉ ሁሉ በዚህም ዘመን አሉ:: "ወንጌል ሰባኪ" የሚለው ቃል ወንጌልን ከመስበክና ስለ ወንጌልም ከመመስከር ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነው::

እዚህ ላይ የፊልጶስን አገልግሎት መጥቀሱ ተገቢ ይሆናል:: ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ለስግደት ከሄደበት ከኢየሩሳሌም ወደ አገሩ በመመለስ ላይ እያለ የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር:: በመንፈስ ቅዱስ የተላከው ፊልጶስ ወደ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ቀረበና "የምታነበውን ታስተውለዋለህን?" (ሐዋ 8÷30) በማለት ጠየቀው:: ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የሰጠው መልስ "የሚያስረዳኝ ሰው ሳይኖር እንዴት ሊገባኝ ይችላል?" የሚል ነበር:: ከዚህ በኋላ ፊልጶስ ከኢሳይያስ መጽሐፍ ጀምሮ "ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት" (ሐዋ 8÷35):: እንዲህ ያለ ታላቅ አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ዛሬም ያስፈልጉናል::

በኤፌ 4፥11 ላይ የተጠቀሱት ሌሎች ስጦታዎች "እረኞችና አስተማሪዎች" የሚሉት ናቸው። እዚህ ላይ "እረኞችና አስተማሪዎች" የሚለው ስማዊ ሐረግ ሁለት ሰዎችን ነው? ወይስ አንድ ሰውን ነው? የሚያመለክተው የሚል ጥያቄ ይነሳል። እንደ አንዳንድ ሰዎች አስተያየት ይህ ስማዊ ሐረግ ሁለት ሰዎችን ነው የሚያመለክተው። በሌላ አነጋገር እረኞችም አሉ፤ አስተማሪዎችም ደግሞ አሉ። የሐረጉ ሰዋሰዋዊ አወቃቀር እንደሚያመለክተው ግን ሁኔታው ከዚህ ይለያል። "እረኞችና አስተማሪዎች" የሚለው ሐረግ "ቱስ ዴ ፓይሜናስ ካይ ዲዳስካሉስ" ከሚለው የግሪክ ሐረግ የተተረጎመ ነው። በግሪክ ሰዋስዋዊ አገነባብ በ "ካይ" (እና) ከተጣመሩ ሁለት ስሞች (nouns) ፊት አንድ የጋራ የተወሰነ መስተአምር ሲኖር ሁለቱ ስሞች ሁለት የተለያየ ነገርን አያመለክቱም። ሁለት ስሞች በአንድ የጋራ መስተአምር ሲጣመሩ አንድ የሆነ፥ የተባበረና የተስማማ ይዘት አላቸው ማለት ነው። ነገሩ እንዲህ ከሆነ "አንዳንዶቹ እረኞችና አስተማሪዎች" የሚለው ሐረግ "አንዳንዶቹ እረኞች-አስተማሪዎች" ወይም "አንዳንዶቹ እረኞችም አስተማሪዎችም" ተብሎ መተርጎም ይኖርበታል [3]።

እንዲህ ያለው ድምዳሜ ላይ የደረስነው ሰዋስዋዊ አገነባብን ብቻ መሠረት በማድረግ አይደለም። እረኞች የእግዚአብሔርን መንጋ እንዲጠብቁና እንዲመግቡ የታዘዙ ከሆነ (ሐዋ 20፥28፤ 1ጴጥ 5፥2)፥ ጥበቃውንም ሆነ ምግባውን የሚያካሂዱት የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ነው (ሐዋ 20፥27፤29፥31)። አለበለዚያ የእረኝነት ሥራ ተሠራ ማለት አይቻልም። በሌላ በኩል ደግሞ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ የሆኑ ሁሉ "የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ችሎታ" ያላቸው መሆን አለበት (1ጢሞ 3፥2)። እንግዲህ እረኞች የሆኑ ሁሉ ለማስተማር የሚበቁ መሆን አለባቸው ማለት ነው።

እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባው ከአስተዳደር ተነጥሎ ሙሉ የማስተማር ጸጋና ጥሪ ያላቸው አስተማሪዎች በቤተክርስ ቲያን ውስጥ የሉም ማለታችን አይደለም (የሐዋ 13:1፤ 1ቆሮ 12:29)።



ክርስቶስ ኢየሱስ የጸጋ ስጦታዎችን ለቤተክርስቲያን የሰጠው "አካሉ የሆነችው ቤተክርስቲያን ታድግና ትገነባ ዘንድ፥ ምዕመናንም ለመንፈሳዊ አገልግሎት ይዘጋጁ ዘንድ" ነው (ኤፌ 4፥12)። ጌታ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የወሰነው "አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ" ስጦታዎችን በመስጠት ነው (ኤፌ 4፥11)። የምሥራቹ ቃል ካልተሰበከ እምነት ከወዴት ይገኛል (ሮሜ 10፥14-17)? የእግዚአብሔርስ ቃል ካልተገለጠ ክርስቶስን መምሰል ከወዴት ይገኛል (ኤፌ 4፥12-16)? እምነትም ሆነ ክርስቶስን መምሰል ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ አይገኝም።

እንግዲህ በኤፌ 4፥11 ላይ የተዘረዘሩት የጸጋ ስጦታዎች ቤተክርስቲያንን ለማነጽና ለማሳደግ የሰተጡ እንጂ እንደ ልዩ የአገልግሎት ቢሮ የሚታዩ አይደሉም። በቤተክር ስቲያን ውስጥ ልዩ መደብ ለመፍጠር ካልታሰበ በቀር ይህ ንባብ በተለምዶ "አምስቱ አገልግሎቶች" (fivefold ministry) የሚባለውን እሳቤ አያመለክትም። አማኞች ሁሉ የንጉሥ ካህናት ከሆኑ በኋላ "ከዚህ መለስ አገልጋይ፥ ከዚህ መለስ ምዕመን" የሚል መድረክ መፍጠር ፈጽሞ አግባብ አይደለም። "አምስቱ አገልግሎቶች" የሚለው እሳቤም የኀሩያን ምስፍናን ወይም የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝን (aristocratic) እሳቤ የሚከተል እንጂ የእግዚአብሔርን ሃሳብ የሚከተል አይደለም [4]።

በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛና ዝቅተኛ ወይም ካህንና ምዕመን የሚል የልዩነት መደብ የለም። እንዲህ መሰሉን የልዩነት መደብ ለመፍጠር መሞከር ግን "እናንተ (እከሌ ተከሌ ሳይባል) ... የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ" (1ጴጥ 2፥9) የሚለውን የጌታን ቃል ፊት ለፊት ለመቃረን መወሰን ማለት ነው። አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው፤ እንዲሁም የጸጋ ስጦታዎች ልዩ ልዩ ናቸው ማለት አንድ ነገር ነው። በአገልግሎትና በጸጋ ስጦታዎች ልዩነት ላይ ተመስርቶ የልዩነት ድንበር ማበጀት ግን ሌላ ነገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ለአማኞች ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች እንደተሰጡ እንጂ አንዱ አማኝ በሌላው አማኝ ላይ የበላይነት

እንዳለው አያስተምርም:: ጳውሎስም በኤፌ 4፥11 ላይ ሊያሳየን የፈለገው የተለያየ የጸጋ ስጦታ ያላቸው አገልጋዮች (ልዩና የላቀ ቦታ ያላቸው ሳይሆን) በቤተክርስቲያን ውስጥ መኖራቸውን ነው:: ይህም የሆነው "የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደመሆን ፥ የክርስቶስም ሙላት ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ" እንድንደርስ ነው (ኤፌ 4፥13):: እነዚህ ስጦታዎች የተሰጡት አካሉ ሁሉ አንዱ ከሌላው ሳይለይ በጥቅሉ ወደ ክርስቶስ ሙላት እንዲደርስ ነው:: ሁሉ ወደ ሙላቱ ከደረሱ ደግሞ ይህ የጎደለው የሚባል ማንም አይኖርም:: አማኞች ወደ ክርስቶስ ሙላት ደረሱ ማለት የከፍታና የዝቅታ ወይም የማንነት ልዩነት የለም ማለት ነው:: የአገልግሎቱ ልዩ ልዩነት ይህ የአካሉ ወደ ሙላት የመድረሱ ተልዕኮ እስከሚፈጸም ነው:: ተልዕኮው ግቡ ሲደርስ ይሄም የተጠቀሰው ልዩነት ይቀራል::

ሐዋርያ፥ ነቢይ፥ ወንጌላዊ፥ እረኛ አስተማሪዎች የሚሉት የአገልግሎት ጥሪዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ የሥልጣን ተዋረድን የሚያሳዩ ሳይሆን ለቤተክርስቲያን መታነጽ የተሰጡ ናቸው:: በአካል ውስጥ ያሉ ብልቶች በተጠሩበት መጠራት ተግባራቸውን በሥርዓት እንደሚያከናውኑ ሁሉ ስጦታ ያላቸውም አገልጋዮች በክርስቶስ ጌትነት ስር በመሆን ለቤተክርስቲያን መታነጽ ተግባራቸውን በእኩልነት መፈጸም ይኖርባቸዋል:: ምንም ዓይነት የአገልግሎት ጸጋ ቢኖረንም አማኞች ሁሉ ግን በክርስቶስ የሥልጣን ወንበር ስር በመሆን ራሳችንን መሥዋዕት እስከማድረግ በመሄድ አገልግሎታችንን እንፈጽማለን:: አንዳችን በሌሎች ላይ እንድንሠለጥን አልተፈቀደልንም:: ጌታ አማኞችን በኃጢአትና በሰይጣን ላይ ባለሥልጣን አድርጎናል እንጂ አንዳችን በሌላው ላይ እንድንሠለጥን አላደረገንም::

በዘመናችን በአንዳንድ አገልጋዮች ዘንድ የሚታየው የታላቅነት፥ የባለሥልጣንነት ፍላጎትና አካሄድ በበጉ ሐዋርያት ዘንድ እንኳ ከቶ ያልታየ ነበር:: በእነርሱ ሕይወትና



አገልግሎት ጎልቶ የወጣ የነፍሳት ፍቅርና ስለ እነርሱም መሥዋዕት እስከመሆን የመስጠት ጉዳይ ነበር::

በሐዋ 15 የምንመለከተው የበጉ ሐዋርያት ራሳቸውን በኢየሩሳሌም ሽማግሌዎች ላይ ሲሾሙ ወይም የበላይ አድርገው ሲያስቀምጡ ሳይሆን ሐዋርያቱ ከሽማግሌዎቹ ጋር አብረው እኩል ተቀምጠው ለቤተክርስቲያን የሚበጀውን ጉዳይ ሲመክሩና ሲዘክሩ ነው የምናየው:: እንዲሁም የአካል ብልቶችን ማበላለጥ እንደማይገባ ሁሉ መጋቢን ከወንጌላዊ ወይም ከአስተማሪ ማስበለጥ ወይም እርስ በርስ ማበላለጥ አይገባም::

# ክፍል ሁለት

# የአጥቢያ ቤተክርስቲያን መስተዳድርና ዲኖሚኔሽን



# ምዕራፍ ስድስት

# የአጥቢያ ቤተክርስቲያን መስተዳድር

## 6.1 የመስተዳድር ዓይነቶች

በአዲስ ኪዳን ውስጥ መልክና ቅርጽ ያለው የአስተዳደር ሥርዓት የለም ብለው በእርግጠኝነት የሚናገሩ ሰዎች አሉ [1]:: እንዲያውም እግዚአብሔር ቁርጥ ያለ የአስተዳደር ሥርዓት ያልሰጠን እኛ ያሻንን መስተዳደር እንድንቀርጽ ነው ይላሉ:: እንዲህ ዓይነቱ አባባል ግን ፍጹም ስህተት ነው:: በዚህ ጉዳይ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ እያለው፥ ነገሩን ከባድና ውስብስብ ለማድረግ መሞከር ተገቢ አይደለም::

ቤተክርስትያን ቅርጽ የለሽ ተቋም አይደለችም:: ቤተክርስትያን አስተዳደራዊ መልክና ቅርጽ አላት:: ዋናው ጥያቄ ግን የትኛው መስተዳድራዊ ቅርጽ ነው በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተገለጠው? የሚል ነው:: የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚያሳየው ለረጅም ዓመታት የታወቁ ሦስት ዋና ዋና የቤተክርስቲያን መስተዳድራዊ ቅርጾች በሥራ ላይ ውለዋል:: እነርሱም:- ኤጲስቆጶሳዊ መስተዳድር፥ ሽማግሌያዊ መስተዳድርና ማኅበረ ምዕመናናዊ መስተዳድር በመባል ይታወቃሉ:: ከዚህ በታች እነዚህን መስተዳደራዊ ቅርጾች በየተራ እንመለከታለን::

### 6.1.1 ኤጲስቆጶሳዊ መስተዳድር (Episcopal government)

ኤጲስቆጶሳዊ መስተዳድር በተወሰኑ የኤጲስቆጶሳት አመራር ላይ የተመሠረተ ነው:: ኤጲስቆጶስ የሚለው ቃል "ሄፒስኮፓስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተወረሰ ነው:: ሄፒስኮፖስ ማለት ጠባቂ ወይም አለቃ ማለት ነው:: የዚህ መስተዳድር መሠረታዊ እሳቤ የተመረኮዘው ጳጳሳትን፥ ካህናትንና ዲያቆናትን የመሾም ሙሉ ሥልጣን ያለው በኤጲስቆጶሱ እጅ

ነው በሚለው ጽኑ አቋም ላይ ነው:: ይህ የሹመት አሰጣጥ ሥልጣን "ሐዋርያዊ ምትክነት" (Apostolic Succession) በመባል ይታወቃል::

ኤጲስቆጶሳውያን የሚሰጡት ዓይነተኛ ማስረጃ የጌታ ወንድምና ሐዋርያ የነበረውን ያዕቆብን ነው:: ያዕቆብ÷ በኢየሩሳሌም በነበረች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ቦታ የነበረው መሆኑን ሉቃስ ሲጠቅስ (ሐዋ 15÷13-21)፤ "አዕማድ መስለው ከሚታዩት" (ገላ 2÷9) ውስጥ ደግሞ አንዱ እንደነበር ጳውሎስ ገልጿል (የሐዋ 12÷17፤21÷18፤ገላ 1÷19):: ኤጲስቆጶሳዊያን የመስተዳድራቸውን ልክነት ለማሳየት የሚሞክሩት ይህ ሰው በጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበረውን ሚና ነቅሶ (ለይቶ) በማውጣት ነው::

ያዕቆብ ከሌሎች የቤተክርስቲያን መሪዎች በተለይም ከአጥቢያ ቤተክርስቲያናት ጋር የነበረውን ግንኙነት ቀረብ ብለን ስንመለከት ሁኔታው ከዚህ ለየት ብሎ እናገኘዋለን:: በአንጾኪያ በነበረችው ቤተክርስቲያን ውስጥ "በሙሴ ሕግ መሠረት የግርዘትን ሥርዓት ካልፈጸማችሁ ልትድኑ አትችሉም" (የሐዋ 15÷1) በማለት ክርስቲያኖችን የሚያውኩ ቡድኖች ተነስተው ነበር:: ጳውሎስና ባርናባስ ከሌሎች ወንድሞች ጋር በመሆን ጉዳዩን ለማስታወቅ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ሄዱ:: የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ከሐዋርያትና ከሽማግሌዎች ጋር በመሆን በጉዳዩ ላይ ከተወያዩ በኋላ የውሳኔውን ሐሳብ ለአንጾኪያ ቤተክርስቲያን በወንድሞች በኩል ላኩ (ሐዋ 15÷25):: እዚህ ላይ ልናጤነው የሚገባው ነጥብ የውሳኔው ሃሳብ የአንድ ሰው ማለትም የያዕቆብ ብቻ አለመሆኑን ነው:: ውሳኔው ሲተላለፍ "ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ከቤተክርስቲያን ሰዎች ሁሉ ጋር" (የሐዋ 15÷22) በመሆን ነው:: ይህም የያዕቆብ አመራር ኤጲስቆጶሳዊ ነው የሚለውን አቋም በእጅጉ የሚያፈርስ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ያዕቆብ በጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ ብቸኛ ኤጲስቆጶሳዊ ሥልጣን እንድነበረው የሚያመለክት ማስረጃ የለም:: በጳውሎስ ሚሲዮናዊ አገልግሎት የተቋቋሙ አያሌ ቤተክርስቲያናት (ለምሳሌ በቆሮንቶስና በኤፌሶን የነበሩ ቤተክርስቲያናት)



ችግሮቻቸውን በራሳቸው ሲፈቱ ነበር እንጂ ያዕቆብ የዚህ ሁሉ ወሳኝ ሆኖ በአጥቢያም ሆነ ከአጥቢያው ውጪ መሪዎቻቸውን ሲመርጥ አልታየም (1ቆሮ 5÷12-13፤ የሐዋ 20÷28-29) ::

እርግጥ ነው÷ ያዕቆብ በዘመኑ ጠንካራ የቤተክርስቲያን መሪ ነበር:: በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ንጹሕ ሰው ስለነበር "ጻድቁ ያዕቆብ" የሚል ቅጽል ስም እንደተሰጠውና ለጸሎት በመንበርከኩ ብዛት "ጉልበቱ የግመል እግር ይመስል መጅ አብቅሎ እንደነበር" [2] የቤተክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል:: ያዕቆብ ታላቅ ሰው ነበር ማለትና በአንድ ወቅት ብቸኛ ኤጲስቆጳሳዊ ሥልጣን ነበረው ማለት ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱስ ያዕቆብ ታላቅ ሰው መሆኑን እንጂ የያዕቆብን ብቸኛ ኤጲስቆጶሳዊ ሥልጣን አስመልክቶ ማብራሪያ አይሰጥም::

ኤጲስቆጶሳውያን የአመራራቸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያቀርቡት ሌላው ማስረጃ "ሐዋርያዊ ምትክነት" የሚለውን ነጥብ ነው:: ሐዋርያዊ ምትክነት ማለት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ሥርዓተ ሹመት ማለት ነው:: ሐዋርያት በምትካቸው ጳጳሳትን ሾሙ÷ ጳጳሳት ደግሞ በምትካቸው ሌሎች ጳጳሳትን ሾሙ÷ እንዲህ እያለ ሥርዓተ ሹመቱ እኛ ዘንድ ደረሰ:: እንግዲህ በቤተክርስቲያን ውስጥ ዋናውን የአገልግሎት ቦታ መያዝ ያለባቸው በዚህ ሥርዓተ ሹመት ውስጥ ያለፉ ሰዎች ብቻ ናቸው በማለት ያስተምራሉ::

ስለ ሐዋርያዊ ምትክነት በምንነጋገርበት ወቅት÷ግልጽ መሆን ያለበት አንድ አቢይ ጉዳይ አለ:: ይኸውም ከሐዋርያት የተቀበልነው አስተምህሮ (Doctrine) እንጂ ሥርዓተ ሹመት አይደለም:: ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተቀባበለ የመጣው ሐዋርያዊ ትምህርት እንጂ ሐዋርያዊ ሥልጣን ወይም ሐዋርያዊ ቢሮ አይደለም [3]:: ሐዋርያት ወንጌል እንዲሰብኩ÷ ድውዮችን እንዲፈውሱና አጋንንትን እንዲያወጡ ሥልጣን ተሰጣቸው እንጂ ሐዋርያዊ ሹመት እንዲሰጡ ከቶ አልታዘዙም (ማር 3÷13-19) :: ሌላው ቀርቶ በሐዋርያት ዘመን እንኳን ተተኪ ሐዋርያት አልነበሩም:: አዲስ ኪዳን የሐዋርያትን ቦታ

የተኩ ሽማግሌዎችና ጳጳሳት እንዳሉ ቢያስተምርም ይህ ምትክነት ግን ሐዋርያዊ አይደለም:: ምክንያቱም የአተካኩ ደረጃና ሥልጣን (Position) ልዩ ነው[4]:: ሽማግሌዎችና (እረኞች/ጳጳሳት/ኤጲስቆጶሳት) ዲያቆናት ተመርጠው የሚሾሙት በቅዱሳንና በእግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (ሐዋ 20፥28፤ 1ጢሞ 3፥1-7፤ ቲቶ 1፥5-9):: እንዲሁም በ250 ዓ.ም. አካባቢ ዲዳኬ በመባል በሚታወቀው መጽሐፍ ላይ ጳጳሳትና (ሽማግሌዎች) ዲያቆናት የሚሾሙት በማኅበረ ምዕመናን እንደሆነ በግልጽ ተቀምጧል (ዲዳኬ 15፥1 ይመለከቷል) [5]:: በአሁኑ ጊዜ ኤጲስቆጶሳዊ መስተዳድር በስፋት የሚታየው በአንግሊካን፥ በኦርቶዶክስና በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያናት ውስጥ ነው::

### 6.1.2 ሽማግሌያዊ መስተዳድር (Presbyterian Government)

ሽማግሌያዊ መስተዳድር አንዳንድ ጊዜ ውክልናዊ መስተዳድር ሊባል ይችላል:: ምክንያቱም የሽማግሌዎቹ የአመራር ሥልጣን በውክልና የተገኘ ነው:: አዲስ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ በተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ "ፕረስቡተሮስ" ማለት ሽማግሌ ማለት ነው:: ቃሉ በዕድሜ ብቻ ሳይሆን በአዕምሮም መብሰልን ያካትታል:: በሌላ አነጋገር ዕድሜን ብቻ ሳይሆን ልምድንም የሚያሳይ ቃል ነው::

በሽማግሌያዊ መስተዳድር አወቃቀር ውስጥ በርካታ የሥልጣን እርከኖች አሉ:: አጥቢያ ቤተክርስቲያናት የሚመሩት ከየአጥቢያ ቤተክርስቲያናቱ ከምዕመናን መካከል በሚመረጡ ሁለት ዓይነት ሽማግሌዎች ነው:: እነሱም አስተዳዳሪ ሽማግሌና አስተማሪ ሽማግሌ በመባል ይታወቃሉ:: በአንድ የተወሰነ አውራጃ ወይም ክልል ውስጥ የሚገኙ አጥቢያ ቤተክርስቲያናት የየራሳቸውን ሽማግሌዎች መርጠው በመላክ የአውራጃ ወይም የክልል የሽማግሌዎች ጉባኤ እንዲመሠረት ይደረጋሉ:: ይህን የሽማግሌዎች ጉባኤ በበላይነት የሚመራ ሲኖዶስ ከዚሁ ከሽማግሌዎች ጉባኤ መካከል በሚመረጡ ሰዎች ይቋቋማል:: ከሲኖዶሱ በላይ ደግሞ ጠቅላላ ጉባኤ ይኖራል:: ይህ ጠቅላላ ጉባኤ የመጨረሻው



ከፍተኛ የአስተዳደር አካል ነው:: እንግዲህ ከአጥቢያ ቤተክርስቲያናት በላይ በየደረጃው የተዋቀሩ የአስተዳደር ክፍሎች አሉ ማለት ነው::

ምንም እንኳን አስተዳዳሪና አስተማሪ ሽማግሌዎች እኩል ሥልጣን ቢኖራቸውም በሁለቱ መካከል ግን ግልጽ ልዩነት ተደርጓል:: አስተማሪ ሽማግሌዎች በክህነት አገልግሎት ቀዳሚ ናቸው:: ከአቿቿማቸው መገንዘብ እንደሚቻለው አስተማሪ ሽማግሌዎች የሚሾሙት በአውራጃ የሽማግሌዎች ጉባኤ ወይም በሌሎች ከፍተኛ አገልጋዮች ሲሆን አስተዳዳሪ ሽማግሌዎች የሚሾሙት ግን በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ነው:: አስተዳዳሪ ሽማግሌዎች በአስተዳደር ጉዳዮች ላይ ሲወስኑ ቃሉን ማገልገልና ሥርዓተ ቁርባንን ማስፈጸም ደግሞ የአስተማሪ ሽማግሌዎች ድርሻ ነው::

አዲስ ኪዳናዊ ንባባት በግልጽ እንደሚያሳዩት ቤተክርስቲያንን መጠበቅና መንከባከብ ለሽማግሌዎች የተሰጠ አደራ ወይም ኀላፊነት ነው:: ሽማግሌዎች ከሐዋርያት ጋር በመሆን በማናቸውም የቤተክርስቲያን ጉዳዩች ላይ አመራርና አስተያየት ይሰጡ ነበር (የሐዋ 15፥4፥22-23):: የሽማግሌዎችን የአመራር ብቃት ለመለካት የቀረቡት መመዘኛዎች (1ጢሞ 3፥4-5) በትክክል የሚያመለክቱት፥ ሽማግሌዎች የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪና መሪ መሆናቸውን ነው (1ተሰ 5፥12-13፤ ዕብ 13፥17):: በሌላ በኩል ደግሞ ከአጥቢያ ቤተክርስቲያናት በላይ የአጥቢያ ቤተክርስቲያናትን ጉዳይ የሚመለከት አንድ አካል መኖር አለበት:: ምክንያቱም የኢየሩሳሌሙ ጉባኤ (የሐዋ 15፥1-40) የአጥቢያ ቤተክርስቲያናትን ችግር ለመፍታት የተቋቋመ አንድ የበላይ ክፍል ነበርና ነው:: በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተፈጥሮ የነበረው ችግር (የሐዋ 15፥1-2) መፍትሄ ያገኘው በዚህ በኢየሩሳሌሙ ጉባኤ አማካይነት እንደነበር በግልጽ ተጠቅሷል (የሐዋ 15፥22-29):: ይህ እንግዲህ የሽማግሌያዊ መስተዳድር ተከታዮች የሚያቀርቡት ማስረጃ ነው::

ከዚህ በላይ ለማየት እንደተሞከረው በሽማግሌያዊ መስተዳድር ውስጥ የአጥቢያ ቤተክርስቲያናትን ጉዳይ በጋራ ሆኖ የሚመለከት አንድ የበላይ ክፍል ያለ ሲሆን አጥቢያ ቤተክርስቲያናት የሚመሩት ደግሞ በሽማግሌዎች ነው::

የዚህ መስተዳድር አወቃቀሯ ችግር አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ያላቸውን ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት በመንጠቅ ከቤተክርስቲያን በላይ ለሆነ አስተዳደራዊ ሥልጣን ስለሚሰጥ ነው:: የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ውዝግብ አስተያየት እንዲሰጥበት ወደ ኢየሩሳሌም የተወሰደው በራሷ በአንጺያ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ፈቃደኝነት ነበር (የሐዋ 15÷1-2):: ይህ የሚያስረዳን በአንጾኪያ ቤተክርስቲያንና በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መካከል የእህትማማቻዊ ግንኙነት መኖሩን እንጂ አንዱ አጥቢያ በሌላው አጥቢያ ላይ የበላይ መሆኑን የሚያመለክት አይደለም:: አንድ ወቅት ላይ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ከባድ ችግር ገጥሟት ሳለ በመቄዶንያ÷ በአካያና በገላትያ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የገንዘብ እርዳታ ለመላክ ወስነው ነበር (1ቆሮ 16÷1-4፤ ሮሜ 15÷26):: እነዚህ የአሕዛብ ቤተክርስቲያናት ይህን ለማድረግ የተነሱት በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ላይ ሥልጣናዊ ተጽዕኖ ለማድረግ አይደለም:: ይልቁንም በክርስቶስ አካላት መካከል ክርስቲያናዊ ኅብረትና ትስስብ ሊኖር የተገባ መሆኑን የሚያሳይ ነው (1ቆሮ 12÷26):: በአጥቢያ ቤተክርስቲያናት መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት ክርስቲያናዊ እህትማማችነት እንጂ አንዱን የበላይ ሌላውን የበታች የሚያደርግ ግንኙነት አይደለም:: ምክንያቱም የቤተክርስቲያን ራስ ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነውና (ኤፌ 5÷ 24-30)::

### 6.1.3 ማኅበረ ምዕመናናዊ መስተዳድር (Congregational Government)

ማኅበረ ምዕመናናዊ መስተዳድር ቀደም ሲል ከተመለከትናቸው መስተዳድራዊ ቅርጾች በብዙ የሚለይበት ነጥብ አለው:: ከዚህም ውስጥ አንደኛውና ዋነኛው÷ አንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የራሷን ጉዳይ በራሷ የመመርመርና



የመወሰን ነፃነትና መብት አላት የሚለው ነጥብ ነው:: በሌላ አነጋገር በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ላይ ከክርስቶስ በቀር ማንም የበላይ የለም :: በአጥቢያ ቤተክርስቲያኒቷ ውስጥ በማንኛውም ወሳኝ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ መስጠት የሚችሉት አባላት ናቸው:: ይህ ማለት ግን መስፈርቱን አሟልተው የተመረጡ ሽማግሌዎች ቤተክርስቲያኒቷን የመምራትና የማስተዳደር ስፍራ የላቸውም ማለት አይደለም:: ይህ የአመራርና የአስተዳደር ሥልጣን ማኅበረ ምዕመናኑ ካለው ሥልጣን ሥር ነው:: አንድ አባልና አንድ መሪ የሚኖራቸው ድምጽ እኩል ነው:: ሁሉም "የንጉሥ ካህናት" (1ጴጥ 2÷9) በሆኑበት ጉባኤ ውስጥ ታላቅና ታናሽ የለምና:: በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የአመራር ቦታን በመያዝ የሚገኝ ልዩ ሥልጣን የለም [6]:: የዚህ መስተዳድር እሳቤ የተመሠረተው አጥቢያ ቤተክርስቲያን የራሷን ጉዳይ ለመመልከት ሙሉ ሥልጣን አላት፤ እንዲሁም እያንዳንዱ አባል እኩል ነው በሚለው መርህ ላይ ነው::

መሪዎችን መምረጥ የቤተክርስቲያን ሥልጣን ነው:: ሐዋርያት በነበሩበት ዘመን እንኳን ከማኅበረ ምዕመናን ፍላጎት ውጪ የሚደረግ ምንም ነገር አልነበረም:: በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ውስጥ የአድልኦ ችግር በተፈጠረ ጊዜ ሐዋርያት ጉዳዩን በአግባቡ የሚመለከቱ ሰዎች እንዲመረጡ ሃሳብ አቀረቡ:: ሐዋርያት ያቀረቡት ሃሳብ ተቀባይነት ስላገኘ በእምነትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰባት ሰዎች ተመረጡ:: ይህ ሁሉ ተግባር የተከናወነው ግን በማኅበረ ምዕመናኑ ሙሉ ተሳታፊነት ነው (የሐዋ 6÷1-5):: በሌላ በኩል ደግሞ በኢየሩሳሌም ጉባኤ ላይ ቀርቦ የነበረው የመነጋገሪያ ጉዳይ በሐዋርያት አማካይነት ከተብራራ በኋላ ውሳኔ ያገኘው በስብሰባው ላይ በተገኙት ሁሉ ነው (የሐዋ 25÷12÷22-23÷25):: ውሳኔውም ሆነ ስምምነቱ የጥቂት ሰዎች (የሐዋርያትና የሽማግሌዎች) ሳይሆን የጉባኤው ሁሉ ነበር::

በተጨማሪም ሐዋርያዊ አስተምህሮን መጠበቅና ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ማስፈጸም ለአጥቢያ ቤተክርስቲያን የተሰጠ ኀላፊነት እንጂ ለተወሰኑ የአመራር አካላት ወይም

ካህናት የተሰጠ ልዩ ተልዕኮ አይደለም [7]:: ይህ እንግዲህ በማኅበረ ምዕመናናዊ መስተዳድር ውስጥ የሚታይ አቋም ነው::

ይህ መስተዳድር፥ ማኅበረ ምዕመናን በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ ማድረጉ አግባብነት ያለውና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን እንመለከታለን:: ምዕመናን የንጉሥ ካህናት ናቸው የሚለውን ሐሳብ ማንጸባረቁም መልካም ገጽታው ነው:: ይሁን እንጂ ምዕመናን በሁሉ ነገር ላይ ይሳተፉ ማለት ለምሳሌ በአስተምህሮ (Doctrine) ጥበቃና በሕይወት ንጽህና ላይ እንዲሁም በአስተዳደር ጉዳይ ሁሉ ላይ ምዕመናን ሁል ጊዜ በሁሉ ነገር ላይ ይሳተፉ ማለት አስቸጋሪ ይሆናል:: ይህም አጠቃላዩን የመጽሐፍ ቅዱስ ምክር ያላገናዘበና ወደ አንድ አቅጣጫ ያዘመመ ነው::

በሐዋ 20፥28 ላይ እንደምናነበው መንጋውንና ራሳቸውንም ከስህተት ትምህርት የመጠበቅ የመጀመሪያ ኀላፊነት የተሰጠው ለመላው ምዕመናን ሳይሆን ለሽማግሌዎች እንደሆነ በግልጽ እናስተውላለን:: የሕይወት አካሄድን በተመለከተ ደግሞ ሽማግሌዎች የመምከር፥ የመገሠጽና የመዝለፍ ሥልጣን እንዳላቸው እንመለከታለን::

በአስተምህሮ ጉዳይ ላይ ምዕመናን ሁሉ ይገቡ፥ ይሳተፉ ማለት ነባራዊ እውነታን በሚያገናዝብ መልኩ በጥሞና ብንመለከተው አስቸጋሪ ጉዳይ ነው:: ለምሳሌ በዘጸ 32 ላይ እንደምናነበው የእስራኤል ሕዝቦች ከግብጽ ምድር በጸናች ክንድ ያወጣቸውን አምላክና ከግብጽም ባርነት እየመራ ወደ ተስፋይቱ ምድር የወሰዳቸውን ሙሴን በመተው ፊታቸውን ወደ አማልክት ለመመለስ ተነሳስተው ነበር:: ሁሉ ነገር በአማኞች ውሳኔ ብቻ ይለቅ ከተባለ እንዲህ አይነቱ አሳዛኝ ታሪክ ሊፈጠር ይችላል:: ከዚህ በተጨማሪ ጥቂት ሰዎች አንድን ችግር ጠጋ ብለው ሊያዩትና ለችግሩም የመፍትሄ ሐሳብ (መንገድ) ከሰፊው ጉባኤ ይልቅ ለመስጠት ያመቻቸዋል:: በሐዋ 15 ላይ እንደምንመለከተው ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ለየት ብለው ተሰብስበውና ተወያይተው መፍትሄ ይዘው መጥተዋል::



ምዕመናንን ሁሉ በየዕለቱ ለሚነሱ ጉዳዮች እንስብስባቸውና እናወያያቸው ማለት አስቸጋሪ ነው:: ይህ ማለት ለአምልኮና ለትምህርት ጊዜ ጠፋ ማለት ነው:: በአጭር ጊዜ የሚቆረጠው ጉዳይ ምዕመናን ሁሉ አስትያየት ይስጡበት ከተባለ ጊዜ ያልቃል::

ከዚህ በተጨማሪ በአንድ አጥቢያ ጉዳይ ማንም ምንም በምንም አይነት መልኩ አያገባውም የሚለው አቋም ደግሞ አካላዊ አይደለም:: የክርስቶስ አካል አንድ አጥቢያ አይደለችምና:: በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ውስጥ በተከሰተው ጉዳይ ላይ በኢየሩሳሌም የነበረችው የክርስቶስ አካል መክራለች::

እስከ አሁን ድረስ ልዩ ልዩ የቤተክርስቲያን አስተዳደር ዓይነቶችን ስንመለከት ቆይተናል:: ከእነዚህ የአስተዳደር ዓይነቶች ውስጥ የትኛው አስተዳደር ነው የሚበጀው? የሚል ጥያቄ ይነሳብን ይሆናል:: ከላይ የተጠቀሱትን የአስተዳደር ዓይነቶች እንደተመለከትነው ሁሉም የየራሳቸው ደካማና ጠንካራ ጎን አላቸው:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ የመጀመሪያይቱን ቤተክርስቲያን አሠራር ስንመለከት ልብ ልንላቸውና ተግባራዊ ልናደርጋቸው የሚገቡ አሠራሮች እንዳሉ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 እና 15 ላይ ቁልጭ ብሎ ተጠቅሷል:: በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 ላይ ስንመለከት ምዕመናን ምርጫ የማካሄድ ሥልጣን ነበራቸው፤ በምዕራፍ 15 ደግሞ ከአንጾኪያ የመጡት መልእክተኞች ስለ አገልግሎታቸው ምስክርነት ሲሰጡና ሪፖርት ሲያቀርቡ ያዳምጡ የነበሩት ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ብቻ ሳይሆኑ መላው ምዕመናንም የማዳመጥና ጥያቄም የማንሳት ተሳትፎ ነበራቸው:: አወዛጋቢ ችግር ሲፈጠር ግን ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ለብቻቸው በነገሩ ላይ ከተወያዩና ከተመካከሩ በኋላ የደረሱበትን ውሣኔ ለምዕመናን በማስታወቅ ከመካከላቸው በተመረጡት ይሁዳና ሲላስ እንዲሁም ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ውሳኔያቸውን ለአንጾኪያ ቤተክርስቲያን እንዲያደርሱ በጋራ ሲልኳቸው እናያለን::

እንግዲህ ጤናማ የሆነ የቤተክርስቲያን አመራር በተመጣጠነና ሚዛናዊነትን በጠበቀ መልኩ ማለትም

ምዕመናንንና የአጥቢያ ቤተክርስቲያን የአመራር ኀላፊነት ያላቸውን ሽማግሌዎች በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ማሳተፍ እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ እንገነዘባለን:: ይህን አይነቱን አሠራር "ማኅበረ ምዕመናዊ ወሽማግሌያዊ" አመራር ማለት ይቻላል::

### 6.1.4 ማኅበረ ምዕመናናዊ ወሽማግሌያዊ መስተዳድር (Presbyterian-congregational government)

ማኅበረ ምዕመናዊ ወሽማግሌያዊ ስንል በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ አግባብ ባለው ሁኔታ ምዕመናን የሚሳተፉበት እንዲሁም አግባብ ባለው ሁኔታ ሽማግሌዎች የራሳቸውን ውሳኔ የሚሰጡበት ማለታችን ነው:: ለምሳሌ በሐዋ 6 ላይ ምዕመናን መንፈስ ቅዱስ እንዳደረባቸው የእግዚአብሔር ሰውነታቸው አገልጋዮችን ሲመርጡ እንመለከታለን:: ይህ መምረጥ ማን ያገልግል ብሎ የመወሰን ኀላፊነትና ሥልጣን ነው:: እዚህ ላይ የተመረጡትን አገልጋዮች የመሾሙን ጉዳይ ምዕመናን ሲያካሂዱት አንመለከትም:: ይህ የሚጠቁመን ምዕመናንም ሆኑ መሪዎች የየራሳቸው ድርሻ ያላቸው መሆኑን ነው::

በሐዋ 15 ስንመለከት ደግሞ ጳውሎስና በርናባስ እንደመጡ ሪፖርት ያደረጉት ለሁሉም (ለሐዋርያት፥ ለሽማግሌዎችና ለምዕመናን) ነው:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተነሳው ጉዳይ ላይ ሽማግሌዎችም ምዕመናንም ድርሻ ድርሻ እንደነበራቸው እናስተውላለን::

ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው ምዕመናን ሽማግሌዎችን የመምረጥ ኀላፊነትና ሥልጣን አላቸው:: ሽማግሌዎች ደግሞ ለመረጡአቸው ምዕመናን ስለ አጠቃላይ ሥራ ሪፖርት የማድረግና የመጠየቅ ግዴታ አለባቸው::

ሽማግሌዎች የአጠቃላይ ማኅበረ ምዕመናኑን የውክልና ሥልጣን የያዙ በመሆናቸው ይሠራሉ፥ ያስተዳድራሉ፥ አመራርም ይሰጣሉ:: የአጥቢያ ምዕመናን ደግሞ ሽማግሌዎች ለአገልግሎቱ የማይበቁ ሆነው ሲገኙ ወይም ከአገልግሎት ለተወሰነ ጊዜም ሆነ ለዘለቄታው ማረፍ አግባብ ሲሆን ውሳኔ ያደርጋሉ (1ጢሞ 3፥2፤ 5፥19፤ 1ጴጥ 5፥1-5፤ 3ዮሐ 9-10)::



በማኅበረ ምዕመናዊ ወሽማግሌያዊ መስተዳድር ውስጥ ሽማግሌዎችም ሆኑ ምዕመናን ኀላፊነትና አደራ አለባቸው:: የየፊና ኀላፊነታቸውን በተመለከተ በምዕራፍ ሰባት እንመለከታለን::

## 6.2 የአጥቢያ ቤተክርስቲያንና የዲኖሚኔሽን ግንኙነት

እንዲህ እንደ አሁኑ ራሱን በቻለ ንዑስ ርዕስ አይሁን እንጂ አልፎ አልፎ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ኅብረትና ግንኙነት ሊኖር የተገባ መሆኑን አውስተን ነበር:: ሆኖም ያ ኅብረትና ግንኙነት ምን መልክ ሊይዝ እንደሚገባ ምንም አስተያየት አልተሰጠም:: ስለዚህ ነገሩን አሁን ማንሳት አስፈላጊ ሆኗል::

በዚህ ክፍል ትኩረት የምንሰጠው በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያንና በአንድ ዲኖሚኔሽን መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት አስመልክቶ ይሆናል:: ከዚህ በተጨማሪም ስለ አንድ ዲኖሚኔሽን ተግባር ባጭሩ እንነጋገራለን:: በቅድሚያ ግን "ዲኖሚኔሽን" የሚለው ቃል ከየት እንደመጣና ምንስ ሐሳብ እንደወከለ ባጭሩ መመልከት ይኖርብናል::

"ዲኖሚኔሽን" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል "ዲኖሚኖ" ከሚለው የላቲን ቃል የተወረሰ ሲሆን በላቲን ቋንቋ "ዲኖሚኖ" ማለት "ለአንድ ነገር ስም ወይም መጠሪያ መስጠት" ማለት ነው:: ለአንድ ኅብረት ወይም ለአንድ ኅብረተሰብ በተለይም ለአንድ ሃይማኖታዊ ተቋም የምንሰጠው ስያሜ "ዲኖሚኔሽን" ይባላል:: ለምሳሌ ተመሳሳይ የእምነት አቋምና ልምምድ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት የሚፈጥሩት ኅብረትና አንድነት እንደ አንድ ዲኖሚኔሽን ሊቆጠር ይችላል:: በአገራችንም ቢሆን የኢትዮጵያ ወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ፥ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት፥ መሠረተ ክርስቶስ፥ ወዘተ... እያልን አንድ አጠቃላይ መጠሪያ የሰጠናቸው በርካታ ዲኖሚኔሽኖች አሉ:: በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ዲኖሚኔሽን የሚለው ቃል ተመሳሳይ ስም ይወክላል:: ለዚህ ባዕድ ስያሜ አቻ የሆነ የአማርኛ ቃል ባለመኖሩ እንዳለ በእንግሊዝኛው ቃል መጠቀም አስፈላጊ

ሆኖአል። በመሠረቱ ቃሉ የተለመደ ስለሆነ የመግባባት ችግር ይፈጥራል የሚል ግምት የለንም። ስለ ስያሜው አመጣጥና ስለ ወከለውም አሳብ ይሄን ያህል ከተነጋገርን ቀጥለን ወደ መሠረተ አሳቡ እንዘልቃለን።

ከሁሉ በፊት የሚነሳ አንድ መሠረታዊ ጥያቄ አለ። ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዲኖሚኔሽኖች አደረጃጀትና አወቃቀር የሚሰጠው አስተያየት አለ ወይ? ደግሞስ በአንድ ዲኖሚኔሽንና በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት ምን መልክ መያዝ አለበት? የሚል ነው። መቼም "በዚህና በዚያ ጉዳይ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያስተምራል?" ብሎ መጠየቅ ራሱን የቻለ ትልቅ ብልህነት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ተመሳሳይ የእምነት አቋምና ልምምድ ባላቸው አብያተ ክርስቲያናት አማካይነት ስለሚቋቋም ዲኖሚኔሽን የሚሰጠው አንድ ወጥ መርህ የለም። በሌላ አነጋገር ተመሳሳይ የእምነት አቋምና ልምምድ ባላቸው አጥቢያ ቤተክርስቲያናት መካከል የሚኖረው ግንኙነት ምን ዓይነት ነው? ለሚለው ጥያቄ ቁርጥ ያለ መልስ መስጠት አይቻልም። እንዲህ ሲባል ግን ስለዚህ ጉዳይ በተወሰነ ደረጃ ሊያሳዩን የሚችሉ ምንም አብነቶች የሉም ማለት አይደለም። ለምሳሌ የሐዋርያት ሥራ 15:1-16:6 ያለውን ክፍል ከሌሎች አዲስ ኪዳናዊ ንባቦች ጋር በማቀናጀትና የሚያስተሳልፉትንም አሳብ አንድ ላይ በማጠቃለል እንደየጊዜውና እንደየቦታው መጠቀም የምንችልበት የግንኙነት መርህ መጠቆም ይቻላል።

የሐዋርያት ሥራ 15:1-16:6 የሚያትተው የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት በኢየሩሳሌም ተደርጎ ስለነበረው የመጀመሪያው ክርስቲያናዊ ጉባኤ ነው።ይህ ጉባኤው የተጠራበት የራሱ የሆነ ምክንያት ነበረው። ከይሁዳ የመጡ አንዳንድ ሰዎች፥ ደኅንነት የሚገኘው በእምነት ብቻ ሳይሆን የሙሴን ሕግና ሥርዓት በመጠበቅም ጭምር ነው በማለት የአንጾኪያ ክርስቲያኖችን ያውኩ ጀመር (15:1)። ከዚህ በኋላ በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከባድ ውዝግብ ተከሰተ። ውዝግቡም የአስተምህሮ ውዝግብ ነበር (15:2)። የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ግን



በተከሰተው ውዝግብ አልተሸነፈችም። ይልቁንም በጉዳዩ ላይ ምክክር ካደረጉ በኋላ በኢየሩሳሌም ያሉ ወገኖችም ተጨማሪ አስተያየት እንዲሰጧቸው መልእክተኞችን ወደ ኢየሩሳሌም ላኩ (15:3)። በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ውስጥ የተፈጠረው ችግር እንዲህ ቀላል አልነበረም። ችግሩ መሠረታዊ የክርስትና አስተምህሮ ከሚባሉት ውስጥ አንዱን የሚመለከት ነበር። ሰው የሚድነው "በእምነት አማካይነት በጸጋ ብቻ" ነው? ወይስ በሕግ ሥራም ነው? (ኤፌ 2፥8-10)። የአንጾኪያ ወገኖችን ያሳሰባቸው "ታዲያ እውነቱ የቱ ነው?" የሚለው ጥያቄ ነበር። በመካከላቸው እንደነጳውሎስና እንደነበርናባስ ያሉ የበሰሉ ክርስቲያኖች ስለነበሩ የከረረና ከፍ ያለ ልዩነት አልተፈጠረም። ከችግሩ መሸሽ ሳይሆን ችግሩን ፊት ለፊት መጋፈጥ ብቸኛ አማራጫቸው ነበር። ስለዚህ የተከሰተውን ችግር ለመፍታት በአንድነት ተሰበሰቡ። በነገሩም ብዙ ከተወያዩ በኋላ ጉዳዩን በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ወገኖች ለማስታወቅና እነርሱም የሚሰጡትን ምክር ለማድመጥ ተስማሙ።

ከአንጾኪያ የተላኩት መልእክተኞች በኢየሩሳሌም የጠበቃቸው አቀባበል መልካም ነበር። ኢየሩሳሌም እንደደረሱ የሙሴን ሕግና ሥርዓት ካልጠበቃችሁ ልትድኑ አትችሉም የሚሉ ሰዎች ከይሁዳ መጥተው እንዳወኳቸው ተናገሩ (15:5፥24)። በኢየሩሳሌም የሚገኙ ወገኖች ከአንጾኪያ ቤተክርስቲያን የመጣውን ጥያቄ ለመመልከት ስብሰባ አደረጉ (15:7)። በስብሰባው ላይ ከተገኙት ሰዎች መካከል ጴጥሮስና ያዕቆብ እግዚአብሔር በኢየሩሳሌምና በአቅራቢያዋ ከተሞች አሕዛብን እንዴት እንዳዳነና እንዲያውም ለአይሁዶች የሰጠውን መንፈስ ቅዱስ ለአሕዛብም እንዴት እንደሰጠ እነርሱ ራሳቸው ምስክር መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ አይሁዳውያንም ሆኑ አረማውያን ደኅንነትን የሚያገኙት ከክርስቶስ በሚገኘው ጸጋና እምነት ብቻ መሆኑን በአንድ ቃል አረጋገጡ (15:7-11፥16-19)። ከዚህ በኋላ ከአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ለቀረበው ጥያቄ በአንድነት የተስማሙበትን መልስ ለመላክ ወሰኑ (15:22-26)። ለመላክ የወሰኑት መልስ ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር የተስማማና (15:13-15) ከመንፈስ ቅዱስም

ፈቃድ ጋር የተባበረ ነበር (15፡29)። የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን በጉዳዩ ላይ ያላትን ምክር ብቻ ሳይሆን ለመላክ የወሰነችው ጉዳዩን በበለጠ የሚያብራሩ ተጨማሪ መልእክተኞችንም ጭምር ነበር። ከወንድሞች መካከል መልካም ምስክርነት የነበራቸው በርስያንና ሲላስ ወደ አንጾኪያ ተላኩ (15፡22)።

ከላይ በቀረበው ታሪክ ውስጥ በርካታ ነገሮች ይስተዋላሉ። አንደኛው፥ በሁለት አጥቢያ ቤተክርስቲያኖች (በአንጾኪያና በኢየሩሳሌም) መካከል ኅብረትና ግንኙነት ሲደረግ ይታያል። የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን "እኔ ማንንም አልፈልግም" አላለችም። እንዲሁም የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን "ማንም እንዳይደርስብኝ" አላለችም። ኅብረትና ግንኙነት ማድረግ አዲስ ኪዳናዊ ወግ ነበር። ሁለተኛው፥ በችግር ጊዜ (አሁን የተፈጠረው ችግር የአስተምህሮ ችግር ነው) አንዱ ሌላውን ሲያግዝ ይታያል። የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን የገጠመኝን ችግር በራሴ ብቻ እፈታዋለሁ አላለችም። በኢየሩሳሌም ያለችው አጥቢያ ቤተክርስቲያን የተሻለ መፍትሄ ሊሰጧት እንደሚችሉ እርግጠኛ ነበረች። የኢየሩሳሌምም ቤተክርስቲያን ስለ ሌላው ምንም አያገባኝም አላለችም። ይልቁንም የሌላውን ችግር እንደ ራሷ በመቁጠር በምትችለው ሁሉ ለመርዳት ተነሳች። ሦስተኛው፥ በሁለቱ አጥቢያ ቤተክርስቲያኖች መካከል የነበረው ግንኙነት በመተሳሰብ ከዚያም አልፎ በወንድማማችነትና በእህትማማ ችነት ላይ የተመሠረተ ነበር። የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ማድረግ የምትችለውን ሁሉ ከማድረግ ወደ ኋላ አላለችም። በተፈጠረው የአስተምህሮ ችግር ላይ ያላትን ምክርና አስተያየት እንዲሁም ለተፈጠረው ችግር መፍትሄ ይሆናል ብላ የላከችውን ምክር በሚገባ የሚያብራሩ ተጨማሪ ወንድሞችንም ላከች። ምክሯን ብቻ ሳይሆን ያላትንም ነገር ሁሉ አካፈለች።

ይህን የአንጾኪያና የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ግንኙነት እንደምሳሌ የጠቀስነው ከዚህ ግንኙነት ውስጥ ልንገነዘበው የሚገባን "የኅብረትና የግንኙነት መመሪያ"



መኖሩን ለማሳየት ነው። በተጨማሪም በርካታ አዲስ ኪዳናዊ ንባባት እንደሚያረጋግጡት ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ሕዝብ ናት። ለምሳሌ ሐዋርያው ጴጥሮስ በአንደኛ መልእክቱ ላይ "እናንተ ግን ... የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ እግዚአብሔር ለራሱ ያደረጋችሁ ቅዱስ ሕዝብ ናችሁ" በማለት ጽፏል (2፡9)። በሌላ በኩል ደግሞ ቤተክርስቲያን እንደ አንድ ማኅበረሰብ ወይም እንደ አንደ ኅብረት ልትታይ የምትችል ናት። አዲስ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ በተጻፈበት ቋንቋ ይህ የቤተክርስቲያን ማኅበረሰብነትና ኅብረት "ኮይኖኒያ" በመባል ይታወቃል። በግሪክ ቋንቋ "ኮይኖኒያ" ማለት "ኅብረት ወይም መተሳሰብ" ማለት ነው [8]። ጳውሎስ በሁለተኛ ቆሮንቶስ መልእክቱ መዝጊያ ላይ ሲጽፍ "... የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት (ኮይኖኒያ) ከሁላችሁ ጋር ይሁን" (13፥14) በማለት ሐዋርያው ምኞቱን ገልጿል። በሌላ ቦታ ደግሞ እግዚአብሔር ከልጁ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ኅብረት (ኮይኖኒያ) እንዲኖረን የጠራን መሆኑን ይኸው ሐዋርያ አስታውቋል (1ቆ 1፡9)። በአማኞች መካከል እውነተኛ ኅብረትንና አንድነትን ማምጣት የሚችል መንፈስ ቅዱስ ነው። ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚገኘውን ጸጋና ደኅንነት እንደተካፈልን ሁሉ እርስ በርሳችንም ያን ሰማያዊ ኅብረት እንድንካፈል ተጠርተናል።

እንግዲህ ቤተክርስቲያን ሕያው ኅብረት የሚታይባት መንፈሳዊ ተቋም ናት። በአዲስ ኪዳን አነጋገር "የእግዚአብ ሔር ሕዝብ" ናት ሌሎች መንፈሳዊ ድርጅቶችና ተቋሞች እንዲህ ያለ ጠባይ የላቸውም። መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን የሚያቀርበው እንደ ሕያው ኅብረት እንጂ እንደ አንድ ድርጅት አይደለም። እርግጥ ነው ቤተክርስቲያን ድርጅታዊ አወቃቀር አላት። ሆኖም "ኮይኖኒያ" እንጂ "ድርጅት" ብቻ አይደለችም። ቤተክርስቲያን እንደ "ኮይኖኒያ" የምትታይ በመሆኑ ሌሎች መንፈሳዊ ድርጅቶች ሁሉ፥ ለምሳሌ እንደ ቃለ እግዚአብሔር አንባቢያን ማኅበር፥ ኢንተርናሽናል ባይብል ሦሳይቲ፥ ኢቫሱ (የዩኒቨርስቲና የኮሌጅ ወንጌላውያን ክርስቲያን ተማሪዎች ኅብረት)፥ ወንጌል በገጠር፥ ወጣት ለክርስቶስ፥ ኢቫንጀሊካል ቴዎሎጂካል ኮሌጅ (ኢ.ቲ.ሲ.) ወዘተ ... እንደ ድርጅት እንጂ እንደ "ኮይኖኒያ"

አይቆጠሩም። እንደነዚህ ያሉ መንፈሳዊ ድርጅቶች ለቤተክርስቲያን የተሰጠውን ተልዕኮ ለማፋጠን ከፍተኛ እገዛ ቢያደርጉም እንደ ቤተክርስቲያን ግን አይቆጠሩም። "ቤተክርስቲያን-አጋዥ መንፈሳዊ ድርጅቶች" ልንላቸው እንችላለን [9]። ዲኖሚኔሽኖች አስፈላጊና ጠቃሚ ነገሮች ናቸው። በሌላ አነጋገር ዲኖሚኔሽን በኀብረት አራማጅነቱና በአያያዥነቱ አስፈላጊ ነው።

በሐዋሪያት ሥራ 15፥1-29 ያለውን ክፍል ስንመለከት የጋራን ችግር ለመፍታት፥ የአስተምህሮን (doctrine) ጥራት በየአጥቢያው ለመጠበቅ፥ ከሥርዓት ውጪ የሚሄዱትን ለማረምና አካሄዳቸውን ለማስተካከል፥ በጋራ ለመመካከርና ውሳኔ ለማስተላለፍ ሥልጣን ያለው ተዋረድ እንዳለ እንመለከታለን። ይህ ዓይነቱ አሠራር በአካሄድ የገጠመን ችግር ለመፍታትና ለመረዳዳት አመቺ ሁኔታዎችን እንደፈጠረ ያስገነዝበናል (ሐዋ 11፥30፤ ሮሜ 15፥25-27፤ 1ቆሮ 16፥1-3፤ 2ቆሮ 8፥1-2፤ 8፥16፤ 9፤ 1-2)።

በኀብረት የመሥራት ጽንሰ ሐሳብ የግልን ሥልጣን እየቆረሱ በማዕከል ማድረግን ግድ ይላል። ከዚያም ለዚህ ለተማከለው የጋራ ሥልጣን እያንዳንዱ አባል መገዛት ይኖርበታል። ይህ የጋራ ጽንሰ ሐሳብ በባልና በሚስት መካከል ባለው እውነታ ጉልህ ሆኖ ይታያል። ሁለቱም ለጋራ ትዳራቸው በየግላቸው ማደር ይኖርባቸዋል፤ መብትንም ሆነ ግዴታን ይጋራሉና። እንዲሁም አብያተ ክርስቲያናት በጋራ ተሰባስበው ሲሠሩ በፈቃዳቸው የተወሰነ ሥልጣንን ከአጥቢያ ቤተክርስቲያናቸው ቆርሰው (ከፍለው) በአንድ የጋራ ማዕከል በማሰባሰብ ተግባራቸውን ለማከናወን ውሳኔ በሚያሳልፉበት ጊዜ ውሳኔው በአባል አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። ይህ አሠራር በተለምዶ "ዲኖሚኔሽናዊ አሠራር" በመባል ይታወቃል። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ላይ እንደምናነበው አብያተ ክርስቲያናት ለደኅንነት በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን ባሻገር የሙሴን ሕግ የመጠበቅ ማለትም መገረዝ እንደሌለባቸውና የአይሁድ እምነት ሥርዓቶችን መጠበቅ እንደማያስፈልጋቸው፥ ነገር ግን ለጣዖት ከተሠዋ፥



ከደምም፥ ከታነቀም፥ ከዝሙትም እንዲርቁ መመሪያ ተሰጣቸው። ይህም የአስተምህሮን አንድነት የመጠበቅ ሥልጣንን የሚያጸና ነው። ከዚህም የዲኖሚኔሽን አሠራርና አስፈላጊነት ይህን ከመሰለው አገልግሎት አንጻር ሊታይና ሊቀናጅ እንደሚገባ ማስተዋል ያሻል።

በዲኖሚኔሽን አሠራር የተካተቱት አጥቢያዎች ወደፊት ሌላ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ለማደራጀትና ዕውቅናን የመስጠት አሠራር ይኖራቸዋል። በአንድ ዲኖሚኔሽናዊ አሠራር ውስጥ ያሉ አጥቢያ ቤተክርስቲያናትን በዲኖሚኔሽናዊ መልክ የሚያያይዛቸው ትልቁ ነገር የአስተምህሮ ወጥነት (አንድነት) ነው። የአስተምህሮን ወጥነት ለመጠበቅ ራሳቸውን የሚሰጡ አጥቢያዎች በዚህ በጋራ ባወጡት የዲኖሚኔሽን የእምነት አንቀጽና ደንብ የማደር ግዴታ አለባቸው።

# ምዕራፍ ሰባት

## የማኅበረ ምዕመናንና የሽማግሌዎች ኀላፊነት

በኢትዮጲያ ቤተክርስቲያን ውስጥ በማንነት ላይ የተመሠረተ ልዩነት የለም። በምዕመናን መ ከል አገልግሎታዊ እንጂ ማንነታዊ ልዩነት የለም። በጌታ ፊት ሁሉም አማኝ እኩል ነው። በጌታ የተገኘው ቤዛነት በወንድና በሴት እንዲሁም በማንነት ላይ የተመሠረተ ልዩነትን አስወግዷል። ይህ ማለት ግን አገልግሎታዊ ልዩነት የለም ማለት አይደለም። ምዕመናን በጌታ ፊት ያላቸው እኩልነት የአገልግሎት ድርሻቸውን የሚያጠፋ አይደለም። በሌላ አነጋገር በምዕመናን መካከል በማንነትና በጸታ ላይ የተመሠረተ ልዩነት አይኑር እንጂ በአገልግሎት ላይ የተመሠረተ ልዩነት አለ (1ቆሮ 12፥4-11)።

እያንዳንዱ አማኝ የአገልግሎት ድርሻ አለው። ቤተክርስቲያን አንዱ የሌላውን ሌላውም የአንዱን መንፈሳዊ ሕይወት የሚያሳድግበት ቦታ ነች። በሌላ አነጋገር የሌላውን አማኝ መንፈሳዊ ድጋፍ የማይሻ አማኝ የለም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የአማኞችን የእርስ በርስ አስፈላጊነት አስመልክቶ አያሌ መለኮታዊ ትእዛዞች አሉ። ከእርስ በርስ ስምምነት አንስቶ እስከ እርስ በርስ መዋደድና መተናነጽ ድረስ በክርስቶስ የተገኘውን አንድነት መግለጽ አስፈላጊ ስለመሆኑ በተደጋጋሚ ተወስቷል (1ጴጥ 3፥8)። ክርስትና ግለኝነትን ሳይሆን ማኅበረሰባዊነትን የሚያጠብቅ እምነት ነው። በእርግጥ እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱ የሆኑ ልዩ ባህርያት አሉት። ነገር ግን እነዚህ ተፈጥሮአዊና ሥነ-ልቦናዊ ባህርያት ማኅበራዊ ሕይወትን የሚያስከዱ ሳይሆን በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ የራስን ድርሻ ለመወጣት የሚረዱ ናቸው። አንዱ ሌላውን ይረዳል፥ ሌላውም አንዱን ይደግፋል። በጥቅሉ የእርስ በርስ መተባበር አለ ማለት ነው (1ቆሮ 12፥12-27)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በክርስትና ውስጥ በኅብረት የመደጋገፍ ሕይወት መኖሩን ያሳየው "አሌሎን" (እርስ በርስ) የሚለውን የግሪክ ቃል ደግሞ ደጋግሞ በመጠቀም ነው። ሐዋርያው ክርስቲያናዊ ኑሮ ሁሉ "አሌሎን" እንደሆነና ነገር ሁሉ "አሌሎን" ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያለ መሰልቸት አስታውቋል።

እርስ በርሳችን ተገጣጥመናል እያንዳንዳችንም የሌላው ብልቶች ነን (ሮሜ 12፥5፤ኤፌ 4፥25)። የተጠራነውም እርስ በርስ ለመተናነጽ (1ተሰ 5፥11፤ ሮሜ 14፥19) ፤ እርስ በርስ ለመተሳሰብ (1ቆሮ 12፥25)፤ እርስ በርስ ለመዋደድ (1ተሰ 3፥12፤ 4፥9፤ 2ተሰ 1፥3፤ ሮሜ 13፥8) ፤እርስ በርስ ለመቻቻል (ኤፌ 4፥2)፤ እርስ በርስ ለመከባበር (ፊል 2፥3፤ ሮሜ 12፥10)፤ እና እርስ በርስ ለመረዳዳት (ገላ 6፥2) ነው። ሆነን እንድንገኝ የተመረጥነውም እርስ በርስ መልካም ነገር ለማድረግ (1ተሰ 5፥15)፤ እርስ በርስ ራስን ለማስገዛት (ኤፌ 5፥21)፤ እርስ በርስ በአንድ አሳብ ለመስማማት (ሮሜ 12፥16) እና እርስ በርስ ይቅር ለመባባል እንዲሁም እርስ በርስ ደጎችና ርኅሩኆች ለመሆን ነው (ኤፌ 4፥32፤ ቆላ 3፥13)። እንግዲህ በክርስትና ውስጥ የተናጠል ሕይወት የሌለው ክርስትና "የእርስ በርስ" (የ"አሌሎን") ኑሮ በመሆኑ ነው። ምዕመናን የመሪዎችን አገልግሎት እንደሚሹ ሁሉ መሪዎችም የምዕመናንን አገልግሎት ይሻሉ። በጥቅሉ መሪዎች ኀላፊነት እንዳለባቸው ሁሉ ምዕመናንም ኀላፊነት አለባቸው። ከዚህ በታች በዝርዝር የምንመለከተውም ይሄንኑ ጉዳይ ይሆናል። በቅድሚያ የምንመለከተው "ማኅበረ ምዕመናን ለሽማግሌዎች ያላቸው ኀላፊነት ምንድንነው?" የሚለውን ጉዳይ ነው።

### 7.1 የማኅበረ ምዕመናን ኀላፊነት ለሽማግሌዎች

በምዕመናንና በሽማግሌዎች መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት አስመልክቶ ሐዋርያው ጳውሎስ ሰፊ መግለጫ ሰጥቷል። እንደ ሐዋርያው አባባል ምዕመናን ሽማግሌዎችን "የማወቅ"፥ "የማክበር" እና "የመታዘዝ" ኀላፊነት አለባቸው። ሐዋርያው እንዲህ ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ እንመለከታለን።

### 7.1.1 ሽማግሌዎችን የማወቅ ኀላፊነት

ጳውሎስ የተሰሎንቄ ቤተክርስቲያንን ሲያሳስብ "በመካከላችሁ የሚደክሙትን ...ታውቁ ዘንድ ስለ ሥራቸውም... ታከብሯቸው ዘንድ እንለምናችኋለን " (1ተሰ 5÷12) ብሏል:: ሐዋርያው በጌታ ሥራ የሚደክሙትን "እወቋቸው" ሲል ትኩረት ስጧቸው÷ ሥራቸውንና ድካማቸውንም ቁጠሩላቸው ማለቱ ነው [1]:: እነዚህ አገልጋዮች ስለ ማኅበረ ምዕመናኑ መንፈሳዊ ሕይወት ሲሉ ብዙ የሚደክሙና የሚጋደሉ ናቸው:: በመሆኑም አስፈላጊና ጠቃሚ አገልጋዮች እንደሆኑ በመገንዘብ በጸሎት መደገፍና በአክብሮት ልንመለከታቸው ይገባል:: ለእነዚህ ሰዎች ይህን ያህል አክብሮት መስጠት ያስፈለገበት ሦስት ምክንያቶች እንዳሉ ጳውሎስ ቀደም ሲል በጠቀስነው ክፍል ውስጥ አስታውቆአል:: ይኸውም ሽማግሌዎች 1) የሚደክሙ (2) የሚገዙ (የሚያስተዳድሩ) (3) የሚገሥጹ ናቸው::

አንደኛው የሽማግሌዎች ተግባር ሠራተኛነት ነው:: በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ ከትጉነት ውጪ ውጤታማነት ሊገኝ አይችልም:: የመሪነት ቦታ የክብር ቦታ ሳይሆን የታታሪነት ቦታ ነው:: የዚህ ቦታ ክብር የሚገኘው በሽማግሌዎቹ ማንነት (ዕድሜ ÷ ሀብት÷ ዕውቀት) ሳይሆን በሽማግሌዎቹ ትጉነትና ታታሪነት ነው:: "የሚደክሙ" (የሚሠሩ) የሚለው ቃል "ኮፒዮንታስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው:: ፍቺውም "በሥራ ብዛት ከሚገባው በላይ መድከም ወይም መዛል" ማለት ነው:: የአመራር ቦታዎች ሁሉ አድካሚ ከመሆናቸውም በላይ መሥዋዕትነትንም የሚጠይቁ ናቸው:: እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባው ነጥብ እነዚህ ሽማግሌዎች ይሄን ያህል የሚደክሙት ለራሳቸው ጉዳይ ሳይሆን ለሚያገለግሉት ምዕመናን መሆኑን ነው::

ሁለተኛው የሽማግሌዎች ተግባር መሪነት ነው:: "የሚገዙአችሁ" (አለቆቻችሁ) የሚለው ቃል "ፕሮይስታሜኑስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተመለሰ ሲሆን ጥሬ ትርጉሙ "መሪ ወይም ቀዳሚ መሆን" ማለት ነው:: ይሄው ቃል በሮሜ 12÷8



ላይ "የሚገዛ በትጋት ይግዛ" ተብሎ ተተርጉሞአል:: ብዙውን ጊዜ መሪነትን የምናያይዘው ከኀላፊነት ጋር ሳይሆን ከሥልጣን ጋር ነው:: አገልግሎቱ ከሚጠይቀው ትጉነት ጋር ሳይሆን ከክብር ጋር ነው:: በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ግን እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ቦታ ሊሰጠው አይገባም:: ምክንያቱም ትክክለኛ መሪ "በጌታ የሚመራ ወይም የሚገዛ" ነው:: መሪነት ተንከባካቢነት እንጂ ተጋፊነት አይደለም:: ጳውሎስ "ታውቋቸው" ደግሞም "ታከብሯቸው" ዘንድ ይገባል ያለበት ምክንያት ያለ እረፍት የሚደክሙና የሕዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት ለማሳደግ ሲሉ ዘወትር ከኃጢአትና ከሰይጣን ጋር የሚጋደሉ በመሆናቸው ነው:: እውቅናም ሆነ አክብሮት የሚሰጣቸው ከዚህ አኳያ እንጂ የቤተክርስቲያን መሪ በመሆናቸው ብቻ አይደለም::

ሦስተኛው የሽማግሌዎች ተግባር መካሪነት ነው:: ሽማግሌዎች ትክክለኛውን መንገድ በማሳየትና በትክክለኛውም መንገድ ላይ በመምራት ብቻ ሳይሆን በመገሠጽም የሚደክሙ ናቸው:: መገሠጽ (ኖተቲአ) አንድም ማስጠንቀቅ ወይም መምከር ሊሆን ይችላል:: "ኖተቲአ" ለሚለው የግሪክ ቃል አቻ የአማርኛ ቃል ባይኖርም ዋና አሳቡ ግን አስፈላጊውን ምክርና ማሳሰቢያ መስጠት ማለት ነው:: እንዲሁም ሰዎች ወደ ተሳሳተ አመለካከትና አኗኗር እንዳይሄዱ ማስጠንቀቂያ መስጠት ማለትም ይሆናል:: ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶን ሽማግሌዎች÷ ማኅበረ ምዕመናኑን በሚገባ የመጠበቅና የመንከባከብ ኀላፊነት እንዳለባቸው ሦስት ዓመት ሙሉ ቀንና ሌሊት እንባውን እያፈሰሰ ሲገሥጻቸው (ሲመክራቸውና ሲያስጠነቅቃቸው) ነበር (የሐዋ 20÷28-31):: እንግዲህ ሽማግሌዎች በመንፈሳዊ ነገር ሊያበለጽጉን የቆሙ አገልጋዩች በመሆናቸው አክብሮት ይገባቸዋል:: ጳውሎስም እንዲህ ዓይነት አገልጋዮችን "ታውቁ ዘንድ" ደግሞም "ታከብሯቸው ዘንድ" ይገባል ያለው ስለ እኛ ሲሉ ዘወትር ስለሚጋደሉና ስለሚደክሙ ነው:: የሚተጉ÷ የሚመሩና የሚመክሩ(የሚገሥጹ) ሽማግሌዎች አክብሮት ይገባቸዋል::

### 7.1.2 ሽማግሌዎችን የማክበር ኀላፊነት

ሽማግሌዎች ክብር የሚገባቸው ለምንድነው? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል:: ጳውሎስ ለዚህ ጥያቄ መልስ አለው:- "በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት እጥፍ ክብር ይገባቸዋል:: መጽሐፍ የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሠር፥ ደግሞም ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል ይላልና" (1ጢሞ 5፥17-18):: ይህ ጥቅስ ለሽማግሌዎች ሊሰጥ ስለሚገባው ክብር ከፍተኛውን አስተያየት የያዘ ነው:: እንደ ጳውሎስ አገላለጽ ሽማግሌዎች ክብር የሚገባቸው:- (1) በመልካም የሚያስተዳድሩ እንዲሁም (2) በመስበክና በማስተማር የሚደክሙ በመሆኑ ነው:: እነዚህን ሁለት ምክንያቶች በየተራ እንቃኛለን::

አንደኛው በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ክብር ይገባቸዋል:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ በመሆናቸው ብቻ ክብር እንዲሰጣቸው የተነገረ ምንም ትእዛዝ የለም:: ሽማግሌነት በራሱ ክብር አያስገኝም:: በመልካም ወይም እንደሚገባ የማያስተዳድር ሽማግሌ ለዚህ ክብር የተገባ አይደለም:: ሽምግልና ጥሩ ሥልጣን የሚገኝበት ቦታ ሳይሆን ጥሩ አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ ነው:: በሌላ አነጋገር ሽምግልና የሥልጣን ቦታ ሳይሆን የአገልግሎት ቦታ ነው:: የኀይል ቦታ ሳይሆን የሥራ ቦታ ነው:: እናም ሽማግሌ አዛዥ ሳይሆን አድራጊ ነው:: ሽምግልናን ከዚህ ውጪ ማሰብ ትልቅ ስህተት ነው:: ሐዋርያው "ክብር" ይገባቸዋል ያለው በሚገባ ወይም በመልካም ለሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች እንጂ ኀይልና ሥልጣን በአይነ-ኀሊናቸው ውስጥ ብዥ-ብዥ የሚልባቸውን አይደለም:: በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሥልጣንን መለማመጃ ምንም ቦታ የለም:: ለመሆኑ ያ "እጥፍ ክብር" ምንድነው? በሁለተኛው ምክንያት ውስጥ የሚመለስ ጥያቄ ይሆናል::

ሁለተኛው በመስበክና በማስተማር የሚደክሙ ሽማግሌዎች ክብር ይገባቸዋል:: መስበክና ማስተማር ተቀራራቢ ይዘት ቢኖራቸውም ልዩነትም አላቸው:: ልዩነቱ



ግን ጉልህ አይደለም:: ሰበከ ማለት ነገረ፥ አስታወቀ፥ አስጠነቀቀ ማለት ነው:: ሽማግሌዎች የጌታን ቃል በመስበክ ሰዎችን አማኝ ወይም የጌታ ተከታይ ያደርጋሉ:: የስብከት ዋና ዓላማም የአድማጭን ልቡና መለወጥ ነው:: አስተማረ ማለት ገለጠ፥ አስታወቀ፥ አስረዳ ማለት ነው:: ሽማግሌዎች የጌታን ቃል የሚያስተምሩት አማኞች የመጻሕፍትን ምስጢር በሚገባ እንዲረዱና በዚያ መረዳት ላይ ጸንተው እንዲቆሙ ለማገዝ ነው:: ዋና አላማውም የአማኞችን አኗኗር መለወጥ ነው:: ሽማግሌ የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክና በማስተማር ዘወትር ትጉ ሊሆን ይገባል:: ወንጌልን በመስበክና በማስተማር የሚደክም ሽማግሌ "እጥፍ ክብር" ይገባዋል:: "እጥፍ ክብር" የሚለው ሐረግ "ዲፕሎስ ታይሜ" ከሚለው የግሪክ ሐረግ የተተረጎመ ሲሆን አውደ ንባባዊ ፍቺው "ሁለት ነገር ማለትም ክብርና ደመወዝ" ማለት ነው 2::

መስበክም ሆነ ማስተማር አድካሚ ተግባር ከመሆኑም በላይ ዘወትር ትጉኅትንና ጊዜን የሚጠይቅ አገልግሎት ነው:: ሐዋርያው እጥፍ-ክብር አንድም ጥሩ ክብር ደግሞም ጥሩ ደመወዝ-ይገባቸዋል ያለው አገልግሎቱ የሚጠይቀውን መሥዋዕትነት በየዕለቱ ለሚከፍሉ ሽማግሌዎች ነው:: የእግዚአብሔር ቃል በመስበክና በማስተማር የሚደክሙ አገልጋዮችን (ሽማግሌዎችን) በነገር ሁሉ መደገፍ አስፈላጊ መሆኑን በጥብቅ ያሳስባል (ሉቃ 10፥7፤ 1ቆሮ 9፥4-10):: በመንፈሳዊ ነገር የሚያሳድጉን ሽማግሌዎች አክብሮት ብቻ ሳይሆን እንክብካቤም ያስፈልጋቸዋል:: ይህንንም ማድረግ ደግሞ የማኅበረ ምዕመናን ኀላፊነት ነው::

### 7.1.3 ሽማግሌዎችን የመታዘዝ ኀላፊነት

ማንኛውም ክርስቲያን ስለ ታዛዥነት በቂ ዕውቀት ሊኖረው ያስፈልጋል:: በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ ታዛዥነት ትልቅ ቦታ አለው:: በአንዳንድ ቦታዎች ላይ እንደሚታየው ታዛዥ መሆን ማለት የበታች መሆን ማለት ይመስላል:: እውነቱ ግን እንዲህ አይደለም:: እግዚአብሔር ባስቀመጠው አሠራር ውስጥ ታዛዥነት የመለኮት ፈቃድ መከናወኛ

ዓይነተኛ መንገድ ነው። ወልድ፥ አብን የታዘዘው ከአብ ስለሚያንስ ሳይሆን የአብን በጎ ፈቃድ ለመፈጸም ነው (ዮሐ 4፥34፤ ፊል 2፥5-9)። የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን መታዘዝ ያለብን እነሱ ስላሉን ሳይሆን እግዚአብሔር ስላለን ነው [3]። በዚህ ጉዳይ ላይ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ሲናገር "ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት፥ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ" (ዕብ 13፥17) ብሏል። እንደዚህ ቃል አባባል ሽማግሌዎችን መታዘዝ ያለብን ስለ ሁለት ምክንያቶች ነው።

አንደኛው ሽማግሌዎች የሚጠየቁበት ኀላፊነት ስላለ ነው። መንፈሳዊ ሕይወታችን ጤነኛ እንዲሆንና በጌታ ላይ ጽኑ እምነት እንዲኖረን ሁልጊዜ ይደክማሉ። ውስጣዊ አመለካከታችን ፍጹም እስኪጠራ ድረስ ያለ እረፍት ይሠራሉ። ይህንንም የሚያደርጉት አንድ ቀን እግዚአብሔር ስለሚጠይቃቸው ነው። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ "ታዘዙ" ያለን "ስለነፍሳችን ጉዳይ ለሚተጉ" ሽማግሌዎች ነው [4]። የሽምግልናን አገልግሎት ከሥልጣን ጋር ማያያዝ ተገቢ አይደለም ያልነው፥ በኀላፊነት የሚያስጠይቅ ጉዳይ በመሆኑ ነው። "ይተጋሉ" የሚለው ቃል "አግሪፕኔኦ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው። ፍቺውም፥ "ለሥራ የማይተኛ፥ የማይደክም ወይም የማይታክት " ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ "አግሪፕኔኦ" ማለት ያለ ስንፍና ሥራውን በትጋት የሚያከናውንና ሁልጊዜ ነቅቶ የሚጠብቅ ማለትም ነው። ሽማግሌ ልክ እንደ ከተማ ጠባቂ ወይም እንደ እረኛ የእግዚአብሔርን መንጋ ነቅቶ መጠበቅ አለበት። ሐሰተኛ መምህራን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ እጅግ በተበራከቱበት ሰዓት ምዕመናን በአግባቡ ሊጠበቁ ይገባል። ለአፍታ ያህል የተዘናጋ ሽማግሌ በመንጋው ላይ የሚያደርሰው ጉዳት እንዲህ በቀላሉ የሚገመት አይሆንም። ይህን ኀላፊነት በቅጡ ሳይፈጽም የቀረ ሽማግሌ በእግዚአብሔር ተጠያቂ ነው። ራሱ ጳውሎስ እግዚአብሔር ለሰጠው መንጋ ተጠያቂ እንደ ሆነ ሲገልጽ፡- "...እኔ ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ እንደሆንሁ ዛሬ በዚች ቀን



እመሰክርላችኋለሁ። የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነገሬአችኋለሁና፥ ምንም አላስቀረሁባችሁም" (የሐዋ 20፥26-27) ብሏል።

ሁለተኛው ሽማግሌዎች ሥራቸውን በደስታ ማከናወን እንዲችሉ ነው። በእርግጥም የሰዎች ሕይወት ሲለወጥ ማየት ታላቅ ደስታ ነው። አንድ ወቅት ላይ ይህን ደስታ በሕይወት ዘመኑ ያየው ዮሐንስ "ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለኝም" (3ዮሐ 4) ያለበት ትልቅ ምክንያት አለው። ይኸውም፥ እያንዳንዱ መሪ የአገልግሎት ፍሬውን በማየት የሚገኘውን ደስታ የመናፈቅ መብት አለው (2ቆሮ 2፥3፤ ፊል 2፥16፤ 1ተሰ 2፥20)። ነገር ግን ይህ ደስታ እውን የሚሆነው "ታዛዥነት" ሲኖር ነው።

እንደሚገባ ለሚያገለግሉ ሽማግሌዎች ምላሹ "እሺታ" እንጂ "እምቢታ" መሆን የለበትም። የዚህ ተቃራኒ በሚሆንበት ጊዜ ግን ሁልጊዜ ሐዘን ይከሰታል። ለዚህም ነው፥ የዕብራውያን ጸሐፊ ሥራቸውን በሐዘን እንዳይሠሩ ታዘዙአቸው ሲል የመከረን። "ሐዘን" የሚለው ቃል "ስቴናዞንቴስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ሲሆን ፍቺውም "በሐዘን ብዛት ማልቀስ ወይም ጥልቅ የልብ ስብራት" ማለት ነው። ለጌታ እውነት ግድ የለሽ መሆን ሽማግሌዎችን እጅግ ያሳዝናል። እዚህ ላይ ሙሴንና ጳውሎስን ለአብነት ያህል መጥቀሱ በቂ ነው። የእስራኤላውያንን አመጸኝነት መሸከም ያቃተው ሙሴ ሞቱን የመረጠበት ወቅት ነበር፤ "እጅግ ከብዶኛልና ይህን ሁሉ ሕዝብ ልሸከም አልችልም። እንዲህስ ከምታደርግብኝ፥ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ፥ በእኔ ላይ የሚሆነውን መከራ እንዳላይ፥ እባክህ ፈጽሞ ግደለኝ" (ዘኁ 11፥14-15)። ሐዋርያው ጳውሎስ ከመሠረታቸው ቤተክርስቲያኖች ውስጥ የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያንን ያህል የጳውሎስን ልብ የሰበረው የለም። የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የጳውሎስን ሐዋርያነት ብቻ ሳይሆን ወንጌሉንም ጭምር አቃላለች (2ቆሮ 2፥4፤ 19፥7-14፤ 11፥1-33)።

እንግዲህ ሕይወታቸውን ሁሉ ለጌታ አገልግሎት የሰጡ መሪዎችን ማሳዘን ምንኛ ክፉ ነገር እንደ ሆነ የሙሴና

የጳውሎስ ሕይወት ምስክር ነው። እንደሚገባ የማያገለግሉ ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ተጠያቂ እንደ ሆኑ ሁሉ ሽማግሌዎቻቸውን የሚያሳዝኑ ምዕመናንም በእግዚአብሔር ተጠያቂ ናቸው። የዕብራውያን ጸሐፊ መሪዎችን ማሳዘን "እናንተን የሚጠቅም አይሆንም" ሲል "የሚጎዳችሁ ነው" ወይም "አደገኛ ነገር የሚያስከትልባችሁ ነው" ማለቱ ነው። ጸሐፊው አዎንታዊ ነገርን ለመግለጽ አዎንታዊ ቃላትን ከመጠቀም ይልቅ አሉታዊ ቃላትን ነው የተጠቀመው። እንዲህ ዓይነቱ የአጻጻፍ ዘዬ "ጠምዛዜ" (Litotes) በመባል ይታወቃል [5]። ለምሳሌ "ግሩም ሥራ ነው" ከማለት ይልቅ "መጥፎ ሥራ አይደለም" ብንል አዎንታዊ ነገርን በአሉታዊ ነገር መግለጻችን ነው። የዕብራውያንም ጸሐፊ ያደገረው ልክ እንዲሁ ነው [6]። ሽማግሌዎች አገልግሎታቸውን በደስታ መፈጸም ይችሉ ዘንድ ምዕመናን በጎ ምላሽ ሊሰጧቸው ይገባል። በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ አገልግሎታዊ ታዛዥነት መቼም መጥፋት የለበትም። አልያ ግን መንፈሳዊ በረከት መጓደሉ የማይቀር ይሆናል።

ሽምግልና ቀላል አገልግሎት አይደለም። ይልቁንም አያሌ መሥዋዕትነት ያለበት አገልግሎት ነው። የጌታን ሕዝብ በነገር ሁሉ በሳል ለማድረግ የራስን ነገር መተው ያስፈልጋል። በዚህ ዘመን ስለ ሽምግልና ያለው አስተሳሰብ ግን ከዚህ ፈጽሞ የተለየ ነው። አንዳንዶች ሽምግልናን የሚመለከቱት በቤተክርስ ቲያን ውስጥ ታዋቂና ዝነኛ የሆኑ ሰዎች የሚይዙት ሥፍራ አድርገው ነው። ሌሎች ደግሞ የሥልጣንና የኀይል ቦታ አድርገው ነው። ሽምግልና በጌታ ቤት ብዙ ዘመን ለኖሩ ሰዎች የሚሰጥ ሹመት አድርገው የሚገምቱም ብዙ ናቸው። ነገር ግን አዲስ ኪዳናዊ ንባባት የሚያመለክቱን የዚህን ተቃራኒ ነው። ሽማግሌ የምዕመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ለማሳደግ ሲል ዘወትር የሚደክም ነው (1ተሰ 5፥12)፤ በመምከርና በማስተማር በየዕለቱ በሚጋደል ነው (1ጢሞ 5፥17-18)፤ ይህንን ሳያደርግ ቢቀር ደግሞ በእግዚአብሔር የሚጠየቅ ነው (ዕብ 13፥17)። እንግዲህ፥ ምዕመናን ሽማግሌዎችን የማወቅ፥ የማክበርና የመታዘዝ ኀላፊነት ያለባቸው አገልግሎቱ ከባድና አድካሚ በመሆኑ ነው። በአንድ



አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ የአንድ አቅጣጫ ኀላፊነት ብቻ (ሽማግሌዎች ለምዕመናን) ሳይሆን ያለው የሁለት አቅጣጫ ኀላፊነት ነው። ሽማግሌዎች ምዕመናንን እንደሚገባ የመጠበቅና የመመገብ ኀላፊነት እንዳለባቸው ሁሉ ምዕመናንም ሽማግሌዎችን የማክበርና የመታዘዝ ኀላፊነት አለባቸው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ይህ የሁለት አቅጣጫ ኀላፊነት ሊታጣ አይገባም። ስለዚህ ሽማግሌዎችን ማክበርና መታዘዝ የሚያስፈልገው ራስን ዝቅ በማድረግና እርስ በርስ በክርስቶስ ፍርሃት በመገዛት መሥራት ለሁሉም አማኝ የተሰጠ ኀላፊነት በመሆኑና ለየግል ሕይወትም መታነጽ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

## 7.2 የሽማግሌዎች ኀላፊነት በቤተክርስቲያን

ቀደም ሲል ለማስገንዘብ እንደሞከርነው ሽምግልና አገልግሎት ነው። ጌትነት ሳይሆን ባርነት ነው፤ ነገሩን በሚገባ እናስብበት ካልን ሽምግልና በሁሉ ነገር መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ መንፈሳዊ ተልዕኮ ነው። ሽማግሌዎች ምዕመናንን በሚገባ መጠበቅና መንከባከብ፤ እንዲሁም ቤተክርስቲያንን በሥርዓት ማስተዳደርና መምራት ይኖርባቸዋል። ሽማግሌዎች ምዕመናንን ወይም ቤተክርስቲያንን ያስተዳድራሉ፥ ይጠብቃሉ፥ ይመግባሉ። ቀጥለን የሽማግሌዎችን ኀላፊነት አንድ በአንድ ለማየት እንሞክራለን።

### 7.2.1 ሽማግሌዎች ቤተክርስቲያንን ያስተዳድራሉ

ቤተክርስቲያንን ማስተዳደር ወይም በአግባቡ መምራት አንደኛው የሽማግሌዎች ኀላፊነት እንደሆነ አዲስ ኪዳን በግልጽ ያስተምራል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕዝቡ ነፍስ "እረኛና ጠባቂ" (በግሪክ "ቶን ፓይሜና ካይ ኤፒስኮፖን") እንደ ሆነ ሁሉ (1ጴጥ 2፥25) ሽማግሌዎችም የምዕመናንን ነፍስ የመጠበቅ ኀላፊነት አለባቸው። በ1ጢሞ 5፥17 ላይ እንደምናነበው "በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች፥ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት፥ እጥፍ

ክብር ይገባቸዋል":: በዚሁ መልእክት ላይ ጳውሎስ ኤጲስቆጶሳትን አስመልክቶ ሲጽፍ ኤጲስቆጶስ "ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር" መሆን ይገባዋል፤ ...የራሱን ቤት እንዲያስተ ዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?" በማለት ሁነኛ ጥያቄ ያነሳበት ምክንያት አለው:: "በመልካም የሚያስተዳድሩ" የሚለው ቃል "ፕሮይስቴ ማይ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ሲሆን ፍቺውም "ተጠንቅቆ የሚያስተዳድር ወይም ተንከባክቦ የሚመራ" ማለት ነው[7]::

እንደ ሐዋርያው አባባል የቤቱን ኀላፊነት በትክክል ያልተወጣ ሰው ቤተክርስቲያንን ለማስተዳደር የተገባ አይደለም:: ምክንያቱም የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ መሆን ማለት የቤተክርስቲያን አለቃ ወይም ገዢ መሆን ማለት አይደለም-ለመንጋው ምሳሌ በመሆን መንጋውን የሚጠብቅ ማለት እንጂ:: በዚሁ አቅጣጫ ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲጽፍ "... በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ" (1ጴጥ 5፥1-3) ብሏል:: ሽምግልና በባህሪው ምንጊዜም የአለቅነት መንፈስ (ስሜት) የለበትም:: ይልቁንም የጌታን ሐሳብ የተከተለ እንጂ:: በጌታ ደቀመዛሙርት መካከል "የታላቅነት" ጥያቄ በተነሳ ጊዜ ኢየሱስ የሰጠው መልስ "ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ፥ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን" (ሉቃስ 22፥26) የሚል ነበር:: እንግዲህ ሽምግልና "እንደ አገልጋይ መሆን" የሚለውን መርህ የሚከተል ነው:: የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ከዚህ መርህ ውጪ ለማስተዳደር መሞከር ትልቅ ስህተት ነው:: ጌታ ኢየሱስ እንዳለው በሰዎች ላይ መሠልጠን (ሉቃስ 22፥25) የዚህ ዓለም ነገሥታት መለያ ነው:: ሽምግልና ግን እንዲህ አይደለም:: የነገሮች ሁሉ ባለቤት የሆነው ጌታ "እኔ ግን በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ" (ሉቃ 22፥27) ባለው ተመርሆ የሚመራ ነው::



በመሠረቱ ሽምግልና "የአገልጋይነትን ተመርሆ መከተል አለበት" የተባለው ነገሩን በጣም መንፈሳዊ ለማድረግ ታስቦ አይደለም:: በሽምግልና አገልግሎት ዓለም ሁሉ እንዲደሰት ለማድረግ ቢታሰብ ኖሮ መንገዱ ይህ አልነበረም:: ነገር ግን የክርስትና መሠረት ክርስቶስ ኢየሱስ ከሆነ፥ ክርስቲያናዊ አገልግሎቶች ሁሉ የሚመራኮዙት እሱ ትቶልን በሄደው ተመርሆ (principle) ላይ ነው:: እሱ "እንደ አገልጋይ ሆኖ" እንዳገለገለው ዓይነት እኛም እንዲሁ እንድናገለግል ይህ መለኮታዊ ተመርሆ ተሰጥቶናል:: ጌታ "በመካከላችሁ እንደ አገልጋይ ነኝ" ካለ እሱ እንደ ሆነው ከመሆን ወዲያ ሌላ አማራጭ የለንም::

ቤተክርስቲያንን ለማስተዳደር ኀላፊነት የተቀበሉ ሽማግሌዎች ሁሉ ይህን ኀላፊነት መፈጸም ያለባቸው በዚህ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመርሆ መሠረት ነው:: ከዚህ ተመርሆ የወጣ አስተዳደር ሥጋዊ ምኞትን እውን ለማድረግ ካልሆነ በቀር ለማንም አይጠቅምም:: ይህም በመጀመሪያ ክርስቶስን ቀጥሎም ምዕመናንን የሚጎዳ ይሆናል:: እዚህ ላይ ክርስቶስ ይጎዳል ሲባል ÷ የሆነ ነገር ያጣል ማለት አይደለም:: ክርስቲያናዊ አገልግሎቶች ሁሉ እንዲመሩበት ያስቀመጠው ምሳሌያዊ ሕይወት ተከታይ ሲያጣ ያዝናል ማለት እንጂ:: እንዲሁም ምዕመናን ይጎዳሉ ሲባል ትክክለኛ መንፈሳዊ ዕድገት ከመጥፋቱ የተነሣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ክርስቶሳዊ ሕይወት ይጠፋል ማለት ነው:: እንዲህ ዓይነቱን ውድቀት ማስቀረት የሚቻለው በክርስቶስ የሕይወት ምሳሌነት መመላለስ ሲቻል ብቻ ነው::

### 7.2.2 ሽማግሌዎች ምዕመናንን ይጠብቃሉ

ሽማግሌዎች ምዕመናንን የሚጠብቁት በበትር ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የመጨረሻ አስተያየቱን ሲሰጥ እንዲህ ብሎ ነበር "የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለ ሁና፥ ምንም አላስቀረሁባችሁም" (የሐዋ 20፥26-27):: ሐዋርያው ይህንን ያደረገው "ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን

እንባውን እያፌሰሰ ነው" (የሐዋ 20÷31)፡፡ ጳውሎስ የኤፌሶንን ሽማግሌዎች ያስጠራው ለስንብት ብቻ ሳይሆን እርሱ ለነርሱ የሆነውን ያህል እነርሱም "መንፈስ ቅዱስ ጳጳሳት (በግሪክ "ኤፒስኮፖስ") አድርጎ ለሾማቸው ምዕመናን " (የሐዋ 20÷28) እንዲሁ እንዲሆኑ ነው፡፡

ሽማግሌ መንጋውን መጠበቅ ያለበት ልክ እንደ እረኛ ሆኖ ነው፡፡ እረኛ የበጎቹን ማንነት ብቻ ሳይሆን የበጎቹንም ፍላጎት ያውቃል፡፡ የምዕመናን እረኛም ከዚህ የተለየ መሆን የለበትም፡፡ ሽማግሌ የምዕመናን እረኛ ነው ሲባል ምዕመናንን የሚጠብቅና የሚመራ ነው ማለት ነው፡፡ ሽማግሌ ምዕመናንን የሚጠብቀው "ለመንጋው ከማይራሩ እንደ ተኩላ ጨካኞች ከሆኑ ሰዎችና በመካከላቸው ጠማማ ትምህርት ከሚያስተምሩ ሐሰተኞች" ነው (የሐዋ 20÷29-30)፡፡ ሽማግሌ ምዕመናንን የሚመራው በጽድቅ መንገድና ወደ ጽድቅም ኑሮ ነው፡፡ ሽማግሌ ይህንን ሁሉ ማድረግ ያለበት " መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን በበጎ ፈቃድ" መሆን አለበት (1ጴጥ 5÷2)፡፡ በጎና ታማኝ ሽማግሌ (እረኛ) መንጋውን መጠበቅ ያለበት ስለ መንጋው ሲል ሕይወቱን አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ እንደሆነው መልካም እረኛ ነው (ዮሐ 10÷11-14)፡፡ ይህ መልካም እረኛ የእረኞች ሁሉ ምሳሌ ነው፡፡ ከዚህ ምሳሌነት የወጣ እረኝነት እግዚአብሔር የሚፈልገው ዓይነት እረኝነት አይደለም፡፡

እረኞች ምዕመናንን የሚጠብቁት በእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ከጌታ ኢየሱስ ንግግር መረዳት ይቻላል (ዮሐ 21÷15-17)፡፡ ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን ሁለት ጊዜ "መግብ" (ቁ 15 እና 17) አንድ ጊዜ ደግሞ "ጠብቅ" (በግሪክ "ፖይሜን" - መጋቢ ፤ ጠባቂ፥ ተንከባካቢ ፤ ቁ 16 ) ሲለው የሚመግበው ምንድነው? የሚጠብቀውስ በምንድነው? የሚል ጥያቄ ይነሳል፡፡ ከሀውደ ንባቡ እንደምንረዳው ጴጥሮስ የሚመግበው የእግዚአብሔርን ቃል ነው፡፡ የሚጠብቀውም በእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ የመንፈሳዊውን ዓለም ገጽታ በዚህ ዓለም እውነታ መመሰሉ ነው፡፡ ይህ ዐውደ ንባብ የሚያሳየን ይህን ካልሆነ ሌላ ምን ሊባል ይችላል? መቼም ጌታ ኢየሱስ፥



ጴጥሮስን ከዓሣ አጥማጅነት አውጥቶ "የበግ እረኛ" እንዳላደረገው ግልጽ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ነገር ቢኖር "ሰው አጥማጅ" አደርግሃለሁ ነው (ማቴ 4÷19)፡፡ እንደ ተባለውም ሕይወቱ በሮም እስካለፈበት ዕለት ድረስ እሱና የእግዚአብሔር ቃል ተለያይተው አያውቁም፡፡ ከቤተክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ጳውሎስ አንገቱን ተቀልቶ ሲሞት ጴጥሮስ ግን ተሰቅሎ ነው የሞተው፡፡ "እንደ ጌታዬ ሳይሆን ቁልቁል ዘቅዝቃችሁ ስቀሉኝ" ማለቱ በሞት ሰዓት ላይ እንኳን ክርስቶስ የንግግሩ ማዕከል መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ከአይሁዱ ዓለም ተነስቶ አሕዛቡ ዓለም እስኪደርስና በዚያም የሕይወቱ ማብቂያ እስኪሆን ድረስ የክርስቶስን ቃል ያስተምር ነበር፡፡ ክርስትና ያለ ክርስቶስ ሊቆም እንደማይችል ሁሉ ክርስቲያናዊ ሕይወትም ያለ እግዚአብሔር ቃል ሊቆም አይችልም፡፡ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ሊተጉ የሚገባውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ ተግባር የሚያፈገፍግ ሽማግሌ እንደ ሽማግሌ ሊቆጠር አይገባም፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር የሽማግሌዎች ቀዳሚ ኀላፊነት ነውና፡፡

### 7.2.3 ሽማግሌዎች ምዕመናንን ይመግባሉ

በዚህ ዘመን ስለ ሽማግሌዎች ተግባር ያለን አስተሳሰብ ከአስተዳደራዊ ተግባር ጋር ብቻ የተጎዳኘ ነው፡፡ እንዲያውም ሽማግሌዎች የተጠሩት ለአስተዳደራዊ ጉዳይ ብቻ የሚመስለን ብዙዎች ነን፡፡ በመሠረቱ እንዲህ ብናስብ ልንኮነን አይገባንም፡፡ ምክንያቱም ለአያሌ አመታት የተነገረን ልኩ ይሄ ነው ተብሎ ነው፡፡ ሁኔታውን ከአዲስ ኪዳን ትምህርት አኳያ ከተመለከትነው ግን ይህንን ብቻ አይደለም የምናገኘው፡፡ ጴጥሮስ በምን ሥልጣን እንደሚናገር አስቀድሞ ካስታወቀ በኋላ ሽማግሌዎችን ሲመክር "በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ" (1ጴጥ 5÷2) ብሏል፡፡ በዚህ ንባብ ላይ "ጠብቁ" የሚል ቃል ተጠቅሷል፡፡ ይህ ቃል "ፖይሜኖ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተመለሰ ሲሆን ትርጓሜውም "መጋቢ ወይም እረኛ" ማለት ነው፡፡ የዚህ ሐረግ ሰዋስዋዊ አወቃቀር እንደሚያስገነዝበን ይህ መጋቢነት ወይም

ጠባቂነት ከእረኝነት እስከ መሪነት እንዲሁም ከተንከባካቢነት እስከ አስተማሪነት ድረስ ያለውን ኀላፊነት ያጠቃልላል። እንደ ሐዋርያው አባባል ሽማግሌዎች እረኝነቱ የሚጠይቀውን ዋጋ ሁሉ መክፈል አለባቸው [8]።

የጴጥሮስ ምክር እጅግ አስፈላጊና ዘወትር ወቅታዊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች በበግ የመሰለው፥ በግ የሚመገበውና የሚጠብቀው እንደሚያስፈልገው ሁሉ የእግዚአብሔርም ሕዝቦች እንዲሁ የሚመግባቸውና የሚጠብቃቸው የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ማስገንዘብ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደ መንጋ የሚታዩ ከሆነ ደንበኛ እረኝነት ያሻቸዋል። ይህ እረኝነት ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል መመገብንና ከሐሰተኛ መምህራን መጠበቅን ያካተተ መሆን አለበት። ምዕመናን እረኝነት ያስፈልጋቸዋል ሲባል የማያቋርጥ ምግባና ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል ማለት ነው። ይህም በቅርብ ሆኖ ማበረታታትንና ማጽናናትን እንዲሁም ከክፉ ነገር መጠበቅንና ወደ በጎም ነገር መምራትን ይጨምራል።

ከዚህ የምንረዳው ሽማግሌዎች ምዕመናንን እንደሚገባ መንከባከብ ያለባቸው መሆኑን ነው። ዋናው ጥያቄ ግን እንዲህ ዓይነት እረኞች አሉን ወይ? የሚል ነው። እንደ ሃሳቡ የሚኖሩ እረኞች በጠፉበት ዘመን እግዚአብሔር በነቢዩ ሕዝቅኤል በኩል እንዲህ ብሎ ነበር፥ "ራሳቸውን ለሚያሰማሩ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው! እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን? ጮማውን ትበላላችሁ፥ ጠጉሩንም ትለብሳላችሁ፥ የወፈሩትንም ታርዳላችሁ፤ በጎቹን ግን አታሰማሩም። የደከመውን አላጸናችሁትም፥ የታመመውንም አላከማችሁትም፥ የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም፥ በኃይልና በጭቆናም ገዛችኋቸው። እረኛንም በማጣት... በጎቼ... ተቅበዝብዘዋል... ተበትነዋል፤ የሚሻም፥ የሚፈልግም አልነበረም" (ሕዝ 34፥2-6)። ይህ የሕዝቅኤል ትንቢት የዚህን ዘመን እረኞችንም (ሽማግሌዎችንም) ይመለከታል። የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የእግዚአብሔርን መንጋ የሚመግቡ፥ የሚጠብቁ፥ የሚያክሙ፥ የሚጠግኑ፥ የሚመልሱና የሚፈልጉ



ይገኙ ይሆን? ጥያቄውን በሽምግልና ለሚያገለግሉ ሁሉ የምንተወው ይሆናል።

ብዙ ጊዜ ስለ ሽምግልና ስናስብ እንዲህ እናስባለን። ሽምግልናን የምናያይዘው ምዕመናንን ከመመገብ፥ ከመጠበቅ፥ ከመጠገን ፥ ከመመለስና ከማከም ጋር ሳይሆን ከበጀት፥ ከገንዘብ፥ ከውሳኔ በጥቅሉ አስተዳደራዊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር ብቻ ነው። አዲስ ኪዳን የሚያስተምረን ግን የዚህን ተቃራኒ ነው። የአዲስ ኪዳን ሽማግሌዎች የምዕመናን እረኞች ናቸው። ለመንጋው የሚያስፈልገውን ጥበቃና ምክር የመስጠት ኀላፊነት አለባቸው፤ የመንጋውን ጥያቄና ጭንቀት የመፍታት አደራ አለባቸው፤ ከመንጋው ጋር የመንጋውን ሐዘንና ደስታ፥ መከራና ችግር፥ በጥቅሉ የመንጋውን ዕለታዊ ገጠመኝ አብሮ የመካፈል ጥሪ አለባቸው። እርግጥ ነው ሽማግሌዎች አጠቃላይ አመራርና አስተዳደር የመስጠት ኀላፊነት አለባቸው። ለምሳሌ የገንዘብ አወጣጥን፥ አባላትን ዲሲፕሊን ማድረግን፥ ማቀድን፥ ፕሮግራም መንደፍንና ሪፖርት ማድረግን የሚያጠቃልል ነው። ነገር ግን ይህ ኀላፊነት የሁሉንም ኀላፊነት ጠቅልሎ እስከ መያዝ የሚደርስ አይደለም።

ይህን እጅግ ታላቅ የሆነን መለኮታዊ አደራ እንደ ቀላል ነገር ማየት ተገቢ አይደለም። ሁኔታውን በቅን ልቦና ከተመለከትነው አያሌ ሽማግሌዎች ሽምግልናን የሚመለከቱት እንደ ቀላል አደራ ነው። በዚህም ምክንያት በርካታ የእግዚአብሔር ሰዎች ተመልካች አጥተው ሲባዝኑ ይታያል። እንዲህ መሰሉ ውድቀት በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚከሰተው ሽማግሌዎች ሽምግልናን እንደ ኀላፊነት ሳይሆን እንደ ልዩ ሹመት መቁጠር ሲጀምሩ ነው። ታዲያ እንዲህ ዓይነት ሽማግሌዎች ባሉበት ቦታ ምዕመናን ቢቅበዘበዙ፥ ተመልካች አጥተው ቢባዝኑ፥ መሪ አጥተው ውል ቢስቱ ምን ያስገርማል! መፍትሄው አንድ ነገር ብቻ ነው - ያም ሽምግልናን እንደ ሹመት ሳይሆን እንደ እረኝነት መመልከት ነው [9]።

የሽምግልናን ኀላፊነት በሚያስደንቅ ምሳሌ ያብራራው ጴጥሮስ፥ መቼም የማይዘነጋ አንድ መሠረታዊ ነጥብ

አንድ አማኝ የአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል መሆን ያለበት ለኅብረት ብቻ ሲባል ሳይሆን እርስ በርስ ለመተናነጽም ነው:: በአማኞች መካከል የእርስ በርስ መተናነጽ እንዲኖር መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ አማኝ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችን አድሏል:: የጸጋ ስጦታዎች የታደሉት ለግል ጥቅም ሳይሆን ለጋራ ወይም ለቤተክርስቲያን ጥቅም ነው:: እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱን ሥርዓት ያስቀመጠው በአማኞች መካከል መለያየት ሳይኖር የእርስ በርስ መተሳሰብና መረዳዳት እንዲኖር ለማድረግ ነው (1ቆሮ 12÷8-11፤ 21-26):: በመሆኑም አንዱ ሌላውን በማነጽ "እርስ በርሳችሁ ... ተጽናኑ" የሚለውን ትእዛዝ መፈጸም ተገቢ ነው (1ተሰ 4÷18፤ 5÷11፤ ሮሜ 1÷12)::

በሐዋርያት ዘመን ኅብረት ትልቅ ቦታ ነበረው:: የኅብረቱ ዋና ዓላማ ግን በአንድነት ጌታን ማምለክ ብቻ ሳይሆን እርስ በርስ መበረታታትና መተራረምም ነበር (የሐዋ 4÷25-32):: ዛሬ ግን የሚታየው ከዚህ በጣም የተለየ ነው:: የራስን ማንነት ማለትም ስም÷ ክብር÷ ዝና ከማሳየት ወዲያ ምንም ዓላማ የሌላቸው አገልጋዮች ቁጥር ጥቂት አይደለም:: የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ የሚታዩት ከዚህ አንጻር እንጂ ሌላውን አማኝ ለማገልገልና ለማነጽ ከሚደረግ ተጋድሎ ጋር አይደለም:: እናም የሌላውን አማኝ መንፈሳዊ ሕይወት ለማሳደግ የሚጥር ሰው ማግኘት ብርቅ ቢሆን ምንም አያስደንቅም:: ነገሩን አላስተዋልነውም እንጂ የጸጋ ስጦታዎችን እንደ ፈቀደ ለእያንዳንዱ አማኝ የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ ነው:: ስለሁኔታው ጳውሎስ ሲገልጽ:- "... ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል" (1ቆሮ 12÷11) ብሏል::

ምንም ያህል ለእግዚአብሔር ሥራ ተቆርቋሪ ብንሆንም÷ የጸጋ ስጦዎችን እኛ እንደ ፈለግን ማግኘት አንችልም፤ ደግሞም አይቻለንም:: ምክንያቱም ማን ምን ስጦታ እንዳለው የሚወስን እግዚአብሔር ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚሁ ጉዳይ በ1ቆሮ 12÷28 ላይ ሲናገር የስጦታዎች ደልዳይ እግዚአብሔር እንደሆነ በግልጽ



አስታውቆአል:: እንግዲህ ከሁሉም ብልጫ ያላቸው የሚመስሉንንና በሰው ፊት ታላቅ መስለው የሚታዩትን የጸጋ ስጦታዎች በብርቱ ለመፈለግ መጣር ከንቱ ድካም ነው:: ከሁሉም የሚያሳዝነው ግን "... አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ የሚገዛ በትጋት ይግዛ የሚምር በደስታ ይማር" (ሮሜ 12÷8) የሚሉትና ሌሎችም ስጦታዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ አለመታየቱ ነው:: ግን እኮ ማገልገልም ሆነ መለገስ÷ መምከርም ሆነ ምሕረት ማድረግ ወዘተ ... እንደ ሌሎቹ ሁሉ የጸጋ ስጦታዎች ናቸው:: ታዲያ የት አሉ እነዚህ የጸጋ ስጦታዎች ጥቅም ላይ የዋሉት? በጣት የሚቆጠሩ የጸጋ ስጦታዎች ላይ ብቻ የምናተኩር ከሆነ በእነዚህ የጸጋ ስጦታዎች በኩል የሚደርሰን የጌታ በረከት ቀርቶብናል ማለት ነው::

በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ሙሉ በሙሉ መቀበል እጅግ አዳጋች ሆኗል:: ዘመኑ "የእኔነት" ዘመን በመሆኑ÷ የእግዚአብሔር መንገድና አሠራር ተቀባይነት ሲያጣ በግልጽ ታይቷል:: ይህ አባባል ክርስቲያኖችን ሳይሆን ሌሎችን የሃይማኖት ክፍሎች የሚመለከት ነው እንል ይሆናል:: ነገር ግን የወቅቱ መንፈሳዊነት የሚያሳየን ይሄንኑ ነው:: የአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል ወይም አገልጋይ መሆን የመንፈስ ቅዱስ አሠራርን እንደ ማፈን ይቆጠራል የሚሉን ሰዎች ጥቂት አይደሉም:: የእኔነት ዘመን ከመግነኑ የተነሳ "ጌታ አዲስ የአሠራር መንገድ ሰጥቶኛል" ካላልን በስተቀር÷ መንፈስ ቅዱስ የራሱን መገለጥ ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስን ሲቃረን አንድም ጊዜ አልታየም:: አባባሉ ግን የራስን ስምና ዝና ለማስጠራት የሚደረግ ጥረት ነው:: አንድ አማኝ የአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል እንጂ የአብያተ ክርስቲያናት አባል ሊሆን አይችልም:: የአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባልነትን ለመሠረዝ የሚደረግ ሙከራ ሁሉ አግባብ አይደለም::

የአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል መሆን አስፈላጊ የሆነበት ሁለተኛው ምክንያት፥ ከልዩ ልዩ የስህተት ትምህርቶች መጠበቅ እንዲቻል ነው። ይህ ያለንበት ዘመን የፍጻሜ ዘመን ነው። በፍጻሜ ዘመን ደግሞ አያሌ የስህተት አስተማሪዎች እንደሚነሱ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ አድርጓል (2ተሰ 2፥7-12)። በአሁኑ ጊዜ ከ2500-5000 የሚደርሱ የስህተት ትምህርቶች ዓለማችንን አጥለቅልቀውታል [11]። ይህ አሀዝ የክርስትናን መሠረታዊ አስተምህሮ ፊት ለፊት የሚቃረኑትን ብቻ የሚያካትት መሆኑን ልብ ማለት ያሻል። ዛሬ ቤተክርስቲያንን የሚያሰጓት እነዚህ የስህተት ቡድኖች አይደሉም። ከዚህ ይልቅ ግን፥ እውነቱን ከሐሰት መለየት እስኪሳነን ድረስ የልዩነቱን ድንበር ያጠፉብን አያሌ የስህተት አስተማሪዎች ከበውናል። አስተምህሮአቸውም ሆነ ልምምዳቸው "ልዩ ወንጌልና" "ልዩ ክርስትና" ነው። ነገሩ ያልገባው አማኝ የትኛው ልክ፥ የትኛው ስህተት እንደሆነ መለየት ያቅተዋል። የእንዲህ ዓይነቱ አማኝ ዕጣ በትምህርት ነፋስ ወዲያና ወዲህ መፍገምገም ብቻ ነው። እንግዲህ የአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል መሆን የግድ የሚያስፈልገው፥ በሐሰት ትምህርት በመታለል ግራ የሚያጋባ አመለካከት ውስጥ ከመግባት ለመጠበቅ ነው።

እርግጥ ነው፥ ምዕመናን አጥቢያ ቤተክርስቲያናቸውን ትተው እንዲሄዱና የሌላ ቤተክርስቲያን ደንበኛ እንዲሆኑ የሚያስገድዷቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። አንደኛው ምክንያት መልካም እረኛ ማጣት ነው። ክርስቶስ በደሙ የዋጃቸውን ሕዝቦች እንደሚገባ የሚጠብቁና የሚንከባከቡ እረኞች እንደ ልብ የሌሉበት ዘመን ቢኖር ይህ ዘመን ነው። ዛሬ እረኝነት አገልግሎት መሆኑ ተረስቶ ሹመት ብቻ ሆኗል። አጋጣሚው አድሏቸው እንጂ አገልግሎቱ የሚጠይቀውን ችሎታና ልምድ በሚገባ አሟልተው የተሾሙ እረኞች ናቸው ለማለት ያስቸግራል። ለዚህ አባባል ትልቁ ምስክር፥ የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት ነው። አገልግሎቱ የሚጠይቀውን ችሎታና ልምድ በሚገባ የሚያሟሉ እረኞች አሉ ቢባል እንኳ በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። ታዲያ ይህ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከአንዱ ቤተክርስቲያን ወደ ሌላው ቤተክርስቲያን ቢንከራተት ምን



ያስገርማል! ደግሞስ መልካም እረኛን ማጣት የመሰለ ምን ክፉ ነገር አለ!

ሁለተኛው ምክንያት፥ መልካም አስተዳደር ማጣት ነው። ዓይነቱ ምንም ይሁን ምን አስተዳደራዊ ቀውስ ፈጽሞ ያልነካቸው አብያተ ክርስቲያናት አሉ ቢባል እጅግ ጥቂቶች ናቸው። ምዕመናንን ማብቂያ ለሌለው እንግልት ከዳረጋቸው አስተዳደራዊ ቀውሶች ውስጥ አንደኛውና ዋነኛው የመሪዎች በኀላፊነት ለመጠየቅ ፈቃደኛ አለመሆን ነው። ለአብነት ያህል ይህን ጠቀስኩ እንጂ ሌሎችም በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ እሙን ነው። የችግሩ ዓይነት ልዩ ልዩ ይሁን እንጂ የሁሉም ውጤት ግን ተመሳሳይ ነው ፤ ውጤቱም ቤተክርስቲያንን ለአስተዳደራዊ ቀውስ መዳረግ ነው። ምዕመናን እንዲህ ዓይነቱን ችግር መሸከም ሲያቅታቸው፥ ያላቸው አማራጭ ወደ ሌላ ቤተክርስቲያን መሰደድ ነው። ሌላው ቤተክርስቲያን ችግር እንዳለ ጠፍቷቸው ሳይሆን ለጊዜው የተሻለ መፍትሄ ሆኖ ስለሚታያቸው ነው።

ሦስተኛው ምክንያት፥ መልካም ኅብረት ማጣት ነው። ክርስትና በብዙ መልኩ የማኅበራዊነት ጠባይ አለው። በሌላው አነጋገር ክርስትና "እኔነትን" ሳይሆን "አብሮነትን" (ኅብረትን) የሚያጠብቅ እምነት ነው። የወቅቱን ክርስትና እንመርምር ብንል ግን ከዚህ እውነታ ርቆ እናገኘዋለን። በአብዛኛው ማለት ይቻላል፥ ክርስቲያናዊ ኅብረቶች ሁሉ ልባዊ ወዳጅነት ይጎድላቸዋል። ክርስቲያናዊ ወንድማማችነቶች ላይ ላዩን ናቸው። መተሳሰብ የለም፥ መሸካከም የለም፥ መተራረም የለም። በጥቅሉ "ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ" (ገላ 6፥2) ከሚለው ትእዛዝ ጋር ሆድና ጀርባ ሆነናል። ላይ ላዩን የሚጋልብ ኅብረት ማንንም አይጠቅምም። ደግሞም ግልብልብ ያለ ኅብረት ማንንም ለቁም ነገር አያደርስም።

ቤተክርስቲያን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ማኅበራዊነትን ማጥበቅ ያለባት ወቅት ቢኖር ይህ ወቅት ነው። የዚህ ምክንያቱ ማኅበራዊ ሕይወት ከማጣቻቸው የተነሳ በብቸኝነት

የሚሰቃዩ አያሌ ወገኖች ስላሉ ነው። እንዲህ ሲባል ምናልባት ችግሩ እንደ ችግር አይታየን ይሆናል። ምናልባትም የሕዝብ ብዛት አሳሳቢ ደረጃ ላይ በደረሰበት ዘመን ስለ ብቸኝነት ማውራት ቂልነት ሊመስል ይችላል። በተግባር የምናየው ግን የዚህን ተቃራኒ ነው። የዕለት ተዕለት ግንኙነቶችም የሚያስረዱን ከማኅበራዊ ሕይወት የተነጠሉ አያሌ ሰዎች መኖራቸውን ነው። ጌታ ኢየሱስ ለሦስት ዓመታት ያህል ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የነበረው የቅርብ ወዳጅነት ለቤተክርስቲያን ትልቅ ምሳሌነት አለው። ከዓለም የመረጣቸውን ደቀ መዛሙርት ወደዳቸው፥ ተንከባከባቸው፥ አስተማራቸው፥አስጠነቀቃቸው፥አበረታታቸው፥ አዳመጣቸው፥ በእምነት አጸናቸው፥ በስሙ ላካቸው፥ በመጨረሻም አንዱ ለሌላው እንዲሁ እንዲያደርግ አዘዛቸው። ይህ የክርስቶስ ማኅበራዊ ምሳሌነት የጥንቷ ቤተክርስቲያን "መለያ" ወይም "መታወቂያ" ነበር።

የጳውሎስ የቅርብ ወዳጅና የታሪክ ጸሐፊው ሉቃስ፥ ስለ ጥንቷ ቤተክርስቲያን ማኅበራዊ ሕይወት ሲገልጽ:- "ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው፥ ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደሆነ ማንም አልተናገረም... ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር" (የሐዋ 4:32፥35 እንዲሁም የሐዋ 2:44፥46 ይመለከቷል) ብሏል። እነዚህ የጥንት ክርስቲያኖች አብረው ይጸልዩ ነበር፤ አብረው ያመልኩ ነበር፤ አብረው ይመሰክሩ ነበር፥ ያላቸውንም ነገር አብረው ይካፈሉ ነበር። እርስ በርስ የነበራቸው ፍቅርና መተሳሰብ የመዳናቸው አንዱ ምስክር ከመሆኑም በላይ በዙሪያቸው ላለው ዓለም ትልቅ ምሳሌነት ነበረው። ፍቅር የእርሱ የሆኑ ሁሉ መለያ እንደሆነ ራሱ ጌታ ኢየሱስ ተናግሯል። የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የነበራቸው ፍቅር ግልብ ፍቅር አልነበረም። በመሀከላቸው የነበረው እውናዊ ትስስብ የትንሣኤው ኀይል እውናዊ ምስክር ነበር። በዚህም ምክንያት "ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር" (የሐዋ 2፥47)። ሐዋርያት በመልእክቶቻቸው ላይ በተደጋጋሚ አጽንኦት የሰጡት ጉዳይ ቢኖር የእርስ በእርስ ትስስብን ነበር [12] ።



# ምዕራፍ ስምንት

## የሽማግሌዎች የአመራረጥ መስፈርት

በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደምንመለከተው በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሁለት ቋሚ ቢሮዎች አሉ። እነሱም የሽማግሌ (የእረኛ ወይም የመጋቢ ወይም የኤጲስቆጶስ) ቢሮና የዲያቆናት ቢሮ ናቸው። በሐዋርያት ዘመን እኒህ ሁለት ቢሮዎች የሌሏት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ተጠቅሳ አናገኝም (የሐዋ 20፥17፤ ፊል 1፥1 1ጢሞ 3፥1-12)። የሽማግሌዎች ቢሮ መንፈሳዊና አስተዳደራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን የዲያቆናት ቢሮ ደግሞ ማኅበራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ነው። ቢሮ የሚለው ቃል ተግባርን፥ ሹመትንና ሥልጣንን የሚያመለክት ቃል ነው። ቤተክርስቲያን ተልዕኮዋን መልክና ሥርዓት ባለው መንገድ ማከናወን የምትችለው የተወሰነ ሥልጣንና ኀላፊነት ያለው የአገልግሎት ክፍል ወይም ቢሮ ሲኖራት ነው። ሥልጣናዊ አካል ሲባል ግን ጠያቂ የሌለው አምባገነናዊ አካል ማለት አይደለም። የሽማግሌዎችም ሆነ የዲያቆናት ሥልጣን ከማኅበረ ምዕመናኑ ሥልጣን የሚበልጥ ወይም የሚልቅ አይደለም። የሽማግሌዎችና የዲያቆናት ቢሮ ሥልጣን በፍጹማዊ አገዛዝ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በኀላፊነትና በተጠያቂነት ላይ የተመሠረተ ነው። በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ በሥርወ ትውልድ ሐረግ (በውርስ)፥ በተለየ ሙያዊ ሥጦታና ችሎታ፥ እንዲሁም በዕድሜና በሀብት ላይ የተመረኮዘ የሥልጣን ድልድል ፈጽሞ ቦታ የለውም።

የማኅበረ ምዕመናንን ዋነኛነት የሚንቅና ለምዕመናንም ቦታ የማይሰጥ አመራር አዲስ ኪዳናዊ አይደለም። የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ጥቂት የአመራር አካላት በዚህ መልክ ሊሠለጥኑ አይችሉም። እርግጥ ነው ቤተክርስቲያን ድርጅታዊ ቅርጽ ያላት መንፈሳዊ ተቋም በመሆኗ ነገሯን ሁሉ መልክና ሥርዓት ባለው ሁኔታ ማራመድ ይኖርባታል። ለዚህ ደግሞ አንድ የሥልጣን ተዋረድ አስተዳደር ያስፈልጋል። እንዲህ ማለት ግን ይህ ሥልጣናዊ

አካል ያሻውን ያስገባል፥ ያሻውን ያስወጣል፥ ያሻውን ይሠራል፥ ያሻውን ይተዋል ማለት አይደለም። በደፈናው ተጠያቂነት የሌለበትና እንዳሰኘው የሚኖር አካል አይደለም። እንዲያውም የእነዚህ ቢሮዎች ሥልጣን የተመሠረተው በቢሮው አገልግሎት ውስጥ በሚገቡት ሰዎች ማንነት ላይ ሳይሆን እግዚአብሔር ለይቶ ባቆመው የቢሮው አገልግሎት ኀላፊነት ላይ ነው። ለዚህ ኀላፊነት መብቃት የሚቻለው እግዚአብሔር ያስቀመጠውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመዘኛ ወይም መስፈርት ማሟላት ሲቻል ነው። እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመዘኛዎች በ1ጢሞ 3፥1-13 እና በቲቶ 1፥6-9 ተዘርዝረዋል። ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዱን መመዘኛ በየተራ እንዳስሳለን። በቅድሚያ ግን ለንጽጽርና ለግንዛቤ እንዲረዳን በጢሞቴዎስና በቲቶ መልእክቶች ላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች ጎን ለጎን እናቀርባለን።

| <u>መስፈርት በጢሞቴዎስ</u> | <u>መስፈርት በቲቶ</u> |
|---|---|
| (1ጢሞ 3፥2-7) | (ቲቶ 1፥6-9) |
| 1. የማይነቀፍ | 1. የማይነቀፍ |
| 2. የአንዲት ሚስት ባል | 2. የአንዲት ሚስት ባል |
| 3. ልከኛ | 3. የሚያምኑ ልጆች ያሉት |
| 4. ራሱን የሚገዛ | 4. የማይኩራ |
| 5. እንደሚገባው የሚሠራ | 5. የማይቆጣ |
| 6. እንግዳ ተቀባይ | 6. የማይሰክር |
| 7. ለማስተማር የሚበቃ | 7. የማይጨቃጨቅ |
| 8. የማይሰክር | 8. ረብ የማይወድ |
| 9. የማይጨቃጨቅ | 9. እንግዳ ተቀባይ |
| 10. ገር የሆነ | 10. በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ |
| 11. የማይከራከር | 11. ጠንቃቃ |
| 12. ገንዘብን የማይወድ | 12. ጻድቅ |
| 13. ልጆቹን በጭምትነት የሚገዛ | 13. ቅዱስ |
| 14. የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር | 14. ራሱን የሚገዛ |
| 15. አዲስ ክርስቲያን ያልሆነ | 15. ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት መምከር የሚችል |
| 16. በውጭ ካሉ ሰዎች መልካም ምስክርነት ያለው | 16. ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የሚቃወሙትን መውቀስ የሚችል |



አንድ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ወይም ዲያቆን በመንፈሳዊና በአስተዳደራዊ ጉዳይ ላይ ከመሾሙ በፊት የውስጣዊና የውጫዊ ማንነቱን የሚመለከቱ መመዘኛዎች የግድ ማሟላት አለበት። እነዚህ መመዘኛዎች የተሰጡትና የተቀመሩት በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር ነው።እንደ አዲስ ኪዳን አስተያየት በሽማግሌም ሆነ በዲያቆናት ቢሮዎች ውስጥ ገብቶ ለማገልገል፥ መመዘኛዎቹን አሟልቶ መገኘት ይጠበቃል። ከሁለቱ በአንዱ ቢሮ ውስጥ ገብቶ ለማገልገል መፈለግ ብቻ በራሱ በቂ አይደለም። ምክንያቱም ሁለቱም ቢሮዎች የሚፈልጉት ሰው እግዚአብሔር ያስቀመጠውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመዘኛ በበቂ የሚያሟላውን ነው። ከሁሉ በላይ መታወቅ ያለበት ግን "በእነዚህ ቢሮዎች ውስጥ ገብቶ ለማገልገል፥ መመዘኛዎቹን ሙሉ በሙሉ ማሟላት ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም?" የሚል ጥያቄ ከቶ መነሳት አይችልም። መመዘኛዎቹ የተቀመጡት ለይስሙላ ሳይሆን ለምዘና ነው። እናም "አዎ" የግድ መመዘኛዎቹን ማሟላት ያስፈልጋል። ከዚህ በመቀጠል በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች እንመለከታለን።

## 8.1 "...ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይባዋል፤ የማይነቀፍ"

በጢሞቴዎስም ሆነ በቲቶ መልእክቶች ላይ የምናገኘው የመጀመሪያው መመዘኛ "የማይነቀፍ" የሚለውን ነው። ከመመዘኛዎቹ ጠቅላላ ይዘት እንደምንረዳው በሁለቱም መልእክቶች ላይ ያሉት መመዘኛዎች ሁሉ "የማይነቀፍ"

በሚለው መመዘኛ ሥር የሚካተቱ ናቸው። ይህ ቃል "አኔፒሌምፕቶን" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ሲሆን ፍቺውም "በአንዳች ነገር የማይወቀስ ወይም የማይተች" ማለት ነው። እንዲሁም በሥራው ሁሉ ጸያፍም ሆነ ነውር ነገር የሌለበት ማለት ነው [1]። ሽማግሌ በየትኛውም የሕይወቱ አቅጣጫ ተነቃፊ ወይም አስነዋሪ ነገር ሊኖረው የማይገባው ፥ አገልግሎቱ አርአያዊነትን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው። ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ቤት የሚጠብቁና የእግዚአብ ሔርን ሕዝብ የሚመሩ ናቸው፤ እግዚአብሔር ለእንዲህ ዓይነቱ አገልግሎት የሚመርጣቸው ሰዎች ለእርሱ የሚገዙትን እንጂ ከፈቃዱ የሚያፈነግጡትን አይደለም። ይህ ታላቅ አገልግሎት ታማኝ ሰውን ይፈልጋል። ያም ሰው "በነገር ሁሉ የማይነቀፍ" ሰው ነው። እውነተኛ እረኛ አርአያዊ እረኛ ነው። በመልካም ተግባርና አኗኗር የተመሰከረለት እንጂ ከዚህም ከዚያም እጅ የሚጠቀምበት አይደለም። እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚፈልገው እንዲህ ዓይነቱን ነው።

## 8.2 "...ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤... የአንዲት ሚስት ባል..."

ይህ ሐረግ ብዙ ያከራከረ ሐረግ ነው። በዚህ ሐረግ ላይ የተሰጡት ትንታኔዎች ልዩ ልዩ ከመሆናቸውም በላይ የራስን አስተምህሮ እንዲደግፉ የተደረጉ ናቸው። "የአንዲት ሚስት ባል" ማለት ምን ማለት ነው? የሚለው ጥያቄ በእርግጥም የሚያወያይ ጥያቄ ነው። በዚህ ሐረግ ላይ ወደ አምስት የሚጠጉ ፍቺዎች ተሰጥተዋል። በመሆኑም አምስቱንም ፍቺዎች እንቃኛለን።

8.2.1 የአንዲት ሚስት ባል ማለት "ሚስቱ ቤተክርስቲያን የሆነች ወይም ሳያገባ እንዳገባ ሰው ራሱን የቆጠረ" ማለት ነው። የዚህ ፍቺ አውራ አቀንቃኝ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ነች። ካቶሊካውያኑ ይህን ሐረግ በዚህ መልኩ የፈቱበት ዋናው ምክንያት "ጳጳሳት ወይም ካህናት ሁሉ ማግባት የለባቸውም" የሚል ጽኑ አቋም ስላላቸው ነው። እርግጥ ይህ አቋም



የካቶሊካውያን ሁሉ አቋም አይደለም። ይሁን እንጂ ይህ አቋም የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጳጳሳት በሆኑ ሁሉ ላይ ተፈጻሚነት አለው። እንደ እነሱ አባባል "አለማግባት ወይም ሳያገባ እንዳገባ ሰው ራስን መቁጠር" በፍቺ ጉዳይ የሚመጣ ጣጣን ያስቀራል።

አለማግባትን እንደ ከፍተኛ መንፈሳዊነት ቆጥሮ ከጋብቻ መራቅ ይህን ትርጓሜ ሊያሰጥ አይችልም። ከዚህ በተጨማሪ ጳጳሳት ሚስት የለሽ እንዲሆኑ የሚያዝ አንድም አዲስ ኪዳናዊ ጥቅስ የለም። ጳጳሳዊ አገልግሎትን የቱንም ያህል ብናላቀው፥ ጳጳሳት አያግቡ የሚል መለኮታዊ ድንጋጌ ከቶ የለም። ጋብቻን የፈጠረ አምላክ ጋብቻን ከልክሎ አያውቅምና።

8.2.2 የአንዲት ሚስት ባል ማለት "ኤጲስቆጶስ ወይም ሽማግሌ እንደገና ማግባት አይችልም" ማለት ነው። ኤጲስቆጶስ አንድ ጊዜ ብቻ ማግባት ይፈቀድለታል። ሆኖም፥ ሚስቱ የሞተችበት እንደሆነ ግን ዳግም ማግባት አይችልም። የዚህ አቋም ተከታይ የሆኑ ሁሉ ለአቋሙ ተመሳሳይ የሆነ አመለካከት ባይኖራቸውም ሁሉም ግን ዳግም ጋብቻን አይቀበሉም። ለምሳሌ "የቅዱሳን ሐዋርያት የእምነት አቋም" በተሰኘው መጽሐፍ ላይ እንዲህ የሚል አስተያየት ሰፍሯል፥ "አንድ ያገባ ሰው የጵጵስናን ሹመት ሊቀበል ይችላል፤ ሆኖም ሳያገባ የጵጵስና ሹመት የተቀበለ ሰው እስከ መጨረሻው ድረስ ሳያገባ መዝለቅ አለበት" [2] ።

የዚህ ፍቺ ዓይነተኛ ድክመት፥ መጽሐፍ ቅዱስ በጋብቻ ጉዳይ ላይ ያለውን አስተያየት በሚገባ ያላገናዘበ መሆኑ ነው። በየትኛውም የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ውስጥ ሚስቱ የሞተችበት ሰው ዳግም እንዳያገባ አልተከለከለም። ሌላው ቀርቶ ሚስቱ የሞተችበት ሰው ዳግም ቢያገባ እንኳን

ድርጊቱ የምግባር ጉድለት ሊያስነሳ የሚችልበት አንድም መሠረት የለም::

8.2.3 የአንዲት ሚስት ባል ማለት "ኤጲስቆጶስ የግድ ያገባ መሆን አለበት" ማለት ነው:: ያላገባ ሰው ኤጲስቆጶስ ለመሆን ማሰብም ሆነ መመኘት የለበትም:: ምክንያቱም ኤጲስቆጶስነት የግድ ባለ ትዳር መሆንን ይጠይቃል::

ይህ አመለካከት የተሳሳተ ነው:: ጳውሎስ ለማለት የፈለገው "ኤጲስቆጶስ ያገባ ወይም ባለትዳር መሆን አለበት" ከሆነ "አንዲት" (በግሪክ "ሚያስ") የምትለዋን ቃል መጠቀም አስፈላጊው አልነበረም ምክንያቱም "አንዲት" የምትለው ቃል አበክራ የምታሳየው "የግድ ያገባ መሆንን" ሳይሆን "የብዙ ወይም የአያሌ ሚስት" ባል አለመሆንን ነው:: ጸሐፊው ሊል የፈለገው ይህን ከሆነ ግን "አንዲት" (ሚያስ) የምትለውን ቃል ሳያስገባ በቀላሉ ማለት ይችል ነበር:: ከሁሉ በላይ ግን በአንድ ወቅት የቤተክርስቲያን ሽማግሌ የነበረው ጳውሎስ (1ጢሞ 4÷14፤ ከ2ጢሞ 1÷6 ጋር ያመሳክሩ) ራሱ ያላገባ ሰው ሆኖ ሳለ (1ቆሮ 7÷6-7) እንዴት አድርጎ ሌሎችን ካላገባችሁ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ልትሆኑ አትችሉም ሊላቸው ይችላል? ደግሞስ እንዴት አድርጎ ገና ያላገቡትን ሰዎች (ጢሞቴዎስንና ቲቶን 1ጢሞ 5÷19-20፤ ቲቶ 1፥5) በቤተክርስቲያን ጉዳይ ላይ ዋነኛ አድርጎ ይሾማቸዋል? ከቶ የማይሆን ነገር ነው:: ጳውሎስም ሆነ ሌሎች የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች አለማግባትን አንድም ጊዜ አልኮነኑም:: እንዲያውም አለማግባት ጌታን በነፃነት ለማገልገል ጠቃሚ እንደሆነ ጳውሎስ የራሱን ሕይወት ምሳሌ አድርጎ በመጥቀስ አስረድቷል (1ቆሮ 7÷32፤ 7÷7-8፤ 9÷5):: ሐዋርያው ያለሚስት በመሆኑ ራሱን ለጌታ ሥራ እንደማይገባ አድርጎ የቆጠረበት ጊዜ የለም (1ቆሮ 7÷17)::



8.2.4 የአንዲት ሚስት ባል ማለት "ኤጲስቆጶስ የአንድ ሴት ሰው ብቻ መሆን አለበት" ማለት ነው:: በሌላ አነጋገር ኤጲስቆጶስ ጌታን ከማግኘቱ በፊትም ሆነ ጌታን ካገኘ በኋላ አግብቶ የፈታ መሆን የለበትም ማለት ነው:: እንዲህ ሲባል ግን የመጀመሪያ ሚስቱ የሞተችበት ሰው ሌላ ሴት ቢያገባ የአንዲት ሴት ሰው አይደለም ማለት አይደለም:: አንድ ሰው እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ቢገጥመው፥ ኤጲስቆጶስ ከመሆን የሚያግደው ምንም ምክንያት የለም:: "የአንዲት ሚስት ባል" የሚለው መመዘኛ የሚያመለክተው ጋብቻን አስመልክቶ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ምንጊዜም ንጹህ ሆኖ መገኘትን ነው:: ይህ መመዘኛ የትዳር ሕይወትን ብቻ ሳይሆን የሚመለከተው በትዳር ሕይወት ውስጥ ያለ ባህርይንም ጭምር ነው:: የአንዲት ሴት ሰው የሆነ ሽማግሌ የወንድና የሴትን ግንኙነት በተመለከተ አንዳች ወቀሳ ሊቀርብበት አይችልም:: ጋብቻ የአንድን ሰው ማንነትና ሕይወት በሚገባ ማሳየት ይችላል:: ለምሳሌ በጥንት አይሁዳውያንና ሮማውያን ዘንድ ጋብቻ ከምንም የማይቆጠር ተራ ነገር ነበር:: በአይሁዳውያን የትዳር ሕይወት ውስጥ በወንድና በሴት መካከል ያለው ግንኙነት አንድነትን የሚያሳይ አይደለም:: አንድ አይሁዳዊ ሚስቱን በፈለገው ጊዜና ምክንያት ሊፈታ ይችል ነበር:: ለምሳሌ ጥሩ ምሳ ባይቀርብለት ወይም ማታ ከውጭ ሲገባ የእግር ውኃ ተሰናድቶ ባይጠብቀው በዚህ ተበሳጭሁ ብሎ ሊፈታት ይችላል:: ወይም ደግሞ ከእሷ የተሻለ ሴት ያገኘ ከመሰለው ያለ ምንም ርኅራኄ በአንድ ምሽት ሊያባርራት ይችላል [3]:: በጌታ ኢየሱስ ዘመን የአይሁዳውያንን ታሪክ በሚገባ ዘግቦ በጽሑፍ ያቆየው ፍላቪየስ ጆሴፈስ ስለ ፍቺ ጉዳይ ሲጽፍ "የፍቺ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ወንዱ ብቻ ነው" [4] ብሏል:: ይህ የሚያሳየን በዚያን ዘመን ሰዎች ስለ ትዳር የነበራቸው ግምት እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን ነው::

እንደ ጳውሎስ አስተያየት ግን ጋብቻ ክቡር ነገር ነው:: እንዲያውም የአንድ ሰው ማንነት የሚለካው ለጋብቻው ባለው ታማኝነት ነው:: እዚህ ላይ ግን አንድ መሠረታዊ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: ይኸውም የጢሞቴዎስና የቲቶ መመዘኛዎች በቀጥታ የሚመለከቱት ከጌታ በኋላ ያለን ሕይወት ነው? ወይስ ከጌታ በፊት ያለውንም ይጨምራል? እርግጥ ነው "የአንዲት ሚስት ባል" የሚለው መመዘኛ አንድ ሰው ከመዳኑ በፊት የነበረውን ሕይወት የሚመለከት አይደለም:: የአንድን ሰው መንፈሳዊ ሕይወት በቀደመ ሕይወቱ ወይም አኗኗሩ መለካት ከቶ አይቻልም:: የክርስቶስ መንፈስና ቃል የሌለውን ሰው እንዴት ልንኮንነው እንችላለን? ደግሞስ እግዚአብሔር ይቅር ያለውን ሰው እንዴት በቀድሞ አረማመዱ ልንፈርድበት እንችላለን? በቀድሞ ወይም ከጌታ በፊት በነበረ ሕይወት ላይ የተመሠረተ መመዘኛ ሁሉ የጌታን ጸጋ የሚያቃልል ነው:: የ1ጢሞ 3፥2 መመዘኛ ቅድመ-ለውጥ ወይም ቅደመ-ደህንነት ሕይወትን በጭራሽ አይመለከትም 5 ::

8.2.5 የአንዲት ሚስት ባል ማለት "ኤጲስቆጶስ ከአንድ ሚስት በላይ ሊኖረው አይገባም" ማለት ነው:: የአያሌ ወይም የብዙ ሚስቶች ባል (Polygamist) መሆን በጭራሽ አይቻልም:: ጳውሎስ ይህንን መመዘኛ ለሽማግሌዎች ብቻ ሳይሆን (1ጢሞ 3፥2፤ ቲቶ 1፥6) ለዲያቆናትም ጭምር (1ጢሞ 3፥12) ማውጣት የፈለገበት ትልቅ ምክንያት አለው:: ሐዋርያው ወንጌልን በሰበከባቸው ሀገሮች ሁሉ የብዙ ሚስቶች ባል መሆን የተለመደ ተግባር ወይም ወግ ነበር:: በግሪካውያኑና በሮማውያኑ ባህል ውስጥ የእድሜ ዘመንን ሁሉ ከአንዲት ሴት ጋር ማሳለፍ ጅልነት ወይም ቂልነት ነው ለምሳሌ ቄሳር 4 ሚስት፥ኔሮ 5 ሚስት፥ ሄሮድስ ደግሞ 9 ሚስት



ነበሯቸው [6]:: አይሁዳዊው የታሪክ ጸሐፊ ጆሴፈስ ስለ አይሁዳውያኑ ሲገልጽ ደግሞ "ብዙ ሚስቶች ማግባት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የጥንት ወጋችን ነው" ብሏል [7]:: የአያሌ ሚስቶች ባል መሆን በወቅቱ የተለመደ አገራዊ ወግ መሆኑን በርካታ ራባዊ መዛግብት (rabbinic literatures) ግልጽ ያደረጉት ጉዳይ ነው (ለተጨማሪ ማብራሪያ "ሚሽና" በተባለው የአይሁዶች የትንታኔ መጽሐፍ ውስጥ "ይባሞት 4፥11"፥"ቄቱቦት 10፥1"፥ " ሳንሂድሪን 2፥4" ፥ "ቄሪቶት 3፥7" ፥"ቂዱሺን 2፥7" ፥ "ቤኮሮት 8፥4" መመልከት ይቻላል):: በሌላ በኩል ደግሞ ሰማዕቱ ጀስቲን (Justin Martyr) "ከትራይፎ ጋር የተደረገ ክርክር" በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ የብዙ ሚስት ባል መሆን በአይሁዳውያን ዘንድ የተለመደ ድርጊት መሆኑን አመልክቷል [8]:: በተመሳሳይ ሁኔታ የአያሌ ሚስት ባል መሆን ለአሕዛቡ ዓለም እንግዳ ተግባር አለመሆኑን ከ420 ዓ.ዓ. እስከ 350 ዓ.ም. ባሉት 770 ዓመታት ውስጥ የተጻፉ መጻሕፍት በግልጽ አትተዋል [9]::

ከዚህ በላይ የቀረቡት ታሪካዊ ማስረጃዎች እንደሚያስረዱን ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት በአይሁዱም ሆነ በአሕዛቡ ዓለም የተለመደ ወግ መሆኑን ነው:: የእነዚህን ሁለት ዓለሞች አካባቢያዊና ባህላዊ ወግ ጠንቅቆ የሚያውቀው ጳውሎስ፥ ኤጲስቆጶስ "የአንድ ሚስት ባል" መሆን አለበት በማለት በርካታ ሚስቶችን የማግባትን ልምምድ መቃወም ነበረበት:: ጳውሎስ በ1ጢሞ 3፥1-7 እንዲሁም በቲቶ 1፥6-9 የዘረዘራቸው መመዘኛዎች በቀጥታ የሚመለከቱት አንድ ሰው ጌታን ከመቀበሉ በፊት ያለውን ሕይወት ሳይሆን ጌታን ከተቀበለ በኋላ ያለውን ሕይወትና ለውጥ ነው::

ጳውሎስ ለማለት የፈለገው "ኤጲስቆጶስ አንድ ጊዜ ብቻ ያገባ መሆን አለበት" ከሆነ ይህን አባባሉን በቀላሉ መግለጽ ይችል ነበር:: ግን አላደረገውም:: "አንድ ጊዜ ብቻ ያገባ" ለማለት ቢፈለግ ኖሮ "ሃፓክስ ጊጋሜሜኖስ" የሚለውን

ጠንካራ የግሪክ ቋንቋ አገላለጽ ይጠቀም ነበር:: በዚህ አገላለጽ መሠረት "ሃፓክስ" (አንዴ) የሚለው ቃል"ጊጋሜሜኖስ" (ያገባ) ከሚለው ማሠሪያ አንቀጽ ጋር ሲጣመር የሚሰጠው ትርጉም "አንድ ጊዜ ብቻ ያገባና በዚያው ጋብቻ የዘለቀ" የሚል ነው:: እንዲህ ዓይነቱን ስዋስዋዊ አወቃቀር በዕብራውያን መልእክት 10÷2 ላይ ("አንድ ጊዜ ነጽተው") እና 9÷26 ላይ ("ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጧል) ማግኘት ይቻላል:: ኃጢአትን ሊደመስስ አንድ ጊዜ የተገለጠው አዳኝ ÷ በዚህ ጉዳይ ላይ ዳግመኛ መገለጥ አያስፈልገውም:: "ሃፓክስ ጊጋሜሜኖስ" የሚለው ሐረግ አጥብቆ የሚያሳየው "ጋብቻው የአንዴና የመጨረሻ" መሆኑን ነው 10:: ጳውሎስ እንዲህ ዓይነት ጠንካራ አገላለጽ እያለለት ሌላ ትርጉም የሚሰጥ አማራጭ ይወስዳል ማለት በጣም ያስቸግራል:: ይህን ሁሉ ስንመለከት የዚህ ሐረግ ፍቺ ማለትም ጳውሎስ ለማለት የፈለገው ኤጲስቆጶስ (ሽማግሌ) ከአንድ በላይ ሚስት ሊኖረው አይገባም የሚለውን እውነታ ለመግለጽ ነው::

## 8.3 "...ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤... ልከኛ"

"ልከኛ" የሚለው ቃል "ኔፋሊዮን" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተገጎመ ነው:: በብሉይ ግሪካውያን ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ "ኔፋሊዮን" ማለት በቁሙ (Literally) "በወይን ጠጅ ያልተበረዘ" ማለት ነው [11]:: ይህ ቃል ሰፊም ጠባብም ትርጉም አለው:: ጠበብ ባለ አገባቡ ሲታይ ከወይን ጠጅ ፍጹም የራቀ ማለት ሲሆን ሰፋ ባለ ትርጉም ሲታይ ደግሞ በማንኛውም ረገድ "ልክ ያለው÷ መጠን ያለው ወይም ስፍር ያለው" ማለት ነው:: እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነጥብ ይህ ልከኛነት ከአዕምሮአዊ÷ ከባህርያዊና ከመንፈሳዊ ልከኛነት (መጠነኛነት) ጋር ተዛምዶ ያለው መሆኑ ነው:: ኔፋሊዮን የሚለው ቃል ሰፋ ባለ አጠቃቀሙ ሲታይ ሦስት ዋና ዋና ሐሳቦችን ይይዛል:: አንደኛው÷ የነገሮችን አካሄድና አሠራር (በዚህ አገባቡ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አሠራሮችን) በሚገባ መመዘንና መገምገም የሚችል፤ ሁለተኛው የነሲብ ወይም የመላ ነገር



የሌለበት፤ ሦስተኛው የአመለካከትና የአስተሳሰብ ውጥንቅጥነት እንዲሁም መዘበራረቅ የማይታይበት የሚሉ ናቸው [12]:: ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ቃል የተጠቀመው ጠበብ ባለ ትርጉም ሳይሆን ሰፋ ባለ ትርጉሙ ነው:: እንደ ሐዋርያው አባባል ሽማግሌ የማይናወጥና በእግዚአብሔር ቃል ትምህርት የጸና መሆን አለበት:: የዲያቢሎስን ሽንገላ ለመቋቋም (1ጴጥ 5÷8-9)÷ ሐሰተኛ ትምህርትን ለመከላከልና (2ጢሞ 4÷3-5) ምግባራዊ እንዲሁም መንፈሳዊ ውድቀትን ለማስቀረት ልከኛ መሆን ያስፈልጋል::

## 8.4 "...ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤...ራሱን የሚገዛ"

ይህ መመዘኛ የተተረጎመው "ሶፍሮን" ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ለዚህ የግሪክ ቃል አቻ የሆነ አንድ የአማርኛ ቃል ማግኘት በጣም ያስቸግራል:: ሶፍሮን ማለት በቁሙ የጠራ "ንቅአ ኅልዮ" ያለው (ንቅአ ኅልዮ ማለት ሥራን ከድርጊት በፊት በሐሳብ ውስጥ መመርመር÷ ማውጣት ማውረድ ወይም ማሰናዳት ማለት ነው) ወይም ምክንያታዊ ኀሊና ያለው ማለት ነው:: ይህ ቃል የቲቶን መልእክት ጨምሮ (1÷8፤ 2÷2÷5) በአዲስ ኪዳን ውስጥ በዚህ ቦታ ብቻ የሚገኝ ቃል ነው:: እንደ ጳውሎስ አስተያየት ሽማግሌ መንፈሳዊና መንፈሳዊ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ሚዛናዊ አቀራረብ ያለው መሆን አለበት:: ሶፍሮን በሚለው ቃል ውስጥ የተዋደደው ሌላው ፍቺ ደግሞ ሽማግሌ በአንድ በኩል ምክንያታዊ የሆነ በሌላ በኩል ደግሞ ስሜታዊ ያልሆነ (ግራና ቀኙን ሳያይ ዳኝነት የማይሰጥ) መሆን አለበት:: በሌላ አነጋገር ሽማግሌ ሚዛናዊና ትክክለኛ ዳኝነት መስጠት የሚችል÷ ጠቃሚ ምክሮችን መለገስና ውስብስብ መንፈሳዊ ችግሮችን መፍታት የሚችል መሆን አለበት:: ትክክለኛ ምክርን የማይሰጥ ሽማግሌን ወዳጁ የሚያደርግ ማን ነው? ሽማግሌ ቁም ነገረኛ መሆን አለበት:: ደግሞም በማያባራ የአመለካከት ግብግብ ውስጥ ለሚያልፉ ምዕመናን ትክክለኛና ምክንያታዊ የሆነ ምክር መስጠት የሚችል መሆን አለበት:: አንድ ሽማግሌ ለዚህ ደረጃ የሚበቃው ራሱን እንደሚገባ

መግዛት ሲችልና ለነገሩ ሁሉ ልክና ገደብ ሲያበጅ ነው። ሽማግሌ ከራሱ ፍላጎት ይልቅ የምዕመናንን ፍላጎት ማስቀደም አለበት [13]።

## 8.5 "...ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ ... እንደሚገባ የሚሠራ"

ይህ መልእክት ለመጀመሪያ ጊዜ በተጻፈበት ቋንቋ "እንደሚገባው የሚሠራ" የሚለው ሐረግ "ኮስሚዮስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው። "ኮስሚዮስ" የሚለው ቃል የተገኘው "ኮስሜኦ" (በሥነ ሥርዓት አደራጀ ወይም በመልክ በመልኩ አበጀ) እና "ኮስሞስ" (በሥርዓት አዋቀረ ወይም በሥርዓት አቀናጀ) ከሚሉት ቃላት ነው [14]። ሥርወ ቃላቱ እንደሚያመለክቱት ያ በሥርዓት የተደራጀው ወይም በሥርዓት የተዋቀረው ነገር የተደበላለቀ ወይም የተመሰቃቀለ አይደለም። በሌላ አነጋገር ሠርፀ ቃላቱ የሚያሳዩት ለነገሩ ሁሉ ሥርዓትና ደንብ ያለው መሆኑን ነው። እንደ ጳውሎስ አባባል ሽማግሌ ዛሬ እንዲህ ዓይነት ሰው ነገ ደግሞ እንዲያ ዓይነት ሰው መሆን የለበትም። ደግሞም በአኗኗሩ ሁሉ ወጥነትን ያጣ ዝብርቅርቅ ሰው መሆን የለበትም። ይልቁንም ለነገሩ ሁሉ ሥርዓት ያለው ሰው ነው መሆን ያለበት። የተጣጣመ ሕይወት የሌለው ሰው ለሽምግልና አገልግሎት የተገባ አይደለም። ሐዋርያው የቤተክርስቲያን ሽማግሌ "እንደሚገባው የሚሠራ" ("ኮስሚዮስ" በሥርዓት የሚኖር) መሆን አለበት ሲል ለአኗኗሩና ለአረማመዱ ሁሉ ቅጥ ያለው ሰው መሆን አለበት ማለቱ ነው። አኗኗሩ የታወከ ሰው የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ሊሆን አይገባም።

## 8.6 "... ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ ... ለማስተማር የሚበቃ"

ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ላይ ነው። የቤተክርስቲያን ሽማግሌ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር በቂ ችሎታ ያለው እንዲሆን



ይጠበቅበታል። "ለማስተማር የሚበቃ" የሚለው ሐረግ "ዲዳክቲኮስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ሲሆን ፍቺውም "የማስተማር ችሎታ ያለው" ማለት ነው። ይህ ቃል ለጢሞቴዎስ በተጻፉለት መልእክቶች ውስጥ የሚገኝ ቃል ነው (1ጢሞ 3፥2፤ 2ጢሞ 2፥24)። የቃሉ ፍቺ ሁለት ይዘቶች አሉት። አንደኛው፥ ለማስተማር የሚበቃ ሲባል ለሌሎች የሚተርፍ የእውነት ቃል ትምህርት ያለው ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል የማያውቅ ሰው ሌሎችን ሊመክርና ሊያበረታታ አይችልም። የእግዚአብሔርን ቃል የማያውቅ ሰው ሌሎችን ወደ እውነት ሊመራና የእውነት ባለቤቶች ሊያደርግ አይችልም። የክርስትናን መሠረታዊ አስተምህሮዎች በሚገባ ማስረዳት የሚቻለው ስለ አስተምህሮዎቹ በቂ ዕውቀት ሲኖረን ነው። የሽምግልና አገልግሎት የማስተማርም አገልግሎት በመሆኑ እንዲህ ዓይነት ችሎታን ይሻል። ሁለተኛው፥ ለማስተማር የሚበቃ ሲባል የእግዚአብሔርን ቃል የመግለጥ (በዚህ አገባቡ ገለጠ ማለት አዲስ ነገር አመጣ ማለት ሳይሆን በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተሰጠውን እውነት አሳወቀ፥ አስረዳ ማለት ነው) ብቃት ያለው ማለት ነው።

## 8.7 "...ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ ... እንግዳ ተቀባይ"

ይህ መመሪያ በተጻፈበት ዘመን ለአገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ የሆነን መጻተኛ ተቀብሎ ማስተናገድ የተለመደ ወግ ነበር። በተለያየ ምክንያት ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩ ሰዎች ሰላማዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ከያዙ ማንም ሰው ተቀብሎ ያስተዳድራቸው ነበር። በተለይ በየአገሩ የተበተኑ አይሁዶች የራሳቸውን ወገኖች ከማንም አብልጠው ያስጠጉ ነበር [15]። "እንግዳ ተቀባይ" የሚለው ሐረግ "ፊሎኬኖስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ሲሆን በቁሙ "መጻተኞችን የሚወድ" ማለት ነው። በሐዋርያት ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች ከቦታ ቦታ እንዲሁም ከአገር አገር በሚጓዙበት ወቅት በማንኛውም ሰው ቤት በእንግድነት አያርፉም። የዚህ ምክንያቱ የአካባቢው ሕዝብ ጣዖት አምላኪና ለጣዖትም የተሰዋ ሥጋ በላተኛ ነው ብለው ስለሚያስቡና ራሳቸውን

ከእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ጋር ማስተሳሰር ስለማይፈለጉ ነው (1ቆሮ 8፥1-13)። ስለዚህ የክርስቲያኖችን ቤት አፈላልጎ ምሽቱን በዚያ ማሳለፍ ብቸኛ አማራጫቸው ነበር [16] ።

ከዚህ በተጨማሪ መተላለፊያ መንገዶች ዘራፊና ነጣቂ ስለማያጣቸው ቀኑ ከመምሸቱ በፊት ማረፊያ ቦታ መፈለግ የግድ አስፈላጊ ነበር። ጳውሎስ በሮሜ ያሉ ክርስቲያኖችን ሲመክር "... ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ፤ እንግዶችን ለመቀበል ትጉ" (ሮሜ 12÷13 ) ብሏል። ሐዋርያው ጴጥሮስ ደግሞ "ያለ ማንጎራጎር እርስ በርሳችሁ እንግድነትን ተቀባበሉ" (1ጴጥ 4÷9) በማለት አሳስቧል። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊም "እንግዶችን መቀበል አትርሱ፤ በዚህ አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋልና" (ዕብ 13÷2) በማለት የእንግዳ ተቀባይነትን አስፈላጊነት አስታውቋል። ምዕመናን እንግዶችን በመቀበል እንዲተጉ ይሄን ያህል ከታዘዙ በነገር ሁሉ ምሳሌ እየሆኑ ቤተክርስቲያንን እንዲጠብቁ የታዘዙ ሽማግሌዎች ምን ያህል በዚህ ነገር ትጉአን ሊሆኑ ይገባል? ክርስትና ከአፍ ይልቅ የተግባር እምነት ነው። የክርስትናን ተግባራዊነት (Practicality) በሚገባ ከሚገልጡ ነገሮች ውስጥ አንዱ እንግዳ ተቀባይነት ነው።

## 8.8 "... ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ ... የማይሰክር"

የጥንት ቀርጤስ ነዋሪዎች "ዲዮኒሰስ" የተባለ አምላካቸውን ሲያመልኩ ነፍሳቸውን አያውቁም ነበር። ምክንያቱም ለአምልኮ የሚሄዱት ሁሉ በመጠጥ እየሰከሩ ነበር። በእንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ለአምልኮ የሚሄዱ ሰዎች አምባጓሮ ሳይፈጥሩና ሳይራበሹ አይመለሱም ነበር [17] ። በብሉይ (በጥንት) ግሪካውያን ፍልስፍና ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የነበረው አሪስቶትል "የማይሰክር" ("ሜ ፓሮይኖስ") የሚለውን ቃል "እምባ ጓሮኛ ያልሆነ ወይም የመጠጥ ሱሰኛ ያልሆነ" በማለት ነው የተጠቀመበት[18] ። "የማይሰክር" የሚለው ቃል "ሜ ፓሮይኖስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተመለሰ ሲሆን በቁሙ



"የመጠጥ ወዳጅ ያልሆነ ወይም የመጠጥ ባሪያ ያልሆነ" ማለት ነው። ይህ ቃል ሌላ ሁለተኛም ፍቺ አለው። ይኸውም "የማይሰክር" ማለት "ጠበኛና አንባ ጓሮኛ" ያልሆነ ማለትም ነው። የመጀመሪያው ፍቺ ሁለተኛውንም ፍቺ ያካትታል። በሌላ አነጋገር ሁለተኛው ፍቺ በአንደኛው ፍቺ ውስጥ ተካቷል።

የክርስቶስን ቤተክርስቲያን እንዲመግቡና እንዲጠብቁ የሚሾሙ ሽማግሌዎች የማይሰክሩ ደግሞም የመጠጥ ሱሰኞች ያልሆኑ መሆን አለባቸው። ሽማግሌዎች የመጠጥ ብቻ ሳይሆን ከሌላም ማንኛውም ዓይነት አስካሪ ነገር የተለዩ መሆን አለባቸው። በመጠጥም ሆነ በአደንዛዥ ዕጽ ራሱን የሚሰት ሰው መልካም ምሳሌ ሊሆን አይችልምና።

## 8.9 "...ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤... የማይጨቃጨቅ"

እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ጠብንና ክርክርን ማየት አይፈልግም። ምክንያቱም ጠብና ክርክር ቤተክርስቲያንን ያዳክማል፥ ደግሞም ያቀረቅዛል። "የማይጨቃጨቅ" የሚለው ቃል "አማኮስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው። ፍቺውም "ጸበኛ ያልሆነ ወይም ነትራካና ነዝናዛ ያልሆነ" ማለት ነው [19]። ሽማግሌ ነገረኛና አተካሪኛ መሆን የለበትም። እንዲሁም ነገር የሚያበዛና በነገርም የሚያደክም መሆን የለበትም። ጳውሎስ በመጀመሪያው መልእክቱ ላይ አሉታዊ በሆነ አነጋገር የሰጠውን መመሪያ (1ጢሞ 3÷3) በሁለተኛው መልእክቱ ላይ አዎንታዊ በሆነ አነጋገር ሲሰጥ፥ "የጌታም ባሪያ ለሰው ሁሉ ገር ለማስተማርም የሚበቃ ለትዕግሥትም የሚጸና ሊሆን እንጂ ሊጣላ አይገባውም" (2ጢሞ 2÷24) ብሏል። የበሰለ ሽማግሌ መሠረታዊና ዋነኛ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ነገር ዘብዛቢ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የትኛውንም ዓይነት ጸበኛነት አጥብቆ ይቃወማል። ሌላው ቀርቶ የእውነተኛውን ወንጌል ተቃዋሚዎች እንኳን በትህትናና በርኅራኄ የሚመልስ መሆን አለበት (2ጢሞ 2÷25)። ሰዎችን ለሽምግልና ከመምረጣችን በፊት ነገር ዘብዛቢና ነትራካ

አለመሆናቸው መመልከት ያሻል:: ከዚህ በተጨማሪ ሙሉ መልስ በሌላቸው ጉዳዮች ላይ ግትር አቋም የሌላቸውና ከእኔ ወዲያ ላሳር የማይሉ መሆናቸውን በሚገባ መመርመር ያስፈልጋል:: ምክንያቱም ሽማግሌ በሆነው ባልሆነው በነገር የሚበቅት (የሚነተርክ፥ የሚነዘንዝ፥ የሚችክ) መሆን የለበትም::

## 8.10 "...ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል!... ገር የሆነ"

ይህ ቃል ድርብርብ ትርጉሞች አሉት:: በሌላ አነጋገር ቃሉ አሳስቦ ወይም አዋዶ የያዛቸው ፍቺዎች በርካታ ናቸው:: "ገር የሆነ" የሚለው ቃል "ኤፔይኬስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ሲሆን ደግ (ክፉ ያልሆነ ይልቁንም በነገሩ ሁሉ መልካም የሆነ)፤ ቸር (ያለ መሰሰት የሚሰጥ፥ ሸርጎራጌ የሚለግስ፥ በፍጹም ልቦናው የሚቸር)፤ የዋህ (ቅን፥ ተንኮልን የማያስብ፥ መሠሪነትና ክፉነት የሌለበት)፤ ቻይ (ታጋሽ፥ ነገርን የሚችል፥ የሰላም ነገርን የሚከታተል) እና ለሰው አሳቢ" ማለት ነው [20] :: "ኤፔይኬስ" የሚለውን ቃል በአንድ የአማርኛ ቃል መተካት የማይቻለው፥ ቃሉ ከላይ የተዘረዘሩትን ፍቺዎች ሁሉ የሚይዝ በመሆኑ ነው::

ገር የሆነ ሰው የሌሎችን ጥፋትና ድክመት ታግሶ የሚያልፍ ነው:: ደግሞም የሌሎችን ውድቀት በቅንነት የሚመለከትም ነው:: ገርነት የታላቁ የእግዚአብሔር መለያ ባህርይ መሆኑን መዝሙረኛው ዳዊት ሲጽፍ፥ "አቤቱ አንተ መሓሪና ይቅር ባይ ነህና፥ ምሕረትህም ለሚጠሩህ ሁሉ ብዙ ነውና" (መዝ 86፥5) ብሏል:: በዚህ ቦታ "መሓሪና ይቅር ባይ" የሚለው ሐረግ "ኤፔይኬስ" ከሚው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው:: የሰፕቱዋጀንት ተርጓሚዎች (ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ቋንቋ ወደ ግሪክ ቋንቋ የተረጎሙት) የእግዚአብሔርን ገርነት "ኤፔይኬስ" በማለት መልሰውታል:: የእግዚአብሔር ሕዝቦች መቆየት የቻሉት እግዚአብሔር "ቻይ፥ ገርና መሓሪ (ኤፔይኬስ)" በመሆኑ ነው:: እግዚአብሔር



የሕዝቡ እረኞች እንዲሆኑ ኀላፊነት ከሰጣቸው ሽማግሌዎች ይሄንኑ ዓይነት ገርነት ይጠብቃል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲገፋና እንዲጣል ከቶ አይፈልግም::

ሽማግሌ እንደ እግዚአብሔር እረኛ ቻይና ታጋሽ፥ ቅንና የዋህ፥ ቸርና ደግ እንዲሁም ይቅር ባይና ለሰው አሳቢ መሆን አለበት:: በዚህ ኃጢአተኛ ዓለም ውስጥ የምንኖር ሰዎች፥ ይህ ነው የማይባል ጉዳት ይገጥመናል:: ከአካባቢያዊ ቀውስ አንስቶ እስከ ውስጣዊ ቅራኔ ድረስ አያሌ ሁኔታዎች ያብጠለጥሉናል:: በአንድ በኩል ረሀብና ድህነት በሌላ በኩል ደግሞ ሥራ አጥነትና ኢኮኖሚያዊ ዝቅጠት መድረሻ ያሳጡናል:: በየጊዜው እያሽቆለቆለ የሚመጣው የኑሮ ሁኔታ ሳያባራ ሌላው የኑሮ ጣጣ ብቅ ማለት ይጀምራል:: በዚህ ሁሉ ላይ የፍትህና የዳኝነት መጓደል ሲደረብ የት ልድረስ የትስ ልብረር ያሰኛል:: እንግዲህ ገር የሆኑና ገርነታቸውም ማብቂያ የሌለው ሽማግሌዎች የሚያስፈልጉን ይሄኔ ነው:: በየዕለቱ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ተጋግጠው የሚመጡ ምዕመናንን በገርነትና በቸርነት የማያቀና ሽማግሌ እንደምን ሽማግሌ ሊባል ይችላል? ሽማግሌ በክርስቶስ ገርነትና ትዕግሥት የሚያጸናና የሚያጽናና ነው (2ቆሮ 10፥11)::

## 8.11 "...ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ ... የማይከራከር"

"የማይከራከር" የሚለው ቃል "ሜ ፕሌክቴን" ከሚለው የግሪክ ቃል የተመለሰ ነው:: በግሪክ ቋንቋ "ሜ ፕሌክቴን" ማለት "ጠበኛ ያልሆነ፥ ሞገደኛ ያልሆነ ወይም ነገር ነገር የማይለው" ማለት ነው [21]:: ሽማግሌ የእግዚአብሔርን መንጋ መምራት ያለበት በገርነትና በቅንነት እንጂ በማን አለብኝነት መንፈስ አይደለም:: ወይም ደግሞ "መቀልጠሚያ ዱላ ተሸክሞ" በመንጋው መሀል የሚንጎራደድም አይደለም:: ሽማግሌ የነገር ጠረኛ ሊሆን አይገባም:: ደግሞም የቀናውን ነገር የሚያወናግርና የሌሎችን ግላዊ አስተያየት የሚያናንቅ መሆንም የለበትም::

የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔር መንጋ ነው (ሐዋ 20÷28):: ይህን መንጋ እንደሚገባ አለመንከባከብ ማለት የዚህን መንጋ ባለቤት ከምንም አለመቁጠር ማለት ነው (1ጴጥ 5÷1-4):: አንድ ሽማግሌ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የሚገጥሙትን አለመግባባቶች በትዕግሥትና በከሐሊነት የሚፈታ እንጂ ሞገደኛና ስልፈኛ ሊሆን አይገባም:: ሽማግሌ ልዩነቶችን ሁሉ ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍታት አለበት::

## 8.12 "...ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ ... ገንዘብን የማይወድ"

በተሃድሶ እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ የነበረው ጆን ካልቪን አንድ ጥንታዊ የላቲን ምሳሌ ጠቅሶ ሲጽፍ እንዲህ ብሎ ነበር÷ "ባለ ጠጋ ለመሆን የሚመኝ ሰው በአንድ ጀንበር ባለጠጋ ለመሆን ይጓጓል" [22]:: እንደ ካልቪን አባባል በአንድ ምሽት ባለጠጋ ለመሆን መመኘት የገንዘብ አፍቃሪነት ምልክት ነው:: ገንዘብ አፍቃሪነት ደግሞ ለከፋ ስህተት ይዳርጋል:: "ገንዘብን የማይወድ" የሚለው ሐረግ "አፊላርጊሮስ" ከሚለው ከአንድ ወጥ የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው:: ይህ መመዘኛ ሁለት ሥርወ ቃላት አሉት:: አንደኛው "አርጉሮስ" (ብር ወይም ገንዘብ) የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "ፊሌኦ" (መውደድ ወይም ማፍቀር) የሚል ነው [23]::

የሽማግሌ ልብ ገንዘብን መውደድ ላይ መሰቀል የለበትም:: እንዲሁም ነገሩ ሁሉ መያያዝ ያለበት በዚህ ምድር አላፊ ጠፊ ከሆነ ነገር ጋር ሳይሆን ከወዲያኛው ዓለም ነገር ጋር ነው (ማቴ 6÷19-24):: ካለፉት ሃምሳ አመታት ወዲህ አንዳንድ ቤተክርስቲያናት የመንፈሳዊ ውድቀት መናኸሪያ ለመሆን የበቁት ለገንዘብ የተንሰፈሰፈ ልብ ካላቸው መሪዎች የተነሣ ነው:: ለቁሳዊ ነገር ከፍተኛ ግምት በሚሰጥበት ዓለም ውስጥ የሚኖር ሽማግሌ የገንዘብን ጉዳይ በአግባቡና በጥንቃቄ መመልከት መቻል አለበት:: ደግሞም ስለ ገንዘብ በተነሳ ቁጥር ማንነቱና አመለካከቱ በጥያቄ ስር መውደቅ የለበትም:: የተሰጠውንም ኀላፊነት መከታ በማድረግ የንዋይ ማጋበሻ መንገድ ማድረግ የለበትም (1ተሰ 2÷5 ):: ነጋም ጠባም ስለ



ገንዘብ ማሰብ ልብን የሚያሸፍት ክፉ ነገር መሆኑን ጳውሎስ ለወጣቱ ጢሞቴዎስ ሲጽፍ "... ገንዘብን መውደድ የክፉት ሁሉ ሥር ነውና÷ አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ::" (1ጢሞ 6÷10) ብሏል:: እንግዲህ ሽማግሌ "ያለኝ ይበቃኛል" (1ጢሞ 6÷6) የሚለውን ትምህርት በሚገባ የተረዳና ራሱንም በዚህ መርህ ስር የሚያኖር መሆን አለበት (ዕብ 13÷5)::

ለሽምግልና አገልግሎት የሚመረጡ ሰዎች ለገንዘብ የሚስገበገቡና የሚዋደቁ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ÷ ከዚህ የሚከተሉት ጥያቄዎች ተጨባጭ ፍንጭ ሊሰጡን ይችላሉ:: ለአገልግሎቱ የታጩት ሰዎች ትልቅ ትኩረት የሚሰጡት ለሰዎች ነው ወይስ ለነገሮች (ለገንዘብ÷ ለቁሳቁስ ወዘተ...)? ዕጩዎቹ ባለ ጠጋ ከሆኑ ባለጠጋ ወይም (ሀብታም መሆን በራሱ መጥፎነት የሌለው መሆኑ ሳይዘነጋ) ወዳጅነታቸው ሁሉን አቀፍ (ያለውንም የሌለውንም) ነው ወይ? ያላቸውን ጊዜ ሁሉ የሚያውሉት ሀብትና ንብረት በመሰብሰብ ላይ ነው? ወይስ ሌሎችን ባላቸው ነገር ሁሉ በመርዳትና በመደገፍ? ስለ ሽምግልና ያላቸው አመለካከት ምንድን ነው? ሽምግልናን የሚያዩት የጥቅም ማግኛ መንገድ አድርገው ነው ወይስ ምዕመናንን የማሳደጊያ ቦታ አድርገው? እነዚህ ጥያቄዎች የዕጩዎቹን ማንነት በሚገባ የሚፈትሹ ናቸው:: ከአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችና ሕይወታቸው እንደምንረዳው÷ ሽማግሌ በእግዚአብሔር ጸጋ ተመክቶ የእግዚአብሔርን መንጋ የሚንከባከብ ነው:: ሽማግሌ የእምነት ሰው ካልሆነ እንደምን ብሎ ነው ሌሎችን በእምነት ኑሩ በማለት ሊመክር የሚችለው? ምዕመናን የእምነት ሰዎች መሆን የሚችሉት ሽማግሌዎችም የእምነት ሰዎች ሲሆኑና ሆነውም ሲገኙ ነው:: ትላንትናና ዛሬ ብቻ ሳይሆን ነገም በእግዚአብሔር እጅ ነው:: ሽማግሌ እግዚአብሔርን እንጂ ገንዘብን መታመኛው ሊያደርግ አይገባም:: ምክንያቱም እግዚአብሔር የዛሬ ብቻ ሳይሆን የነገም አምላክና ጌታ ነውና::

### 8.13 "... ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ ... ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር"

አንድ ሰው የመሪነት ወይም የአስተዳዳሪነት ችሎታ እንዳለው በተጨባጭ ማረጋገጥ የሚቻለው ይህ ሰው የገዛ ራሱን ቤት በእንዴት ያለ ሥነ-ሥርዓት መርቷል ወይም አስተዳድሯል? የሚለውን ጥያቄ በበቂ ሁኔታ መመለስ ሲቻል ነው:: የብሉይ ግሪካውያንና ሮማውያን መሪዎቻቸውን ይመርጡ የነበረው የቤተሰብ አያያዛቸውን ከመረመሩ በኋላ ነበር:: በሌላ አነጋገር የአንድ ምስጉን መሪ ችሎታ የሚለካው ከቤተሰቡ ሁኔታና አያያዝ አኳያ ነው:: ለጥንት ሰዎች፥ ቤተሰብ የመሪነት ችሎታ መመዘኛ ቦታ ነበር:: የአመራር ችሎታውንና ብቃቱን በቤተሰቡ አኗኗር ላይ በተግባር ያላሳየ ሰው ለማንኛውም የአመራር ቦታ አይመረጥም ነበር:: ምክንያቱም የገዛ ራሱን ቤት በመልካም ሥነ-ሥርዓት ማስተዳደር ያልቻለ ሰው ፋይዳ ያለው አመራር በሌላም ስፍራ ሊሰጥ ከቶ አይችልም የሚል እምነት ስለነበራቸው ነው [24] ::

በጥንት ዕብራውያንም ዘንድ ተመሳሳይ የሆነ አመለካከት እንዳለ በግልጽ መረዳት ይቻላል:: ልጆች በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚያሳዩት ባህርይ አብዛኛውን ጊዜ ተወልደው ያደጉበትን ቤተሰብ አኗኗር ያመለክታል:: በሥነ-ሥርዓት ያላደጉ ልጆች የቤተሰባቸውን ስም ያጎድፋሉ:: ለጥንት አይሁዳውያን ቤተሰብን በሚገባ ማስተዳደር ማለት መልካም ማኅበረሰብ ማፍራት ማለት ነው:: አይሁዶች ቅዱሳት መጻሕፍትን ለልጆቻቸው ማስተማር የሚጀምሩት ገና ሕፃናት እያሉ ነው (ዘዳ 6፥7፤ መዝ 71፥17፤ 78፥1-5) [25]::

የራሱን ቤተሰብ እንደሚገባ ማስተዳደር የማይችል ሰው የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ለማስተዳደር የተገባ ሰው አይሆንም:: የሽማግሌዎች ማንነት መለካት ያለበት በባለጠግነታቸው ወይም በታዋቂነታቸው ሳይሆን በቤተሰብ



አያያዛቸው ነው 26 :: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ሽማግሌ " ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር" መሆን አለበት (1ጢሞ 3፥4):: ይህ ማለት ግን ሽማግሌ የግድ ልጆች ያሉት መሆን አለበት ማለት አይደለም:: ነገር ግን ሽማግሌ ልጆች ያሉት ከሆነ ልጆቹን በሥርዓት የሚመራ መሆን ይጠበቅበታል ማለት እንጂ:: የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን የሚያስተዳድሩ ሰዎች ቤታቸውንና ትዳራቸውን በሚገባ የሚመሩ መሆን አለባቸው:: ልጆቹን በማበሳጨትና በማስመረር የሚያስተዳድር ሽማግሌ ምዕመናንንም እንዲሁ ሊያበሳጭና ሊያስመርር ይችላል:: ሐዋርያው "ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?" (1ጢሞ 3፥5) በማለት ለጢሞቴዎስ ሁነኛ ጥያቄ ያቀረበው ለዚህ ነው:: የሽማግሌዎች የአስተዳደር ችሎታና ብቃት ምን እንደሚመስል በትክክል ማወቅ ከፈለግን ቤተሰባቸውን ብቻ መመልከት በቂ ነው:: የገዛ ቤቱን በሚገባ ማስተዳደር የማይችል ሰው በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚገጥመው አስተዳደራዊ ችግር ትክክለኛ መፍትሄ ሊሰጥ ያዳግተዋል::

### 8.14 "...ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ ... አዲስ ክርስቲያን ያልሆነ"

በክርስቲያናዊ አገልግሎት ውስጥ ብስለት (maturity) ትልቅ ቦታ አለው:: ክርስትና የብስለት ደግሞም የዕውቀት ጠላት አይደለም:: "አዲስ ክርስቲያን ያልሆነ" የሚለው ሐረግ "ኔኦፊቶስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ሲሆን በቁሙ (literally) "አዲስ ተክል ወይም ገና አሁን የተተከለ" ማለት ነው [27]:: ጳውሎስ ይህንን ቃል በዚህ ቦታ የተጠቀመው በቀጥተኛ ትርጉሙ ሳይሆን በዘይቤያዊ (metaphoricall) ትርጉሙ ነው:: እንደ ሐዋርያው አባባል አዲስ ያመነ ክርስቲያን ወይም ገና በቅርቡ ያመነ ሰው ለሽምግልና መመረጥ የለበትም:: ይህ አዲስ አማኝ ምንም ያህል ቀናኢ ክርስቲያን ቢሆንም በመንፈሳዊ ነገር ግን የሰከነ ወይም የበሰለ

አይደለም:: ብስለት ደግሞ ልምድና ጊዜን ይጠይቃል:: በመሠረቱ ከልምድና ከጊዜ ውጪ ብስለት ሊመጣ አይችልም:: አዲስ አማኝ ለሽምግልና የማይበቃውም ለዚህ ነው::

እርግጥ ነው ማንኛችንም ብንሆን በአንድ ወቅት አዲስ አማኞች ነበርን:: አዲስ አማኝ መሆን በራሱ መጥፎነት የለውም:: በክርስትና ሕይወት ማደግና መብሰል ያለ ነገር ነው (1ቆሮ 3፥1-2):: አዲስ ያመነ ሰው ለምን ይሆን ለመሪነት መመረጥ የማይችለው? የሚል ጥያቄ እናነሣ ይሆናል:: ምክንያቱን ራሱ ጳውሎስ ሲገልጽ፡- "በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ ክርስቲያን አይሁን" ይላል (1ጢሞ 3፥6):: መጽሐፍ ቅዱስ "ትዕቢት ጥፋትን፥ ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል" ሲል ሐቅ ነገርን መናገሩ ነው (ምሳ 16፥18፤ እንዲሁም ምሳ 11፥2፤29፥23 ይመለከቷል):: ትዕቢት አያሌ የእግዚአብሔር ሰዎችን ለጥፋት ዳርጓል:: ሌላው ቀርቶ እጅግ የሰከኑ ወይም የበሰሉ አማኞች እንኳን ከበላይነት ስሜት ጋር ሳይፋለሙ የሚያልፉበት ጊዜ የለም:: ታላላቅ ሰዎች በትዕቢት ሲወድቁ፥ በዕብሪተኛነታቸውም ሲጠፉ በግልጽ ታይቷል (2ዜና 26፥16፤ 32፥25):: ትዕቢት ባለበት ቦታ ሁሉ ውድቀትም አለ:: ዲያቢሎስም ያን ከመሰለ ክብሩ የተዋረደው በትዕቢቱ ነው (ሕዝ 28፥ 11-19፤ ኢሳ 14:12-15):: ልክ እንዲሁ በትዕቢት የሚያዙ ሰዎች ሁሉ አንድ ቀን ተምዘግዝገው ይወድቃሉ:: መንፈሳዊ ብስለት ግን ይህን ሁሉ ሊያስቀር ይችላል::

ጳውሎስ "አዲስ ክርስቲያን ሽማግሌ አይሁን" ያለው ከአዲስ አማኞች ጋር ጠብ ኖሮት አይደለም:: ይልቁንም ያለ ጊዜው በሚገኝ ሹመት ለከፍተኛ ውድቀት እንዳይጋለጡ በማሰብ ነው:: በትዕቢት የሚመጣ ውድቀት አማኙን ብቻ ሳይሆን ማኅበረ ምዕመናኑንም ጭምር ይጎዳል:: ምዕመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው መበርታትና መጠንከር የሚችሉት በነገር ሁሉ የበሰሉና የሰከኑ ሽማግሌዎች ሲኖሯቸው ነው:: ያለንበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ክርስትናም ራሱ በሳል



ሽማግሌዎችን ይሻል:: 1ጢሞ 3፥6 ለቤተክርስቲያን ወቅታዊ መመሪያ ነው::

## 8.15 "ኤጲስቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤... በውጭ ካሉት ሰዎች መልካም ምስክርነት ያለው"

እግዚአብሔር በትልቁ የሚጠላው ነገር ቢኖር ግብዝነትን (hypocrisy) ነው:: አንድ አማኝ በቤተክርስቲያን ውስጥና ከቤተክርስቲያን ውጪ ምንም ተፋልሶ የሌለው አኗኗር ሊኖረው ይገባል:: በወንድሞች መካከል የሚኖረን አረማመድና በሥራ ቦታ፥ በትምህርት ቤት፥ ወዘተ... የሚኖረን አረማመድ ለየቅል መሆን የለበትም:: ሰዎች ክርስትናን የሚለኩት ከመሪዎች አኳያ ነው:: የአንድ ሽማግሌ አረማመድ መለካት ያለበት "ከሰኞ እስከ ቅዳሜ" ባለው አረማመዱ እንጂ "በእሁድ አኗኗሩ ብቻ አይደለም":: የማያምኑ ሰዎች ስለ ማንነታችን ምንም አያውቁም ብሎ መደምደም ትልቅ ስህተት ነው:: እምነታችንን ብቻ ሳይሆን አረማመዳችንንም ጭምር ይመዝናሉ:: እናም እምነት ወዲያ አረማመድ (ተግባር) ወዲህ ሊሆን አይገባም (ያዕ 2፥26)::

ለየቅል የሆነ አኗኗር ያለው ሽማግሌ፥ ስኬታማ አገልግሎት መስጠት ከቶ አይችልም:: ከቤተክርስቲያን ውጪ ያለው አረማመድ ዘወትር የሚከሰው ከሆነ ምዕመናንን እንደሚገባ መምከርና መውቀስ፥ የተሳሳቱትንም ለማረምና ለማቅናት የልብ ድፍረት አይኖረውም:: በጥቅሉ እንደ እግዚአብሔር መጋቢ በኃይልና በሥልጣን መመገብ ይሳነዋል:: ይህም ሌሎችን ለበጎ ሥራ የማነሳሳት ተልዕኮውን ሙሉ በሙሉ ያዳፍንበታል:: የሽማግሌዎች አኗኗር ጥያቄ የሚያስነሳ መሆን የለበትም:: ጳውሎስ እንዳለው መልካም ምስክርነት የሌለው ሽማግሌ "በዲያቢሎስ ነቀፋና ወጥመድ ውስጥ ሊወድቅ " ይችላል (1ጢሞ 3፥7):: አንድም ቀን የማይተኛልን ባላጋራ ዲያቢሎስ ነው:: ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲጽፍ "... ባላጋራችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና (1ጴጥ 5፥8) ብሏል:: ሰይጣን ከየአቅጣጫው ክስና ትችት በማስነሣት ለከፋ ጉዳት ሊያጋልጠን ይችላል::

ይህ ደግሞ በእኛ ላይ ብቻ ሳይሆን በክርስቶስም ላይ ነቀፋን ያስከትላል:: ሰይጣን እኮ ተንኮለኛ ነው፤ እሱ የሚፈልገው መግቢያ ቀዳዳ ብቻ ነው:: እንዲህ ሲባል ግን ሰይጣን ያሻውን ማድረግ የሚችል፥ ከበላዩም ማንም የሌለበት ብርቱና ኃያል ነው ማለት አይደለም:: ነገር ግን ዲያቢሎስ ሁልጊዜ ግብ አለው፤ ያም ግብ ሰዎችን ተስፋ ወደ መቁረጥ ማድረስ ነው (1ቆሮ 2፥5-11):: ቤተክርስቲያን ከእንዲህ ዓይነቱ ችግር ማምለጥ የምትችልበት አንደኛው መንገድ "በውጭ ካሉት ሰዎች ደግሞ መልካም ምስክር" (1ጢሞ 3፥7) ያላቸው ሽማግሌዎች ሲኖሯት ነው::



# የግርጌ ማስታወሻ

## ምዕራፍ አንድ


1 Robert L. Saucy "The church in God's program" (Moody press, Chicago, 1972) p. 11

2 Karl Ludwig Schmidt," ekklesia" in Theological dictionary of the new Testament vol.3 p. 501- 536

3 Schmidt, vol.1 514

4 Francis Brown, S.R. Driver, and Charles A. Briggs, "A Hebrew and english Lexicon of the old testament" p. 874

5 W.F. Moulton and A.S Geden, "A Concordance to the Greek Testament" p. 316-317

6. Alan W. Gomes, "unmasking the cults" (Zondervan publishing house, Grand Rapids, Michigan, 1995 )p. 19-20

7. ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 19-20

8. A.M. Renwick, "The story of the church"(Inter-Varsity Fellowship, London, 1968) p. 108-110

9. Ron Rhodes, "New age movement" (Zondervan publishing house, Grand rapids, Michigan 1995)p. 8

10. ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 7-8


## ምዕራፍ ሦስት


1 James M.Boice, "foundations of the christian faith"( Downers grove :Inter-varsity press, 1986) p. 632

2 Gene getz, "sharpening the focus of the church" (Chicago: moody press, 1974) p. 121

3 John R. Macarthur ,Jr, "answering the key questions about elders" (panorama city: word of grace communications, 1984) p. 27

4 Gordon D. Fee and Douglas stuart,"How to read the Bible for all its worth" (City road :London, Scripture union,1982) p. 59

5 ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 59፣ እንዲሁም Alexander strauch,"Biblcal eldership" (Colorado: Lewis and Roth publishers, 1986) p. 140
6 Bruce stabbert, "The team concept" (Tacoma : Hegg Bros , printing 1982) p. 27-44
7 ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 27-44
8 Jon zens, "The major concepts of elderships in the new testament" (baptist reformation review 7, summer , 1978) p. 28
9. Archibald Thomas Robertson, "Paul's Joy in Christ" (Grand Rapids: Baker book house 1979) p. 43
10. John R.W. Sttot, "the message of Ephesians" (Inter-Varsity press, Leicester, England 1979) p. 167
11. ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 167

## ምዕራፍ አራት

1. Wayne Grudem, "systematic Theology" (Grand Rapids: Zondervan publishing house, 1994) p. 913
2. Robert L.Saucy, " The Church in God's Program" (Chicago: Moody Press, 1972) p. 142
3. Saucy, vol.1 142
4 J.B. Lightfoot. "St. Paul's Epistle to the philippians" (Grand Rapids: Zondervan, 1953; በመጀመሪያ በ1868 ታተመ) p. 95-99
5 Lightfoot, p. 95
6. Homer A.Kent, Jr, "The postoral Epistles" (Chicago: Moody press, 1976) p. 122 እንዲሁም Saucy, p. 142
7. Hermann W. Beyer, "episkopos", TDNT, 2: 608 - 622

## ምዕራፍ አምስት

1. Arthur G.Patzia, "Ephesians, Colossians, Philemon (NIBC) (Hendrickson Publishers, 1993) p. 240
2. John R.W. Stott, "The message of ephesians: God's New society" (Inter-varsity press ,1989) p. 160



3.Wayne Grudem, "Systematic Theology" p. 913
4. Markus Barth as quoted in John R.W. Stott, "The message of Ephesians" (Inter-varsity press, Leicester, 1989) p. 166

## ምዕራፍ ስድስት

1 Donald G. Miller, "The nature and mission of the Church"( Richmond John Knox ,1957) p. 82
2 John Eadie ," Commentary on the Epistle of Paul to the Galations" (Grand Rapids : Zondervan, 1957) p. 98
3 Robert L.Saucy "The church in God's program" (Moody press: Chacago, 1972) p. 109
4 Oscar cullmann, "The Traditon in the Early Church" ed. A.J.B. Higgins, (London : SCM, 1956) p. 78
5 Saucy, p. 110
6 በዚህ አገባቡ ሥልጣን የሚለው ቃል ልል ትርጉም ነው ያለው። በአንድ በኩል ምዕመናን በሌላ በኩል ደግሞ ሽማግሌዎች ሥልጣን አላቸው ሲባል የሚያስጠይቃቸው ኀላፊነት አለባቸው ማለት ነው። ይህ ሥልጣን መያዣ መጨበጫ የሌለውና ማንም እንደፈለገ የሚዘባነንበት ሥልጣን አይደለም። የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ባለው መንገድ መጓዝ እንድትችል የአመራር ስልት የሚያጎናጽፉት እንጂ። በዚህ አጠቃቀም ውስጥ አምባገነናዊ አመለካከትን የሚያሳይ አንድም ነገር የለም፣ ሊኖርም አይገባም። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ይህንን ቃል የምንጠቀምበት በዚህ ፍቺው ነው።
7 Saucy, p. 116
8. Howard A.Snyder, "The problem of wineskins: Church Structure in a Technological Age" (Downers Grove: ill, Inter-varsity press, 1975) p. 89-99
9. ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 160

## ምዕራፍ ሰባት

1 Leon Morris, "The First and second Epistles to the Thessalonians" (Grand rapids: Eerdmans , 1959) p. 165
2 Ralph Earle, "1 Timothy" The Expositor's Bible commentary, ed. Frank Gaebelein (Grand Rapids: Zondervan publishing House, Vol.1 11,1979) p.380

3 "እነሱ ስላሉን ሳይሆን እግዚአብሔር ስላለን ነው" የሚለው ሐረግ "እነሱ የእኛ ስለሆኑ ሳይሆን እግዚአብሔር የእኛ ስለሆነ ነው" የሚል ሌላ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል:: በዚህ ቦታ ግን ለማለት የተፈለገው "እነሱ ታዘዙን ብለው ስለተናገሩን ሳይሆን እግዚአብሔር ታዘዟቸው ብሎ ስለተናገረን ነው" በሚለው አገባቡ ነው:: እግርጥ ዓውደ ንባቡም ቢሆን የመጀመሪያውን ሳይሆን ሁለተኛውን ፍቺ ነው የሚያጸናልን::

4 Leon Morris, " Hebrews" The expositor's Bible commentary ed. Frank Gaebelein (Grand Rapids: Zondervan publishing house, Vol 12,1978) p.153

5 በዘይቤአዊ ወይም በፈሊጣዊ አነጋገር ውስጥ "ጠምዛዜ"(Litotes) በመባል የሚታወቅ የአነጋገር ፈሊጥ ወይም ዘዬ አለ:: ጠምዛዜ በአሉታ ተነግሮ የአዎንታ መልእክት ማስተላለፊያ ነው:: ለምሳሌ ፣ አልሠራሁም አይባልም (ሠርተሃል ለማለት) ቀላል ሥራ አይደለም (ከባድ ሥራ ነው ለማለት)፤ አያሌው አስረስ "ዘይቤአዊ አነጋገር" ከትምህርት ዓለም መጽሔት ቅጽ 14፣ ቁጥር 1፣ ሚያዝያ 1987፤ ገጽ 28

6 Alexander Strauch, "Biblical Eldership" (Littleton, Cololrado: Lewis and Roth publishers, 1988) p. 164-165

7 George W. Knight, "The pastoral Epistles" (Grand Rapids: Eerdmans, 1992) p. 231

8 Alexander Strauch, "Biblical Eldership"(Colorado: Lewis and Roth publishers, 1988) p. 144

9 Alexander Strauch, "Biblical Eldership" (Colorado: Lewis & Roth publishers, 1988) p. 146

10 Alan Stibbs, "God's Church" (Chicago: Inter-varsity, 1959) p. 92

11 ለመሆኑ እነዚህ ቡድኖች እነማን ናቸው? የሚል ተገቢ ጥያቄ ይነሣ ይሆናል:: እነዚህ ቡድኖች "የሀብት፣ የጤንነትና የእምነት" አስተማሪዎች በመባል ይታወቃሉ:: የእነዚህ ቡድኖች ልምምድ ከእኛ ልምምድ ጋር በብዙ የሚመሳሰል በመሆኑ የእኛው ወገን ሊመስሉን ይችላሉ:: የደረቡትን ካባ ብንገልጠውን ግን ሁኔታው እጅግ አስደንጋጭ ሆኖ እናገኘዋለን:: ከጳውሎስ ቋንቋ ካልተዋስን በቀር የትምህርታቸውን ኑፋቄነት በቀላሉ መግለጽ አይቻልም:: የእነዚህ ቡድኖች ትምህርት "ልዩ ኢየሱስ፣ ልዩ መንፈስ፣ ልዩ ወንጌል" ነው:: የደረቡት ካባ እንጂ ውስጣቸው እኛን አይመስልም:: የልዩነቱን ድንበር አደብዝዘውታል የተባለውም ለዚህ ነው::

12 David Watson, "called and Committed: World -Changing Discipleship



## ምዕራፍ ስምንት

1. Ralph Earle, " 1 Timothy" The Expository Bible Commentary, ed. Frank E. Gaebelein (Grand rapids: Zondervan 1978 vol 11) p. 364
2. Antenicene Fathers, Ed by Alexander Roberts & James Donaldson (Grand Rapids: Wm.B. Eerdmans, 1951, Vol 7) p. 457
3. Dictionary of Jesus and the Gospels (Inter Varsity press, 1992) p. 192-198
4. Josephus, Ant., 15.7.10.259
5. Ed Glasscock "The husband of one wife's requirement in 1 Timothy 3:2" (Bibliotheca sacra 140 [July - September, 1983] ) p. 256
6. William Barclay, "The pastoral Epistles"
7. Josephus, "Antiquites", 17.14
8. Dialogue with Trypho, Chap. 134
9. ሄሮዶተስ - 420 ዓ.ም 1.135 እና 4.155፣ 2 መቃብያን 4፣30-170 ዓ.ዓ. ቱርሊያን "አፖሎጂ" ገጽ 46
10. Wayne Grudem, "Systematic Theology" (Grand Rapids: Zondervan, 1994) p. 917
11. Ralph Earle, "1Timothy," in The Expositors's Bible commentary, ed. by Frank E.Gaebelein (Grand Rapids :Zondervan, 1978,vol. 11) p. 346
12. Alexander Strauch, "Biblical Eldership"(Colorado: Lewis and Roth publishers, 1986) p. 195-196
13. Homer A. Kent, Jr "The pastorl Epistles", Chicago: Moody press, 1982, ገጽ 126-ጆሲፈስ ከ37-110 ዓ.ም የኖረ አይሁዳዊ የታሪክ ጸሐፊ ነው
14. Homer A.Kent,Jr. "The Pastoral Epistles"(Chicago: Moody Press, 1982) p. 127
15. Craig S. Keener, "The IVP Bible background commentary NT", (downers grove, ill: Inter varsity press, 1993) p. 612-613
16. Ralph Earle "1 Timothy" The Expositor's Bible Commentary,ed.Frank E.Gaebelein (Grand Rapids: Zondervan,1978, vol.11) p. 364
17. Craig S.Keener, "The IVB Bible background commentary Nt," (Downer Grove, ill: Inter Varsity press, 1993) p. 635-636
18. The Expositor's Bible Commentary, Ed. Frank E. Gaebelein, Grand Rapids: Zondervan, 1978, Vol.11, ገጽ 365
19. ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 365

20. E.K. Simpson and F.F. Bruce, "commentary on the Epistles to the Ephesians and the colossians" (London: marshall, Morgan and Scott, 1957) p. 51
21. Ralph Earle "1 Timothy" The Expositor's Bible Commentary, Rd. Frank E Gaebelein (Grand Rapids: Zondervan, 1978, Vol. 11)p. 365
22. Homer A.Kent, Jr. "The pastoral Epistles" (Chicago : Moody press, 1992) p. 129
23. ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 128
24. Craig S. Keener "The ivp Bible background Commentary NT" (ill Downers Grove, Inter varsity press 1993) p. 613
25. ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 630
26 ባለጠጋ ወይም ታዋቂ ሰው መሆን ክፉ ነገር ነው የሚል አስተሳሰብ ከቶውን የለንም:: ወይም ደግሞ ባለጠጋና ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ሁሉ ቤታቸውን እንደሚገባ ማስተዳደር አይችሉም የሚል አቋምም የለንም:: በዚህ ቦታ ለማለት የተፈለገው ሰዎችን ለሽምግልና ስናጭ መለኪያችን ሀብትና ዝና መሆን የለበትም ነው:: መለኪያችን መሆን ያለበት የቤት አያያዝ ነው:: አሁንም ለማስገንዘብ የምንወደው ባለጠጋና ታዋቂ ሰዎች የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ሊሆኑ አይገባም ያልተባለ መሆኑን ነው::
27. Ralph Earle "1 Timothy" The expositor's Bible commentary, ed fank E.Gaebelein (Grand rapids: Zondervan, 1978, vol 11) p. 365



# የቃላት መፍቻ

1. መመዘኛ - መለኪያ (የአንድን ሰው ጠባይ፥ ባሕርይ፥ ወዘተ መዘን፥ ገመገመ)
2. መርህ - መመሪያ
3. መስፈርት - መመዘኛ፥ መለኪያ
4. ሰፕቱዋጀንት - ሰብዐ ሊቃናት (ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ድርክ ወይም ግሪክ የተረጎሙ ሊቃውንት
5. ሥርወ ትውልድ- የዘር ሐረግ፥ በዘር የሚገኝ ሥልጣንና ሹመት
6. ሥነ-ሐቲት (Exegesis) - ሐታቲ ከሚል ቃል የመጣ ነው፤ ጠያቂ መርማሪ ማለት ነው፤ የአንድን ንባብ ፍቺ ከዚያው ከንባቡ ውስጥ ፈልፍሎና አመራምሮ ማውጣት
7. ብሉይ (Classical) - ጥንታዊ፥ ቀዳማዊ
8. በቁሙ(Literally) - በቀጥታ፥ ቃል በቃል ወይም በጥሬው ትርጉሙ
9. ብዙኀናዊ - ከአንድ በላይ ወይም በርካታ ሰዎች የሚሰጡትን አመራር የሚወክል ቃል
10. ተመርሆ - ቋሚ መመሪያ (ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ)
11. ንባብ/ንባባት (Text)- የንባብ ክፍል (አንቀጽ፥ ምዕራፍ)
12. አሀዳዊ - አንድ ብቻ
13. አማከለ - ነገርን ሁሉ ወደ አንድ ማዕከል ወይም እምብርት ወሰደ
14. አጥቢያ - አንድ ቤተክርስቲያን ያለችበት ቦታ፥ አካባቢ፥ ክልል፤ ስብከትና ትምህርት የሚሰጥበት
15. እሳቤ (Concept)- ስለ አንድ ነገር ያለን አስተያየት፥ አመለካከት
16 ዋሕዳዊ - አንድ ሰው ብቻ የሚሰጠውን አመራር የሚወክል ቃል

17. ግሪካዊ- ሮማዊ - (Greaco-Roman)

18.. ጽንፋዊነት - ወደ አንድ አቅጣጫ ኸው ብሉ የሸመጠጠ÷ የከረረ አቋም

19. አግድማዊ - ጎናዊ ወይም ወደጎን

20 መክሥተ - መከሰቻ÷ መግለጫ÷ ማስታወቂያ÷ ማጣቆሚያ



# ዋቢ መጻሕፍት


Barclay Wlilliam,. The Pastoral Epistles.

Boice, James M. Foundations of the Christian faith. Downers grove, Inter- varsity press, 1986.

Cullman, Oscar. The Tradition in the early church. ed by A.J.B. Higgins. London. SCM, 1956.

Earle, Ralph. 1 Timothy. In The Expositors Bible Commentary, ed by Frank E. Gaebelein. Grand Rapids, Zondervan publishing house. vol. 11, 1979.

Fee, Gordon D. and Douglas Stuart. How to read the Bible for all its worth. London, Scripture Union, 1982.

Gets, Gene. Sharpening the focus of the church Chicago , Mood press, 1974.

Glassock, Ed. The Husband of one Wife's Requirement in 1 Timothy. Bibliotheca Sacra 1983.

Grudem, Wayen. Systematic Theology. Grand rapids, Zondervan publishing house, 1994.

Gomes. Alan. W. Unmasking the Cults. Michigan, Zondervan publishing house, 1995.

Kent, Homer A. The Pastoral Epistles. Chicago, Moody press, 1976.

Keener, Craig S. The IVP Bible background commentary NT. ill, Inter - Varsity press, 1993.

Knight, George W. The Pastoral Epistles. Grand Rapids, Eerdmans, 1992.

Lightfoot, J.B. St. Paul's epistle to the Philipplains. Grand Rapids, Zlondrervan, 1953.

MaCarthur, John R. Answering the Key Questions About Elders. panorama, word of grace communication, 1984.

Miller, Donald G. The Nature and Mission of the Church. Richmond John Knox, 1957.

Morris, Leon. The First & Second Epistles to the Thessalonians. Grand rapids, Eerdmans, 1959.

Patzia, Arthur G. Ephesians, Colossians, Philemona (NIBC), Hendrickson, 1993.

Enwick, A.M. The Story ot the Church. London, Inter- varsity press, 1968.

Robertson, Archibald. Paul's Joy in Christ. Grand rapids, Baker book house, 1979.

Rohdes, Ron. New age movment. Michigan, Zondervan publishing house, 1974.

Saucy, Robert L. The church in God's program. Chicago, Moody press, 1972.

Simpson E.K. and F.F Bruce. Commentary on the Epistles to the Ephesians & the Colossians. London, Morgan and Scott, 1975.

Snyder, Howard A. The problem of Wineskins: Church structure in a technological age. ill, Inter - Varsity press, 1975.

Stabbert, Bruce. The Team Concept. Tacoma, Hegg Bros, 1982.

Stibbs, Alan. God's Church. Chicago, Inter - Vasity press, 1959.

Stott, John R.W. The Message of Ephesians. Leicester, inter-varsity press, 1979.

Strauch, Alexander. Biblical Eldership. Colorado, Lewis and Roth publishers, 1988.

Watson, David. Called & Committed: World- Changing Disipleship.

Zens, Jon. The Major Concepts of Eldership in the NT. Baptist Reformation Review, 1979.